# የአማርኛ ተረትና ምሳሌዎች

በዳንኤል አበራ

1998 ዓ.ም.

## መግቢያ

ይህ የተረትና ምሳሌዎች ስብስብ ከተለያዩ ምንጮች የተጠናቀረ ሲሆን፤ ያሰባሰብኳቸው ለራሴ ጉዳይ ቢሆንም፤ እንዴ ከተየብኳቸው በኋላ ለሌሎችም የሚጠቅም ከሆነ ልካፈለው በሚል መንፈስ አቀርቤዋለሁ። የከርሞ ሰው ይበለንና ተረትና ምሳሌዎቹን አበጃጅተን ወግ እናወጋለን። አስተያየት ለሚኖራችሁ danlinet@yahoo.com ብትሰዱልኝ ይደርሰኛል።

## ምስጋና

አቶ አምሓ አስፋው ይህንን የአማርኛ ተረትና ምሳሌዎች መድበል በድረ-ገጹ ለማካተትና ለታዳሚ ለማድረስ ስለተባበረኝ በራሴና በእናንተ አንባቢዎች ስም ምስጋናዬ የላቀ ነው።

## መታሰቢያነቱ

ለቋንቋ እድገት ባተሌዎች
ለቋንቋ ውበት አድናቂዎች
ለቋንቋ እድገት ናፋቂዎች

ሀ
ሀሜተኛ ነው ከዳተኛ
ሀሜተኛ ያፍራል ሀሰተኛ ይረታል
ሀሜተኛ ያፍራል እውነተኛ ይረታል
ሀሜት አይቀር ከድሀም ቤት
ሀሜትና ጅራት በስተኋላ ነው
ሀምሌ ቢያባራ በጋ ይመስላል
ሀምሌና ሙሽራ ሳይገለጡ ነው
ሀምሌን በብጣሪ ነሀሴን በእንጥርጣሪ
ሀምሳ ሎሚ ለሀምሳ ሰው ጌጡ ለአንድ ሰው ሸክሙ
ሀረጉን ሲስቡት ዛፉ ይወዛወዛል
ሀረጉን ሳብ ዛፉ እንዲሳሳብ
ሀረግ ለመዳፍ አልጋ ለምንጣፍ
ሀሰተኛ ምስክር ጉልበት ይሰብር
ሀሰተኛን ሲረቱ በወንድም በእህቱ
ሀሰተኛ ሲናገር ይታወቃል ስሱ ሲበላ ይታነቃል
ሀሰተኛ ሲናገር ይታወቃል በሶ ሲበሉት ያንቃል
ሀሰተኛ በቃሉ ሰደተኛ በቀሉ
ሀሰተኛ በቃሉ ሰደተኛ በቀሉ ይታወቃሉ
ሀሰተኛ ብርቱ ወንጀለኛ
ሀሰተኛ ያወራውን ፈረሰኛ አይመልሰውም
ሀሰት ስለበዛ እውነት ሆነ ዋዛ
ሀሰት ቢናገሩ ውቃቢ ይርቃል
ሀሰትና ስንቅ እያደረ ያልቅ
ሀሰት አያቀላ እውነት አያደላ
ሀሰት አያድንም መራቆት መልክ አያሳምርም
ሀሰት እያደር ይቀላል እውነት እያደር ይበራል
ሀሰት እያደር ይቀላል እውነትና ውሀ እያደር ይጠራል
ሀሰት ነገር ክፉ ገሀነም እሳት ትርፉ
ሀሳቡ ጥልቅ ነገሩ ጥብቅ
ሀሳብህን ጨርቅ ያድርገው
ሀሳብና መንገድ ማለቂያ የለውም
ሀሳብ ከውለታ አይቆጠርም
ሀሳብ ከፊት አይፈታ ሙት አይመታ
ሀሳብ ያገናኛል ፍራት ያሸኛኛል
ሀሳብ ያገናኛል ፍርሀት ያሸኛኛል
ሀ ሳይሉ ጥፈት ውል ሳይዙ ሙግት
ሀ ባሉ ተዝካር በሉ
ሀ ባሉ ደሞዝ በሉ
ሀብታም ለሀብታም ይጠቃቀሱ ድሀ ለድሀ ይለቃቀሱ
ሀብታም ለሰጠ የድሀ ሙርጥ አበጠ
ሀብታም ለሰጠ የድሀ ሙርጥ ያብጣል
ሀብታም ለሰጠ ደሀ ምንጭሩ አበጠ
ሀብታም ለሰጠው ደሀ ይንቀጠቀጣል
ሀብታም ሊሰጥ የደሀ ቂጥ ያብጥ
ሀብታም ሊሰጥ የደሀው ሙርጥ ያብጣል
ሀብታም ሊሰጥ ደሀ ምርጥ ያወጣል
ሀብታም ሲወድቅ ከሰገነት ድሀ ሲወድቅ ከመሬት

ሀብታም በመመጸወቱ ድሀ በጸሎቱ
ሀብታም በከብቱ ድሀ በጉልበቱ
ሀብታም በወርቁ ድሀ በጨርቁ
ሀብታም በገንዘቡ ድሀ በጥበቡ እርስ በርስ ይቃረቡ
ሀብታም በገንዘቡ ይኮራል ድሀ በጥበቡ ይከበራል
ሀብታም በገንዘቡ ይኮራል ድሀ በጥበቡ ይከብራል
ሀብታም ቢሰጥ አበደረ እንጂ አልሰጠም
ሀብታም ቢያብር ድህነትን ያጠፋል
ሀብታም ነው መባል ያኮራል ድሀ ነው መባል ያሳፍራል
ሀብታም እንደሚበላለት ድሀ እንደሚከናወንለት
ሀብታም ያለ ድሀ አይኮራም ድሀ ያለ ሀብታም አይበላም
ሀብታም ገንዘቡን ያሰባል ድሀ ቀኑን ይቆጥራል
ሀብት እና እውቀት አይገኝ(ም) አንድነት
ሀብት የጠዋት ጤዛ ነው
ሀኪም ሲበዛ በሽተኛው ይሞታል
ሀኪም የያዘው ነፍስ ባያድር ይውላል
ሀኪሞች እስኪመካከሩ በሽተኛው ይሞታል
ሀዘንሽ ቅጥ አጣ ከቤትሽ አልወጣ
ሀዘንና ደስታ ጎን ለጎን ናቸው
ሀዘንን የፈራ በደስታ የተጣራ
ሀይለኛ ውሀ አሻቅቦ ይፈሳል
ሀይለኛ ዱቄት ከነፋስ ይጣላል
ሀይማኖቱ ከጅማት ጉልበቱ ከብረት የጠና
ሀይማኖት ከግብር ጸሎት ከፍቅር
ሀይማኖት ያለ ፍቅር ጸሎት ያለ ግብር
ሀይማኖት የሌለው ሰው ልጓም የሌለው ፈረስ ነው
ሀጢአት ለሰሪው ምህረት ለአክባሪው
ሀጢአት ሲደጋገም ጽድቅ ይመስላል
ሀጢአት ሳያበዙ በጊዜ ይጓዙ
ሀጢአት በንስሀ በደል በካሳ
ሀጢአት በንስሀ እድፍ በውሀ
ሀፍረት ያከሳል ያመነምናል
ሁለተኛ ደሞ ለዘበኛ! አሉ
ሁለተኛ ግፌ ጫንቃዬን ተገርፌ ልብሴን መገፈፌ
ሁለተኛ ግፍ ልብሴን ይገፍ ጀርባዬን ይገርፍ
ሁለተኛ ጥፋት ቆሞ ማንቀላፋት
ሁለተኛ ጥፋት ከገበያ ማንቀላፋት
ሁለተኛ ጥፋት ከገበያ ቆሞ ማንቀላፋት
ሁለቱን የተመኘ አንዱንም አላገኘ
ሁለቱን የተመኘ አንድም አላገኘ
ሁለቱን ወንበዴ በአንድ ዘዴ
ሁለቴ ሰላምታ አንዱ ለነገር ነው
ሁለት ሆነው የተናገሩት በመሬት የቀበሩት
ሁለት ሞት መጣ ቢለው አንዱን ግባ በለው አለ
ሁለት ሞግዚት ያለው ህጻን ያለጥርጥር በእሳት ይቃጠላል
ሁለት ቁና ሰጥቼ አንድ ጥንቅል
ሁለት ባላ ትክል አንዱ ሲሰበር ባንዱ ተንጠልጠል
ሁለት ባላ ትክል አንዱ ሲነቀል ካንዱ ተንጠልጠል

ሁለት ብልጥ ኑግ አያደቅ
ሁለት አይወዱም ከመነኮሱ አይወልዱም
ሁለት አይወዱ ከመነኩሴ አይወልዱ
ሁለት አይወዱ ከመነኮሱ አይወልዱ
ሁለት አገር አራሽ ለባልንጀራው አውራሽ
ሁለት እግር አለኝ ብሎ ሁለት ዛፍ አይወጡም
ሁለት እግር አለኝ ብሎ እሁለት ዛፍ አይወጣም
ሁለት እግር አለኝ ተብሎ ሁለት ዛፍ አይወጣም
ሁለት አፎች ባይናከሱ ይናቀሱ
ሁለት ወፎች ባይናከሱ ይናቀሱ
ሁለት የተመኘ አንድም አላገኘ
ሁለት የወደደ አንዱን ሳያገኝ ሄደ
ሁለት ጉድጓድ ያላት አይጥ አትሞትም
ሁለት ጊዜ ተናገርህ ከፋህ ሁለት ጊዜ በላህ ተፋህ
ሁለት ጊዜ ተናግረህ ከፋህ ሁለት ጊዜ በላህ ተፋህ
ሁለት ጊዜ ነው የዶሮ ልደት አንዱ በእንቁላል አንዱ በጫጩት
ሁለት ጊዜ ይፈርዱ ጉድ ይወልዱ
ሁለት  ጥፋ ካገር ይጥፉ
ሁሉ ሄዶ ተበተነ እህና እኔ ቀረነ አለ እያዘነ
ሁሉ ሄደ ተበተነ እህና እኔ ቀረነ አለ ያዘነ
ሁሉ ሆነ ቃልቻ ማን ይሸከም ስልቻ
ሁሉም ሰው መምሰሉ ባይታይ አመሉ
ሁሉም ሽክሙን ፍቅርም ያዥውን
ሁሉም በየዘመድህ ቢሉት አክንባሎ ጋጥ ገባ
ሁሉም አካል ነው ግን እንደአይን አይሆንም
ሁሉም ከኋላው ያገኘዋል እንደሰራው
ሁሉም ከልኩ አያልፍም
ሁሉም ወንፊሉን ፈታይም ድውሩን
ሁሉም ያልፋል እውነት ብቻ ይተርፋል
ሁሉ በእጄ ሁሉ በደጄ
ሁሉ ቢናገር ማን ይሰማል
ሁሉ አማረኝን ገበያ አታውጣት
ሁሉ አረሰ ማን ይሸምት
ሁሉ የሚገኝ ከእሱ የሚገኝ የለም ያለእርሱ
ሁሉን ለእኔ አትበል
ሁሉን ቢናገሩት ሆድ ባዶ ይቀራል
ሁሉን አውቆ አሳውን እሾህ ከስጋው ለይቶ
ሁሉ ያልፋል እስኪያልፍ ያለፋል
ሁሉም ያልፋል ግን እስኪያልፍ ያለፋል
ሁሉ ያልፋል እውነት ብቻ ይተርፋል
ሁሉም በየዘርህ ቢሉት አክንባሎ ጋጣ ገባ
ሁሉም ያልፋል የሚኮርጅም ቢሆን
ሁሉ አማረሽን ዲስኮ (disco) አታውጧት
ሁሉ አማረሽን ገበያ አታውጧት
ሁል ጊዜ ባሬራ ትበያለሽ ወይ አንዳንድ ጊዜ እንኳ ወጥ አትይሞይ
ሁል ጊዜ ከመደንገጥ አንድ ጊዜ መሸጥ
ሂዳ ጉበት ቢነሷት ታናሽ ታላቅ ስደዱልኝ አለች
ሂዳ ጉበት የነሷት ታናሽ ታላቅ ስደዱልኝ አለች

ሂዳ ጉበት ይነሷታል ታናሽ ታላቅ ላኩልኝ አለች
ሂድ አትበለው እንዲሄድ አድርገው
ሂድ አትበለው እንደሚሄድ አርገው
ሂድ ካገር ኑር ካገር
ህልም ተፈርቶ ሳይተኛ አይታደርም
ህልም አለ ተብሎ ሳይተኛ አይታደርም
ህመሙ ቀርቶ ሞቱን በሰጠኝ
ህመሙ ቀርቶ ሞቱን በተወኝ
ህመሙን የሸሸገ መድሀኒት የለውም
ህመሙን የደበቀ መድሀኒቱም አልታወቀ
ህመሙን የደበቀ መድሀኒት የለውም
ህዳር መሚረሪያ ሰኔ መቃጠሪያ
ህያዋን ለነገስታት ሙታን ለካህናት ይገብራሉ
ህግ ይኖራል ተተክሎ ስርአት ይኖራል ተዛውሮ
ሆሆ ስቄ ልሙት አለ ሰውየው
ሆቴል ቢያብር ገንዘብ ያስገኛል
ሆደ ሰፊ ነገር አሳላፊ
ሆደ ሰፊ ይሻላል ከአኩራፊ
ሆዱ ሲሞላ ፍቅሩ ሌላ ሆዱ ሲጎድል ሰው ያጋድል
ሆዱ ናረት ሙያው ከጅረት
ሆዱን የወደደ ማእረጉን የጠላ
ሆዱን የወደደ ማእረጉን ይጠላል
ሆዱን ያለ ሆዱን ተወጋ
ሆዱ ወድዶ አፉ ክዶ ክፉ ለምዶ
ሆዱ ፈሪ እግሩ ዳተኛ አዳም ሲዋጋ እርሱ ይተኛ
ሆዳም ሰው እንብርት የለውም
ሆዳም ቢሸከም የበላ ይመስለዋል
ሆዳም ቢፈተፍት የጠገበ ይመስለዋል
ሆዳም ፍቅር አያውቅም
ሆዴ በጀርባዬ ቢሆን ገፍቶ ገደል በጣለኝ
ሆዴ ኑር በዘዴ
ሆዴን በልቶኝ ጎኔን ቢያኩኝ አይገባኝ
ሆዴ አታጣላኝ ከዘመዴ
ሆድህና ልጅህ አይጥሉህ
ሆድህን ጎመን ሙላው ጀርባህን ለጠላት አታሳየው
ሆዴ ሆዴ የሚለውን ጌታ ያየዋል አይኔ አይኔ የሚለውን ሰው ያየዋል
ሆድ ሆዴን የምትል ወፍ አለች ምናለች
ሆድ ለማታ በልቶ ለጠዋት
ሆድ ለባሰው ማጭድ አታውሰው
ሆድ ለባሰው ቢላዋ አታውሰው
ሆድ ለተተባሰው ማጭድ አታውሰው
ሆድ ሲሞላ ራስ ባዶ ይቀራል
ሆድ ሲያር ጥርስ ይስቃል
ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ
ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ጠዋት
ሆድ ባዶን ይጠላል
ሆድ ባዶ ይጠላል
ሆድ ከሁዳድ ይሰፋል

ሆድ ካገር ይሰፋል
ሆድ እንዳሳዩት ነው
ሆድና ግንባር አይሸሸጉም
ሆድና ግንባር አይሸሽግም
ሆድን በጎመን ቢደልሉት ጉልበት ዳገት ላይ ይለግማል
ሆድን በጎመን ቢደልሉት ይለግማል ጉልበት
ሆድን በጎመን ቢደልሉት ጉልበት በዳገት ይለግማል
ሆድ ወደ አፍ ክደ ክፉ ለምደ
ሆድ ዘመድ ሳይወድ አፍ እህል ሳይለምድ
ሆድ የኔ ነው ሲሉት ቁርጠት ሆኖ ይገድላል
ሆድ የሸሸገውን ብቅል ያወጣዋል
ሆድ ያበላውን ያመሰገናል
ሆድ ያባውን ብቅል ያወጣዋል

**ለ**

ለሀምሳ ጋን አንድ አሎሎ
ለሀምሳ ጋን አንድ አሎሎ ይበቃል
ለሀብት መትጋት ሰውነትን ያከሳል ገንዘብን ማሰብ እንቅልፍ ይነሳል
ለሀጥአን የወረደ ለጻድቃን ይተርፋል
ለሁሉም ጊዜ አለው
ለሂያጅ የለውም ወዳጅ
ለህልም ምሳሌ የለውም
ለሆዳም ሰው ማብላት ውቅያኖስን ለመደልደል መቃጣት
ለሆዳም በሬ ገለባ ያዝለታል
ለሆዳም በሬ ጭድ ያዝለታል
ለሆዳም በሬ ሻት ተከፈለ
ለሆዳም በቅሎ ጭድ ያዝለታል
ለሆዴ ጠግቤ በልብሴ አንግቤ
ለሆድ ቁርጠት ብላበት ለራስ ምታት ጨህበት
ለላሙ መንጃ ለሽማው መቅደጃ
ለላሙ መንጃ ለሽማው መከንጃ
ለላም ቀንዷ አይከብዳትም
ለላም ከጥጃዋና ከአላቢዋ ማን ይቀርባታል
ለላም የሳር ለምለም
ለላም ጥጃዋ ለአህያ ውርንጭላዋ
ለሌለው ምን ትለው
ለሌባ ቅሌት ልብሱ ነው
ለልደት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ
ለልጅ ሲሉ ይበሉ ለወዳጅ ሲሉ ይጠሉ
ለልጅ ሲሉ ይበሉ ለወገን ሲሉ ይጠሉ
ለልጅ አይስቁለትም ለውሻ አይሮጡለትም
ለልጅ ከሳቁለት ለውሻ ከሮጡለት
ለልጅ ጥርስህን ለዝንብ ቁስልህን
ለልጅ ጥርስህን ለዝንብ ቁስልህን አታሳይ
ለልጅ ጨዋታ ለባለጌ ቧልታ
ለሎሌው ምን ትለው
ለመሀን እምዬ ለአገልጋይ እትዬ ብርቋ ነው
ለመሄድና ለመላወስ አዛዥ ራስ

ለመሄድና ለመመለስ አዛዥ ራስ
ለመሆኑ ሳይሆን እንዴት ይሆናል ቢሆን
ለመሆን ሳይሆን እንዴት ይሆናል ቢሆን
ለመማር ክፍል መግባት ለመኮረጅ ካሮት መብላት
ለመማር ክፍል መግባት ለማለፍ ካሮት መብላት
ለመስማት የፈጠንህ ለመናገርና ለቁጣ የዘገየህ ሁን
ለመስማት የፈጠንህ ለመናገር የዘገየህ ሁን
ለመስራት የሚያፍር መብላት አይደፍርም
ለመስራት ያፈረ ለመብላት ደፈረ
ለመስጠት አለመቸኮል ከሰጡም ወዲያ አለመጸጸት
ለመነኩሴ መልካም ሎሌ
ለመታማት መፍራት
ለመከራ ያለው መነኩሴ ዳዊቱን ሽጦ አህያ ይገዛል
ለመከራ የጣፈው ቢነግድ አይተርፈው
ለሙት የለው መብት
ለሚመለከት ለሚያየው ሞት ቅርብ ነው
ለሚስት ያጎርሷል ለተመታ ይክሷል
ለማረም ማን ብሎት ሲሰራው ግን ግድፈት
ለማን አለው ፈጣሪ አለው ጠጅ ለሌለው ውሀ አለው
ለማን ይፈርዱ ለወደዱ አይደለም ለወለዱ
ለማኝ ቢያብድ ስልቻውን አይጥልም
ለማኝ አያማርጥም ማር አይኮመጥጥም
ለማየት የፈለገ አይኑን ይገልጣል
ለማያቅህ ታጠን ብሎህል ሀሰን
ለማያውቅ ፎገራ ዱሩ ነው
ለማያውቁሽ ታጠኚ
ለማያውቁሽ ታጥበሽ ቅረቢ
ለማይሞት መድሀኒት አለው
ለማይሰጥ ሰው ስጡኝ ማለትን ማን አስተማረው
ለማይሰጥ ሰው ስጡኝን ማን አስተማረው
ለማእበል ወደብ ለነፋስ ገደብ የለውም
ለምሽት መብራት ለመከራ ጊዜ ብልሀት
ለምክንያት ምክንያት አለው
ለምን ላለው ፈጣሪ አለው ጠጅ ለሌለው ውሃ አለው
ለምን ሰርግ ይሄዳል ሰርግ አለ በቤቱ
ለምን ተክዤ አምላክን ይዤ
ለምን ያለው ስልቻውን ጫን ያለው ኮርቻውን
ለምን ያለው ስልቻውን ጫን ያለው ኮርቻውን አያጣም
ለምን ጊዜው ነቀዝሽ
ለምኖ ለማኝ ቀቤን ቀማኝ
ለሞኝ ሰኔ በጋው መስከረም ክረምቱ
ለሞኝ ንገረው ምን ይሰማ ብዬ ለብልህ ንገረው ምን ይሳተው ብዬ
ለሞኝ ንገረው ምን ይሰማ ብዬ ለብልህ ንገረው ምን ይስተው ብዬ
ለሞኝ ከሳቁለት ለቅዘን ከሮጡለት
ለሞኝ ከሳቁለት ለውሻ ከሮጡለት
ለሞኝ ጉድጓድ አያሳዩትም ቤት ነው ብሎ ይገባበታል
ለሞፈር ቀራጭ እርፍ አይታየውም በግላጭ
ለረዥም ሰው ልብ እና ልብስ ያጥረዋል

ለረዥም መንገድ አትሩጥበት ለረዥም ነገር አትቸኩልበት
ለራሱ አያውቅ ነዳይ ቅቤ ለመነ ላዋይ
ለራሱ አያውቅ ጠንቋይ መድሀኒቱ ላዋይ
ለራሱ ጥላ ለእግሩ ከለላ
ለራሱ የማይረባ ለሌላም አይረባ
ለራሱ የማይረባ ለሰውም አይረባ
ለራስ ምታት ጩህበት ለሆድ ቁርጠት ብላበት
ለራሱ አያውቅ ሰው አይጠይቅ
ለራሱ ሲቆርስ አያሳንስ
ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ
ለራስ ቢያወሩ ለቅንቅን ይዘሩ
ለራስ ቢያወሩ ለቅንቅን ይዘሩ አለች ዶሮ
ለራስ ከበጁ አይታጡ ደጁ
ለራበው ሰው ቆሎ ለቁልቁለት በቅሎ
ለራበው ባዶ መሶብ ማቅረብ
ለራት የማይተርፍ ዳረጎት
ለርስት ሴቶች ስንኳ  ይሞቱበታል
ለሰማይ ምሰሶ የለው ለባእድ ስር የለው
ለሰለባ የመጣ ልብስ ቢጥሉለት አይመለስ
ለሰለባ የመጣ ልብስ ቢጥሉለት አይመለስም
ለሰበበኛ ቂጥ መረቅ አታብዛበት
ለሰባቂ ጆሮህን አትስጠው
ለሰው ልጅ ሲያበሉ ለውሻ ልጅ ያብሉ
ለሰው ልጅ ከሚያበሉ ለውሻ ልጅ ያብሉ
ለሰው ልጅ ከማብላት ለውሻ ልጅ ማብላት
ለሰው ልጅ እውቀት ለጠጣ ብልጠት
ለሰው ሞት አነሰው
ለሰው ሞት አነሰው ውሻውንስ ፊሴ መለሰው አለች ቀበሮ
ለሰው ቢነግሩት ለሰው
ለሰው ቢናገሩ መልሶ ለሰው ጫር ጫር አድርጌ አፈር ላልብሰው
ለሰው ብሎ መሞት አምላክነት ያሻል
ለሰው ብሎ ሲያማ ለኔ ብለህ ስማ
ለሰው ብትል ትጠፋለህ ለእግዜር ብትል ትለማለህ
ለሰው እንግዳ ላገሩ ባዳ
ለሰው እንዴት F አነሰው
ለሰው ከበሬታው ሰው ለወጥ ማጣፈጫው ጨው
ለሰው ጠላቱ ይወጣል ከቤቱ
ለሰው የማይል ሰው ሞትም ሲያንሰው
ለሰው ብሎ ሲያማ ለእኔ ብለህ ስማ
ለሴትና ለጉም አይዘነጉም
ለሰይጣን አትስጠው ስልጣን
ለእሳት ውሀ ለጸጉር ቡሀ
ለሴት ልጅ እስከአርባ ቀን ሞቷን ከዚያ ወዲያ ሀብቷን
ለሴት ምስጢር ማውራት በወንፊት መቅዳት
ለሴት ምክር አይገባትም
ለሴትና ለጉም አይዘነጉም
ለሴት ጠላ ለፈረስ ቆላ
ለስሟ መጠሪያ ቁና ሰፋች

ለስሱ ፍትፍት አሳይቶ እበት ያጎርሷል
ለሸማኔ ማገጃ ስለት ማረጃ
ለሹመት ካልመከሩለት ለጥርስ ካልነከሩለት
ለሹመት ካልመከሩለት ለጥርስ ካልከደኑለት
ለሹመት ያደለው የለማኝ አለቃ ይሆናል
ለሺ ፍልጥ ማሰሪያው ልጥ
ለቀላል ምስጢር መንገር በቀዳዳ ጤፍ መቋጠር
ለቀላል ሰው ምስጢር መንገር በቀዳዳ ጤፍ መቋጠር
ለቀላል ሰው ምስጢር መንገር በቀዳዳ አቁማዳ ጤፍ መቋጠር
ለቀማኛ የለውም እጅ ለበቅሎ የለውም ልጅ
ለቀበጠች አማት ሲሶ በትር አላት
ለቀባሪው አረዱት
ለቀን ቀጠሮ ለሴት ወይዘሮ
ለቀንዳም በሬ ቤት አትከልክለው ቀንዱ ይከልክለው
ለቀንዳም በሬ ቤት አትከልክለው ቀንዱ ይከለክለዋል
ለቁንጫ ለምጽ ያወጣል
ለቁንጫ መላላጫ
ለቂጡ ጨርቅ የለው ቀንጆ ያባብላል
ለቅልብልብ አማት ሲሶ በትር አላት
ለቅሶ ሳለ ከቤት ለቅሶ ይሄዳል ጎረቤት
ለቅሶ ሳለ ከቤት ይሄዳል ጎረቤት
ለቅናት የለውም ጥናት
ለቅዘን እግር አንስተውለት
ለቅዘን እግር አንስተውለት ለውሻ ሮጠውለት
ለቆመ ሰማይ ቅርቡ ነው
ለቆማጣ አንድ ጣት ብርቁ ናት
ለበራ ወለባ ለውሻ ገለባ
ለበጋ ጥጃ ውስ አነሰው ወይ
ለበግ ደጋ ለምቾት አልጋ
ለቡናሽ ቁርስ የለሽ ለነገርሽ ለዛ የለሽ
ለባለጌ ገድሉ ውርደቱ
ለቤት ሳማ ለውጭ ቁጤማ
ለቤት ሳንቃ ለሰው አለቃ
ለቤት ሳንቃ ለነገር ጠበቃ
ለቤት ባላ ለችግር ነጠላ
ለብልህ ንገረው ምን ይስተው ብዬ ለሞኝ ንገረው ምን ይገባው ብዬ
ለብልህ አይነግሩ  ለድመት አያበሩ
ለብልህ አይነግሩ  ላንበሳ አይመትሩ
ለብልህ አይነግሩ ለንጉስ አይመክሩ
ለብልህ አይነግሩም ለንጉስ አይመክሩም
ለብልህ አይነግሩ ካልጠየቀ በስተቀር
ለተማሪ ቆሎ ለወታደር በቅሎ
ለተሟጋች መዘዘኛ የዳኛ ትእግስተኛ
ለተረታው ያበደረ እሳት ጨመረ
ለተራበ ግብር ለተበደለ ነገር
ለተራበ በግብር ለተበደለ በነገር
ለተራበ ቂጣ ለተጠማ ዋንጫ
ለተሸሸገ ምግብ የተሸሸገ ሆድ አይጠፋለትም

ለተሾመ ይሟገቱለታል ለተሻረ ይመሰክሩበታል
ለተሾመው ይመሰክሩለታል ለተሻረው ይመሰክሩበታል
ለተሾመ ይመሰክሩለታል ለተሻረ ይመሰክሩበታል
ለተቀማጭ ሰማይ ቅርቡ ነው
ለተባባሰው ማጭድ አታውሰው
ለተንኮለኛ ሲሉ ይሰበሰባሉ ለቅን ይፈርዳሉ
ለተወገረ የማያዝን እንብርት የለውም
ለትኋን ልጓም ማጉረስ ላፈኛ ሰው መመለስ
ለትኋን ልጓም ማጉረስ ላፈኛ ሰው መመለስ አይቻልም
ለቸኮለ ሰው ዋንጫ አስጨብጠው
ለችግር የፈጠረው ቢነግድ አይተርፈው
ለነገረኛ ሰው ጀርባህን ስጠው
ለነገረኛ ነገር ተውለት ለሆዳም እህል አቅርብለት
ለኔ ነግ በኔ
ለንጉስ የማይገዛ ለእግዚአብሄር አይገዛ
ለንጉስ ያልረዳ ከባህር የማይቀዳ
ለንጉስ ያልረዳ ከባህር ያልቀዳ
ለንፉግ ሰው የገበያ መንገድ ይጠበዋል
ለንፉግ ሰው የገበያ መንገድ ይጠበው
ለአህያ ማር አይጥማትም
ለአምላክ ልንገረው ለማያስቀረው
ለአበባ የለው ገለባ
ለአቤቱታ የለው ይሉኝታ
ለአንበሳ አታበድር ካበደርክ አትጠይቅ
ለአንተ ያለውን እንጀራ ይሻግታል እንጂ ማንም አይበላውም
ለአኩራፊ ምሳው እራት ይሆነዋል
ለአይነ ስውር መስተዋት
ለአይንና ለወዳጅ ጥቂት ይበቃል
ለአይን የሚከፋ ለአፍንጫ ይከረፋ
ለአዋጅ ነጋሪት ለጥጥ ልቃቂት
ለአገሩ እንግዳ ለሰው ባዳ
ለአፊ ግም አፍንጫ ድፍን ያዝለታል
ለአፉ ለከት የለውም
ለአፍታ የለውም ፋታ
ለአፍ ዳገት የለውም
ለእሳት እንጨት ካልነሱት አይጠፋም
ለእሳት እንጨት ካልነፈጉት አይጠፋም
ለእሳት ውሀ ለጸጉር ቡሀ
ለእሳት ፍላት ለጮማ ሰባት
ለእበጥ ፍላት ለእንጨት እሳት
ለእባብ እግር የለው ለሞኝ መላ የለው
ለእብለት ስር የለው ለእባብ እግር የለው
ለእብለት ስር የለውም ለእባብ እግር የለውም
ለእበጥ ፍላት ለእንጨት እሳት
ለእኔ እናት ምን ደላት ያም አፈር ያም ድንጋይ ጫነባት
ለእውር ዝማሜ ለመላጣ ጋሜ
ለእውር ዝማሜ ለመላጣ ጋሜ አይስማማውም
ለእጅ ርቆ ለአይን ጠልቆ

ለእግሩ የተጠየፈ ለቂጡ አተረፈ
ለእግር የፈሩት ለቂጥ ይተርፋል
ለእግዚአብሄር የቀነቀነ ለጽድቅ ለጌታ የቀነቀነ ለወርቅ
ለእውነት ማማ ለውሸት ጨለማ
ለከለላ ጥላ ቢርብህ ብላ
ለከሳሽ የለው መላሽ
ለካህን ጥምቀት ለገበሬ ግንቦት
ለክፋት ያደለው አሳዳጊ የበደለው
ለኮ መሳቢያ ወፍጮ ማላሚያ
ለወሬ ሞትሁ
ለወሬ ሞትሁ ለእህል ስለፍኩ
ለወሬ ወዳጁ ወሬ ለመነኩሴ ጥሬ
ለወሬ የለው ፍሬ
ለወሬ የለው ፍሬ ለአበባ የለው ገለባ
ለወሬ የቸኮለ እናቱን በመንገድ ይረዳል
ለወርቅ ያሉት አንገት ላሽክት
ለወታደር ሰፊ መንደር
ለወታደር ሰፊ መንደር ለወዲላ መልካም ዱላ
ለወይዘሮ መልካም ዶሮ
ለወደላ መልካም ዱላ
ለወዳጅ የማር ወለላ ለጠላት አሜኬላ
ለወዳጅና ለአይን ትንሽ ይበቃዋል
ለወጡም እዘኑለት ከእንጀራውም ጉረሱለት
ለወጡ ጊዜስ ከደረቁም
ለወጡም እዘኑለት ከደረቁም ብሉለት
ለወጥ የሚሻል ቅልውጥ
ለዋንጫ ቡሽ ለውሀ ጉሽ የለውም
ለዋስ አፍ የለው ለጉንዳን ደም የለው
ለውሻ ምሳ የለው ራት ብቻ
ለውሻ ሞት ፊት አይነጩለትም
ለውሻዬ ያልሁትን ልጄ ቢበላብኝ አልወድም
ለውሽማ ሞት ፊት አይነጩለትም
ለውጡኝ ባይ የሚሻለውን አውቆ
ለዘመዴ ያዝናል ሆዴ
ለዚህ ሆዴ ጠላኝ ዘመዴ
ለዝናም ጌታ ውሀ ነሱ
ለዝናም ጌታ ውሀ ነሱት
ለዝንብ ከትላንት ወዲያም ድሮ ነው
ለይቶ እንደፈፋ አንጓሎ እንዳረፋ
ለይቶት አባ ንጉሷ
ለደህና ሰው ዋጋ አነሰው
ለደህና ሰው ውሸት ለጅብ እሸት
ለደብተራ መቋሚያና ጭራ
ለደደብ ማስረዳት ድንጋይ ቅቤ መቀባት
ለደግ ንጉስ እለት እለት ማልቀስ
ለዳርቻው ሲሳሱ መካከሉን ተነሱ
ለዳርቻው ሲሳሱ ከነመሀሉም ተነሱ
ለዳባ ለባሽ ነገርህን አታበላሽ

ለዳኛ አመልክት እንዲሆን መሰረት
ለዳኛ የነገሩት በርጥብ ያቃጠሉት
ለዳኛ ዳኛ አለው ለአንበሳ ተኩላ አለው
ለድሀ ማን ሰጠው ውሀ
ለድህነት የፈጠረው ቢነግድ አይተርፈው
ለድህነት የፈጠረው ቢነግድ አያተርፍም
ለድሪ ያሉት አንገት ለአሸንክታብ
ለድሪ ያሉት አንገት ላሽክት
ለድካም የጣፈኝ ብነግድ አይተርፈኝ
ለዶሮ ሲነገሩ ምጥማጥ ይሰማል
ለጆሮ ጥርስ ለሆዳም ስስ
ለገላጋይ ደም የለውም
ለገበሬ መልካም በሬ
ለገቢህ ተንገብገብ
ለገና ጨዋታ አይቆጡም ጌታ
ለገደለ ጎፈሬ ላረጋገጠ ወሬ
ለገዳም የረዳ አይጎዳ
ለጉንዳን ደም የለው ለዝንብ ቤት የለው
ለጉንዳን ደም የለው ለገንዘብ ቤት የለው
ለጋስ ቢለግስ አበደረ እንጂ አልሰጠም
ለጋስ ቢለግስ አበደረ እንጂ እንዲያው አልሰጠም
ለእግዜር የተቀናቀነ ጽድቅ ለንጉስ የተቀናቀነ ወርቅ
ለጎበዝ ስጠው ሰንጋ ፈረስ
ለጠላትህ እንደ ዳቦ እስኪገምጥህ አትመቸው
ለጠቢብ አንድ ቃል ይበቃል
ለጠጪ ሰው የመጠጥ ወሬ አውራው
ለጥልና ለዳኛ ያለው ገንዘብ አፋፍ ይቆያል
ለጥርጣሬ ምንጣሬ
ለጥቅም ሲታጠቁ ከጎን ይጠንቀቁ
ለጥቅምት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ
ለውጠኝ ባይ የሚሻለውን አውቆ
ለጨለማ ጊዜ መብራት ለመከራ ጊዜ ብልሀት
ለጨቅጫቃ ሰው ከማበደር ይሻላል በጄ ማደር
ለጭስኛ መሬት ለሳር ቤት ክብሪት
ለጾም ግድፈት ለበአል ሽረት
ለጾም ግድፈት ለባል ሽረት
ለፈረስህ አንገት ለጋሻህ እንብርት
ለፈሪና ለንፉግ እያደር ይቆጨዋል
ለፈሪ ሜዳ አይነሱም
ለፈሪ ምድር አይበቃውም
ለፈሪ ይበቃል ፍርፋሪ
ለፈሪ ስጠው ፍርፋሪ
ለፋሲካ የተዳረች ሁል ጊዜ የፋሲካ ይመስላታል
ለፍቅር ብተተኛ ለጠብ አረገዘች
ለፍቅር ብተኛት ለጠብ አረገዘች
ለፍቅር የለውም ድውር
ለፍየል ቆላ ለሙክት ባቄላ
ለፍየል ህመም በሬ ማረድ

ለፍየል ስም አውጣ ቢለው ሞት አይደርስ አለው
ሊበሉ የፈለጉትን አሞራ ስሙን ይሉታል ጅግራ
ሊበሉዋት ያሰብዋትን አሞራ ይሏታል ጂግራ
ሊወጋ የመጣ ጌታዬ ቢሉት አይመለስም
ሊያልፍ ውሀ አደረገኝ ድሀ
ሊያስቡት አይገድም
ሊጣላ የመጣ ሰብብ አያጣም
ላሀያ ፈስ አፍንጫ አይዙለትም
ላሀያ ማር አይጥማት
ላሀያ ማር አይጥመውም
ላሀያ ያልከበደው ለመጫኛ ከበደው
ላለው ቅንጭብ ያረግዳል
ላለው ይጨመርለታል
ላለፈ አይጸጸቱም ለሚመጣው አይበለጡም
ላለፈው አይጸጸቱም ለሚመጣው አይበለጡም
ላለፈው ክረምት ቤት አይሰራለትም
ላለፈው ክረምት ቤት አይሰራም
ላለፈው ክረምት ውሀ ማቆር አይቻልም
ላለፈው ጸሎት ከንቱ ጩኸት
ላሊበላ ሄደሽ ከሀንጻው ብትሰፍሪ አይገኝም ጽድቅ አለ ባህሪ
ላሊበላ አደራውን አይበላ
ላሊበላ የቃሉን አይበላ
ላሊበላን ካላጠገቡት ይጨሀል ሎሌም ካልሰጡት ይከዳል
ላላየ ልጅ ዳቦ ፍሪዳው
ላላየው የሚያስገርም ለሰማው የሚያስደንቅ
ላላዩ ልጅ ዳቦ ፍሪዳው
ላላወቀው ፎገራ ዱር ነው
ላመት ልብስ ለአለት ጉርስ
ላሜ ቦራ የልጆቼን ነገር አደራ
ላም ሲበዘበዝ ጭራዋን ያዝ
ላም ቀንዷ አይከብዳትም
ላም በረቱን የሰው ልጅ አባቱን አይረሳም
ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ
ላም አለኝ በሰማይ ወተትዋንም አላይ
ላም አለኝ በሰማይ ገመድ እፈልጋለሁ
ላም እሳት ወለደች እንዳትልሰው ፈጃት እንዳትተወውም ልጅ ሆነባት
ላም ከወንዝ ልጅ ከቦዝ
ላንተ መምከር ጥቁር ድንጋይ ላይ ውሀ ማፍሰስ ነው
ላንቺ ቁምነገርሽ በሶብላ ወጥሽ
ላንቺ ብርቅሽ በሶቢላ ወጥሽ
ላያዘልቅ ጸሎት ለቅሰፈት
ላይቀርልኝ እዳ በጊዜ ልሰናዳ
ሌባ ላመሉ ቅድመ እውቅና አገኘ
ሌባ ላመሉ ንግድ ይላል
ሌባ ላመሉ ዳቦ ይልሳል
ሌባ እናት ልጇን አታምንም
ሌባን ሌባ ቢሰርቀው እንዴት ይደንቀው
ልባም ሴት ለባልዋ ዘውድ ናት

ልብስህን በውሀ ገንዘብህን በድሀ
ልብ ካላየ አይን አያይም
ልብ ካላየ አይን አይፈርድም
ልትደርቅ የደረሰች ምንጭ ጭልጭል ትላለች
ልትሰራ ሂዳ ተላጭታ መጣች
ልጅም ከሆነ ይገፋል ድንችም ከሆነ ይጠፋል
ልጅ ለናቷ ምጥ አስተማረች
ልጅ ምን ቢሮጥ አባቱን አይቀድምም
ልጅ ሳለህ አጊጥ ሞል ሳይዘጋ ሸምት
ልጅ ቢያኮርፍ ቁርሱ እራት ይሆናል
ልጅና እሳት ባለቤቱ ያጠፋዋል
ልጅን አሳዳጊ እሳትን ውሀ ያጠፋዋል
ልጅና ወረቀት የያዘውን አይለቅም
ልጅና ጠጣ ውሀ ይጠጣ
ልጅ ያቦካው ለእራት አይሆንም
ልጅ ይወለዳል ከቦዝ ላም ይገዛል ከወንዝ
ልጅ ደረሰ ቤት ፈረሰ
ልግመኛ ባሪያ መጇን ትደብቃለች
ልግመኛ አጋዥ ብታገኝ መጅ ደበቀች
ልግመኛን መምከር ውሀ በወንፊት ማኖር
ልፋት ቢያምርህ መሬት ግዛ ችግር ቢያምርህ ልጅ አብዛ
ልፋ ያለው ሊስትሮ እግር ስር ይውላል
ልፋ ያለው ምረጡኝ አለ
ልፋ ያለው በህልሙ ሲሸከም ያድራል
ልፋ ያለው በሬ ቀዳው ለከበሮ
ልፋ ያለው ቢን ላደንን ይፈልጋል
ልፋ ያለው አንድ እንጨት ያስራል
ሎሌ ለስህተት ጌታ ለምህረት
ሎሌ ሲከብር ጌታውን ይከሳል ሙክት ሲሰባ ሾተሉን ይልሳል
ሎሌ ሲከብር ጌታውን ይከሳል ሙክት ሲሰባ ሾተል ይልሳል
ሎሌ ያገለገለውን ይቆጥራል ጌታ ያስቀየመውን ያስባል
ሎሌና አሞሌ ካዘዙት ይውላል
ሎሚ ካልመጠጡት እምቧይ ነው
ሎሚ ካልመጠጡት እምቧይ ዳቦ ካልገመጡት ድንጋይ
ሎሚና ትርንጎ ሞልቶልህ ባገር እንቧይ ታሸታለህ የድሀ ነገር
ሎሚና ትርንጎ ሞልቶ ባገር እንቧይ ያሸታል አወይ የድሀ ነገር
ሎሚ ቢያብብ ቢኖርና መልካም ሽታ ቢሰጥ መኮምጠጡን አይተውም

## መ

መሄድ በጋ ነው መቀመጥ ክረምት ነው
መሄጃ የሌለው መውጫውን ያበስራል
መልከ ጥፉ በስም ይደግፉ
መልከ ጥፏ ቀንጆዋን አስናቀች
መልካም ባል መጥፎ ሴት ይገራል
መልካም ሴት ለባሏ ዘውድ ናት
መልካም ስም ከመቃብር በላይ ይውላል
መልካም ስም ከመቃብር በላይ ይቆማል

መልካም አባት ለልጆቹ እጁን ኪሱ ይከታል
መልካም ባል መጥፎ ሴት ይገራል
መልኳ ባያምር አመሏ ይመር
መልክ ታጥቦ አይጠጣ ወይ አይበላ
መልክ ስጠኝ እንጂ ሙያ ከጎረቤቴ እማራለሁ
መመራመር ያገባል ከባህር
መሞት የፈለገ ግልገል ቀበሮ ቤት ሄዶ ይጨፍራል
መራጭ ይወድቃል ከምራጭ
መቀመጥ በአልጋ ታላቅ ደጋ
መቅረቢን ሳታውቅ እጇን ታጠበች
ሙብላቷን ሳታውቅ እጇን ታጠበች
መተው ነገሬን ከተተው
መቼ መጣሽ ሙሽራ መቸ ቀረጠምሽ ሽንብራ
መካር የሌለው ንጉስ አለ አንድ አመት አይነግስ
መንገድ ካገር ልጅ ምክር ከጨዋ ልጅ
መወለድ ቋንቋ ነው
ሚስቱ ክፉ ባቄላ እራቱ ብሳና እንጨቱ ሀዘን ነው እቤቱ
ሚስቱ ደግ ስንዴ እራቱ ወይራ እንጨቱ ደስታ ነው እቤቱ
ሚስቱን ጠልቶ ካማቱ ልጁን ከሶ ካባቱ
ሚስቱን ገድሎ አማቱ ቤት ተሸሸገ
ሚስት ባታብል ባሏን ትወልዳለች
ሚስት ከፈቷት ባዳ ማሽላ ከተቀረጠ አገዳ
ሚስትህ አመዳም ጎራዴህ ጎመዳም
ሚስትህ አረገዘች ወይ ቢለው ማንን ወንድ ብላ አለው
ሚስትህን ስደድ በሬህን እረድ ይላል የባለጌ ዘመድ
ሚስትና ዳዊት ከብብት
ሚስት ፈትቶ ካማት መቀለብ በእንፋቅቅ መሄድ
ሙቅ ውሀና የሰው ገንዘብ አይጠቅምም
ሚስጥርህን ለባእድ ለምን አዋየኸው ወንፊት ወሀ ይዞ የት ሲደርስ አየኸው
ማሞ ሌላ መታወቂያው ሌላ
ማር በበላሁበት በጣፈጠው አፌ ጎመን ጎረስኩበት አይ አለማረፌ
ማሽላ ሲያር ይስቃል
ማሽላ እየፈካ ያራል
ማቅ ይሞቃል ጋቢ ይደምቃል ገቢውን ባለቤት ያውቃል
ማን ሙሽራ ቢልሽ ትኳያለሽ
ማን ያውራ የነበረ ማን ያርዳ የቀበረ
ማን ያውራ የነበረ ማን ይጨፍር የሰከረ
ማእድ ጠፋና አንድ ላይ በላን
ማግባቱ ቀርቶብኝ በታጨሁ
ማጣት ከሰማይ ይርቃል
ምላጭ ቢያብጥ በምን ይበጡ ውሀ ቢያንቅ በምን ይውጡ
ምን ያመጣ ድሀ ምን ያገሳ ውሀ
ምን ቢያርሱ እንደጎመን አይጎርሱ
ምንም ቢጠም መንገድ ምንም ቢከፋ ዘመድ
ምን ቢፋቀሩ አብረው አይቀበሩ
ምከረው ምከረው እምቢ ሲል መከራ ይምከረው
ምከረው ምከረው እምቢ ካለ መከራ ይምከረው
ምከረው ምከረው እንቢ ካለህ መከራ ይምከረው

ምከረው ምከረው እንቢ ያለህን ሰው መከራ ይምከረው
ሞት በጥር በነሀሴ መቃብር
ሞት ቢዘገይ ሲኦል ስለሞላ ነው
ሞት ቢዘገይ ነው የምሄደው
ሞት ቢዘገይ የቀረ ይመስላል
ሞት የሰጠው ቀባሪ አያሳጣውም
ሞኝ ሲስቁበት የሳቁለት ይመስለዋል
ሞኝ እከኩን እያየች ስትስቅበት ወደደችኝ ብሎ ይፈነድቃል
ሞኝና ወረቀት ሊደራደሩ ነው
ሞኝና ወረቅት ኢንተርኔትን ናቁ
ሞኝና ወረቅት የያዘውን አይለቅም
ሞኝ ውሀ ሲወስደው ይስቃል
ሞኝ ዘመድ ከልጅህ እኩል አድርገኝ ይላል

ረ
ሬሳ በምኑ ይከበራል በዝምታው
ራስ ሳይጠና ጉተና
ራስ ተላጭቶ ወለባ ልባልባ ታጥቆ አዛባ

ሰ
ሰለሞን ሳባን ውሀ ባያስጠማት ኖሮ የሱ ጥም ባልበረደ ነበር
ሰውን ፈላጊ በምርጫ ይሸነፋል
ሰማይ አትረስ ንጉስ አትክሰስ
ሰርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ
ሰባት አመት ባይማሩ ሰባ አመት ይደንቁሩ
ሰነፍ ሴት ያገባ በሬው በሰኔ ገደል የገባ
ሰነፍ በዓል ያበዛል
ሰነፍ ቢመክሩት ውሀ ቢወቅጡት
ሰነፍ ገበሬ በሰኔ ይሞታል
ሰነፍ ገበሬ ክረምት በጋው በጋው ክረምቱ
ሰኔ መቃጠሪያ ህዳር መገናኛ
ሰኔ ሰላሳ የለውም ካሳ
ሰኔና ሰኞ
ሰኔን በዘራዘር ሃምሌን በጎመን ዘር
ሰካራም ቤት አይሰራም
ሰካራም ዋስ አያጣም
ሰው መሳይ በሸንጎ
ሰው በዋለበት ውሀ በወረደበት
ሰው ቢማር ቄስ እንጂ መላክ አይሆንም
ሰው ባለው ይሰለፋል
ሰውን ማመን ቀብድ ተቀብሎ ነው
ሰውን ሰው ናቀው የራሱን ሳያውቀው
ሰውን ሰው ያሰኘው እቁብ ነው
ሰውን ሲወዱ ከነንፍጡ እና ልጋጉ
ሰውን ሲያማ ለእኔ ብለህ ስማ
ሰው አለብልሀቱ ገደል መግባቱ አለጉልበቱ ውሀ መግባቱ
ሰው አለወንዙ ብዙ ነው መዘዙ
ሰው እንደ እውቀቱ ነው

ሰው ከሞተ የለ ንስሀ ከፈሰሰ አይታፈስ ውሀ
ሰውየው ውሀ ሲወስደው እኔም ወደ ቆላ እወርዳለሁ ብዬ ነበር አለ
ሰው ያመነ ውሀ የዘገነ
ሰው ያስገድላል አባይ ውሀ ያስጨሀል ድንጋይ
ሰው ያለሰራው የተሰረቀ አህያ ይነዳል
ሰው ጥራ ቢሉት መራራን ጠራት
ሰው ጥራ ቢሉት እራሱ መጣ
ሰዶ ማሳደድ ቢሻህ ዶሮህን ለቆቅ ለውጥ
ሰዶ ማሳደድ ካማረህ ዶሮህን በቆቅ ለውጥ
ሲሉ ሰምታ ዶሮ ሞተች ዋና ገብታ
ሲመክሩት ያልሰማ ሲያጨሉት ይሰማ
ሲመች ያማት ተዝካር ይወጣል ሳይመች ያባት ይቀራል
ሲሞቱ ብታይ አንቀላፉች
ሲሮጡ የታጠቁት ሲሮጡ ይፈታል
ሲሮጡ የፈቱት ሲቀመጡ ለማስተካከል ቀላል ነው
ሲሮጥ የመጣን አህያ አጥብቀህ ጫነው
ሲሰርቀኝ ያየሁትን ቢጨምርልኝ አላምነውም
ሲስሟት ትታ ሲሰቧት
ሲስሟት እንቢ ብላ ሲጎትቷት
ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል
ሲበሉ አድርሰኝ ሲጣሉ አርቀኝ
ሲበሉ አድርሱኝ ሲጣሉ መልሱኝ
ሲቃ የቀሰቀሰው ነቅቶ አይተኛም
ሲታጠቡ እስከ ክንድ ሲታረቁ ከሆድ
ሲችኩሉ የታጠቁት ለወሲብ አይመችም
ሲችግር ጤፍ ብድር
ሲያውቀኝ ናቀኝ
ሲያዩት ያላማረ ሲበሉት ያቅራል
ሲያደርጉ አይታ ዶሮም ጡት መያዣ ገዛች
ሲጠሩት ወዴት ሲልኩት አቤት
ሲጠባ ያደገ ጥጃ ቢይዙት ያጓራል
ሲገደገድ ያልበጀው ሲወቀር እሳት ፈጀው
ሳል ይዞ ስርቆት ቂም ይዞ ጸሎት
ሳትወልድ ብላ
ሳያሽ የበላ ዝንጀሮ ሲስል ያድራል
ሳያውቁ የቀረጡት አበባ የፈለጉት ቀን ይደርቃል
ሳያጣሩ ወሬ ሳይገሉ ጎፈሬ
ሳይርቅ በቅርቡ ሳይደርቅ በቅርቡ
ሳይሰሙ ወሬ ሳይገሉ ጎፈሬ
ሳይቃጠል በቅጠል
ሳይተርፋት አበድራ ሳትቀበል ሞተች
ሳይችግር ጤፍ ብድር
ሳይችግር ጤፍ ብድር መከበር በከንፈር
ሳይችግር ጤፍ ብድር በስተርጅና ሙሽርና
ሳይከካ ተቦካ
ሳይደግስ አይጣላም
ሳይጠሩት አቤት የሰይጣን ጎረቤት
ሳይጠሩት ወይ ባይ ሳይሰጡት ተቀባይ

ሴቱ ሲበዛ ጎመን ጠነዛ
ሴትና ዶሮ ዱር ከሄዱ ቤታቸውን ይክዳሉ
ሴት ከወንድ እህል ከሆድ
ሴት ለቤት ወፍጮ ለዱቄት
ሴትና መሬት የማይችሉት የለም
ሴት ማገዶ ሲቸግራት ምሰሶ ትነቅላለች
ሴት ሲበዛ ልማት ይፋጠናል
ሴት ሲበዛ ወንዶች ይፈራሉ
ሴት በማጀት ወንድ በችሎት
ሴት በጳጳስ ኳደሬ በንጉስ
ሴት ብታውቅ በወንድ ያልቅ
ሴት ሲያፏጩላት ያረሱላት ይመስላታል
ሴት ታውቅ በወንድ ያልቅ
ሴት አማት የመረዘው ኮሶ ያነዘዘው
ሴት አግብተው ሴት ቢወልዱ የት አለ ንግዱ
ሴት ከወንድ እህል ከሆድ
ሴት ከጠላች በቅሎ ከበላች አመል አወጣች
ሴት ካላበለች ባልዋን ትወልዳለች
ሴት ካልወለደች ቷንጣ አትጠብስም
ሴት ካልዋሸች ባልዋን ትወዳለች
ሴትና መሬት የማይችሉት የለም
ሴት የወደደ ጉም የዘገነ
ሴት ያመጣው ጠብ አይበርድም
ሴት ይወዷል ማጀት ያንጎዳጉዷል
ሴትና ቄስ ቀስ
ሴትና በቅሎ እንደገሪዋ ነው
ሴትና አህያ በዱላ
ሴትና አህያ ዱላ ይወዳል
ሴትና ድመት ወደ ሞቀበት
ሴትና ዶሮ ሳይጣላ አይውልም
ሴትና ድስት ወደ ማጀት
ሴትና ዶሮ ሳያብድ አይውልም
ሴትና ፈረስ እንደኩሬ ውሀ እያደር ማነስ
ሴትና ፈረስ የሰጡትን ይቀምስ
ሴትን ያመነ ጉም የዘገነ
ሴት የላከው ምልክቱን አይረሳም
ሴት የላከው ሞት አስፈራራው
ሴት የላከው ሞት አይፈራም
ሴት የላከው በር አያንኳኳም
ሴት የላከው አልቃይዳን አይፈራም
ሴት የላከው ጅብ አይፈራም
ሴት የላከው ፓርላማ ይገባል
ሴትየዋ እንደፈራሁት ተቀደደብኝ አለች
ስለ ጨሰ አይነድም ስለዳመነ አይዘንብም
ስልቻ ቀልቀሎ ቀልቀሎም ስልቻ
ስምህ ማነው ላገር አይመች ማን አወጣልህ ጎረቤቶች
ስምሽ ማነው ሲኗት ቂጤ ትልቅ ነው አለች
ስምን መላክ ያወጣዋል

ስም ከመቃብር በላይ ይቆማል
ስም ያለው ሞኝ ነው
ስም ይወጣል ከቤት ይሄዳል ጎረቤት
ስም ይወጣል ከቤት ይከተላል ጎረቤት
ስራ ለሰሪው ምርጫ ለመራጭ
ስራ ለሰሪው እሾህ ላጣሪው
ስራ ከመፍታት ምርጫ መወዳደር
ስራ ከምፈታ ልጄን ላፋታ
ስራ ያጣ መለኩሴ አደገኛ ቦዘኔ ተባለ
ስራ ያጣ መነኩሴ ቆቡን ቀዶ ይሰፋል
ስራ ያጣ መነኩሴ "አደገኛ ቦዘኔ" ተብሎ ታሰረ
ስራ ያጣ መነኩሴ የምርጫ ቅስቀሳ ጀመረ
ስራ ያጣ ቄስ ቆቡን ቀዶ ይሰፋል
ስብ ሊያርዱ ጉፋያ ይነዱ
ስትወልድ የምትበላውን በርግዝናዋ ጨረሰችው
ስትግደረደሪ ጾምሽን እንዳታድሪ
ስደትና አግዳሚ ሁሉንም እኩል ያረጋል
ስጋ ቁጠር ቢሉት ጣፊያ አንድ አለ
ስጋው ያሳማ እንኳን ለበላው ለሰማው ገማ
ስጋው ያሳማ ከበላው የሰማው ገማ
ሶስቴ ከመፍሳት አንዴ መቅዘን

## ሸ

ሸማ ለብሶ ስልቻ በቅሎ ጭኖ ለብቻ
ሸማ ማዋስ ለባላገር በቅሎ ማዋስ ለወታደር
ሸማ በውሀ ሰው በንስሀ
ሸማን በውሀ ሰውነትን በንስሀ
ሸማ በየፈርጁ ይለበሳል
ሸማና ምስጥ ወደ ውስጥ
ሸማኔ በመኑ ጠይብ በከሰሉ
ሸማኔ በድሩ ጠይብ በመንደሩ
ሸማኔ ድውሩን ባለስልጣን ክብሩን
ሸማን ጠምዞ ያሰጧል እህልን አላምጦ ይበኗል
ሸምበቆ በመርዘሙ አይሆንም ምሰሶ
ሸምበቆ በመርዘሙ ምሰሶ አይሆንም
ሽርሙጣ ስታረጅ አቃጣሪ ትሆናለች
ሽርሙጣን የወደደ ልብሱን ጥሎ አበደ
ሽርሙጣን የወደደ ልብሱን ጥሎ ያበደ
ሸኒና ጥላ ቤት አይገባም
ሸኒ ቤት አያደርስም
ሸኝ ቤት አይገባም
ሽክላ ቢጥሉት ገለባ
ሹመት ላወቀው ይከብደዋል ላላወቀው ያሳብደዋል
ሹመት ሲገኝ ዘመድ አይገድም
ሹመት ሺህ ሞት
ሹመት በተርታ ስጋ በገበታ
ሹመት የለመደ ወንዝ ዳር ይወርዳል

ሹመትና ቁመት ከልኩ አያልፍም
ሹመትና ቁመት አይገኝም በምኞት
ሹም ለመነ አዘዘ
ሹም ለሹም ያወርሳል ጉም ተራራ ያለብሳል
ሹም ለሹም ይጎራረሳል ድሀ ለድሀ ይለቃቀሳል
ሹም መክሰስ ወጀድ ማረስ አይቸግርም
ሹም ሲቆጣ ማር ይዞ እደጂ ደስ ሲለው ማር ይዞ እደጂ
ሹም ቢሞት ሀምሳ የሹም ልጅ ቢሞት መቶ ሀምሳ
ሹም ቢሞት ቀባሪው ሀምሳ የሹም ልጅ ቢሞት መቶ ሀምሳ
ሹም ያዛል ቄስ ይናዝዛል
ሹምና ማር እያደር ይከብዳል
ሹምና የጋማ ከብት በጊዜ ይከተት
ሹምና ጥጥ እያደር ይከብዳል
ሹምና ጥጥ እያደር ይከዳል
ሹሩባ ትሰራ ሄዳ ጠጉሩዋን ተላጭታ መጣች
ሹክሹክታ የጠብ ወለምታ
ሺ መት ሺ ሞት
ሺም ታለበ አንድ ያው በገሌ
ሺ በመከረ አንድ በወረወረ
ሺ በመከር አንድ በወረወር
ሺ አውል ሲሞት ሺህ ይሙት
ሺ አውል ከሚሞት ሺ ይሙት
ሺ አውል ኪሞት ሺ ይሙት
ሺ ይሙቱ ሺ አውል አይሙት
ሺ ዝንብ መሶብ አይከፍትም
ሺህ ቢታለብ አንድ በገሌ አለች ድመት
ሺ ቢታለቡ ከገሌ አላልፍም አለች ድመት
ሺ ቢያጨሽ አንድ ያገባሽ
ሺ ያጭሽ አንድ ያገባሽ
ሻማ ራሱ ነዶ ራሱ ብርሀን ይሰጣል
ሻሽ ይደምቃል ማቅ ይሞቃል የሚበጀውን ባለቤቱ ያውቃል
ሻጭ ገዥ ሆኖ ይገምታል
ሽልም እንደሆን ይገፋል ቂጥም እንደሆን ይጠፋል
ሽል ከሆነ ይገፋል ቂጣም ከሆነ ይጠፋል
ሽል እንደሆን ይገፋል ቂጣም እንደሆን ይጠፋል
ሽመልና ዘንግ ቂልና በግ
ሽማግሌ ሳለ ምክር አይጠፋም ጎልማሳ ሳለ ላም አይነዳም
ሽማግሌ በምክሩ አርበኛ በሰናድሩ
ሽማግሌ ካለበት ነገር አይናቅበት
ሽማግሌ ካለበት ነገር አይሰረቅ ጎበዝ ካለበት በትር አይነጠቅ
ሽማግሌ ካልሞተ ሰንዴ ካልመረተ
ሽማግሌ ካልሞተ ሰንዴ ካልሸተ
ሽማግሌ ይገላግላል የተጠቃ አቤት ይላል
ሽማግሌና ስልቻ ሳይሞሉ አይቆሙም
ሽማግሌና ጅብ በላላባት ይገባል
ሽማግሌን ከምክር ከመለየት ከምግብ መለየት
ሽሮን ሲሸውዷት ፕሮቲን ነሽ አሏት
ሽሽት ከኡኡታ በፊት

ሽበት ምን ታረግ መጣህ ቢሉት እኖር ብዬ አለ
ሽበት እኖር ብዬ መጥቻለሁ አለ
ሽታና ግማት ላልሰማ ማውራት
ሽንብራ መኖር በመከራ
ሽንኩርት አንድም በሉት ገማ ደገሙትም ገማ
ሽንኩርት የባህሪውን ይሸታል
ሾላ በድፍን
ሾተልን ወደ ሰገባህ ቁጣህን ወደ ትእግስት
ሾተልን ወደ አራዊት ቁጣህን ወደ ትእግስት
ሾተልን ወደ አፎት ቁጣን ወደ ትእግስት

ቀ

ቀለም ሲበጠበጥ ብርእ ሲቀረጥ
ቀለም ሲበጠበጥ ብርእ ቅረጹልኝ
ቀለበት ለቆማጣ ሚዶ ለመላጣ
ቀሊል አማት ሲሶ በትር አላት
ቀላጅ የሰይጣን ወዳጅ
ቀላዋጭ ወጥ ያውቃል
ቀልብ የሌለው ውሻ ጠዲቅ አምጡልኝ ይላል
ቀልድና ቅዘን ቤት ያጠፋል
ቀልደኛ አልቅሶ ካልተናገረ የሚያምነው የለም
ቀልደኛ ገበሬ ሲያስቀን አደረ
ቀልደኛ ገበሬ ናይት ክለብ ከፈተ
ቀልደኛ ጎረምሳ እያራ ያፏጫል
ቀልድና ቅዘን ቤት ያበላሻል
ቀሙን ላይቀር ከነጨማቸው
ቀማኛና ሽፍታ ጭለማና ማታ
ቀርቀሬ ወርጂ ማር ስልስ ማር ልክፍል
ቀስ በመቀስ
ቀስ እንዳይደፈረስ
ቀስ እንዳይፈስ
ቀስ በቀስ እንቁላል በእግሩ ይሄዳል
ቀስ በቀስ አባይም ዝናብ ይሆናል
ቀበሮ ናት የገጠሩዋ ሚዳቋ ናት የሰፈሩዋ
ቀበሮ የበሬ ቆለጥ ይወድቅልኛል ብላ ስትከተል ዋለች
ቀበቶ ለማፈኛ ሰንሰለት ለማቆራኛ
ቀበኛ ማሰሪያውን በልቶ ያሳጥራል
ቀበኛ ከብት ዋጋውን ያደርስ
ቀባሪ በፈጣሪ
ቀብረው ሲመለሱ እግዜር ይማርዎ
ቀብሮ የሚመለስ የሚመለስ አይመስለውም
ቀኑ የጨለመበት መንገዱ ዘንግ ነው
ቀና ሲታጣ ይመለመላል ጎባጣ
ቀና ቢታጣ ይመለመላል ጎባጣ
ቀናውን ብነግራት ውልግድግዱን አለች
ቀን ስው መስሎ ማታ ጅራት አብቅሎ
ቀን ሲከፋ በግ ይነክሳል

ቀን ሲጥለው ሁሉ ይጠላው
ቀን ሲገለበጥ ውሀ ወደ ላይ ይፈሳል
ቀን ሲደርስ አምባ ይፈርስ
ቀን ሳይቆጥሩ ውሻ ሳይጠሩ ደረሰ በእግሩ
ቀንበር ታርቆ ጣውንት ታርቆ ምን ይሆናል
ቀንበር ታንቆ ጣውንት ታርቆ ምን ይሆናል
ቀን በበቅሎ ማታ በቆሎ
ቀን በቅሎ ማታ ቆሎ
ቀን ቢረዝም ልብ ያደክም
ቀን ቢረዝም ልብ ይደክም
ቀን ቢቆጥሩ ውሻ ቢጠሩ ደረሰ በእግሩ
ቀን ቢቆጥሩ ውሻ ቢጠሩ ይደርሳል በእግሩ
ቀን ባጅብ ሌት በዞብ
ቀን አይጥለው የቀለም ሰረገላ አያሰናክለው
ቀን አይጥለው ጠጅ አያሰክረው
ቀን አይጥለው ጠጅ አያሰክረው የለም
ቀን እስኪወጣ ያባቴ ገበሬ ያግባኝ
ቀን እስኪያልፍልሽ ያባትሽ ሎሌ ያግባሽ
ቀን እስኪያልፍ ያለፋል
ቀን እስኪያልፍ ያባቴ ባሪያ ያግባኝ
ቀን እስኪያልፍ ያባቴ ባሪያ ይግዛኝ
ቀን እንደተራዳ ሌት እንደ ግርግዳ
ቀን ከሀዝብ ሌት ከጅብ
ቀን ከጣለው ሁሉ ይጥለው
ቀን ካልለቀመ ሌት አይቅመ
ቀን ካለቀመ ሌት አይቅመ
ቀን የሰጠው ቅል ድንጋይ ይሰብራል
ቀን የጎደለበት ጠገራ አይጥ ይበላዋል
ቀን ይነዳ እንደ ፍሪዳ
ቀንና ጨርቅ እንደምንም ያልቅ
ቀንና ጨርቅ ያልቃል ብልህ ያውቃል
ቀንዳምን በሬ ቀንድ ቀንዱን
ቀንዱ ሰማይ ጠቀስ ጭራው ምድር አበስ
ቀንድ ካላት ላም ጎዳ ትከፋለች
ቀንድና ጅራት ለዋንጫ አለፋ
ቀንድ አገባበት ጅራት አይቀርም
ቀንድ ውስጥ ገብቶ ጅራት አይቀርም
ቀኝም ሰገሩ ግራም ሰገሩ መገናኛው ኮሩ
ቀድሞ ነበር እንጂ መጥኖ መደቆስ አሁን ምን ያደርጋል ድስት ጥዶ ማልቀስ
ቀድሞ ነበር እንጂ ተራምዶ ማለፍ አሁን ምን ይሆናል ተይዞ መለፍለፍ
ቀይ ምላሱ ጥቁር እራሱ
ቀይ ሰው መልክ አይፈጅም
ቀይ እንደበርበሬ ጥሩ እንደ ብርሌ
ቀዳዳ ያፈሳል ግቢ ያፈርሳል
ቀድሞ ሰኞን አለመሆን ነው
ቀድሞ የሸተውን ወፍ ይበላዋል ቀድሞ የሚናገረውን ሰው ይጠላዋል
ቀድሞ የሸተውን ወፍ ይበላዋል ቀድሞ የተናገረውን ሰው ይጠላዋል
ቀዶ ያለበሰ ቆርሶ ያጎረሰ

ቀጥኜ ቢያየኝ ጅማት ለመነኝ
ቀጥኜ ቢያዩኝ ጅማት ለመኑኝ
ቀጥኜ ቢያዩኝ ሞዴል ነሽ አሉኝ
ቁልቢጥ የላት ቁና አማራት
ቁልቢጥ የላት ድርጎ አማራት
ቁመህ ተከራከር ዙረህ ተመካከር
ቁመህ ተናገር ዙረህ ተመካከር
ቁመቷ  ቢያጥር እንደ ድምብላል ውዷ ክፉ ነው ይደበልላል
ቁም እንደአላማ ቁረጥ እንደጫማ
ቁም እንዳላማ ጥልቅ እንደጫማ
ቁም ነገረኛ መምሰል የተለመደ አመል
ቁም ነገር ይዞ ተረት ቂም ይዞ ጸሎት
ቁራ ሲነጣ አህያ ቀንድ ያወጣ
ቁራ ስሙን የጠራ
ቁርበት ምን ያንቋቁሀል ቢሉት ባያድለኝ ነው እንጂ የነጋሪት ወንድም ነበርኩ አለ
ቁርበት ምን ያንጓጓሀል ቢሉት ባያድለኝ ነው እንጂ የነጋሪት ወንድም ነበርኩ አለ
ቁርጥማት ቢያብር አልጋ ላይ ያማቅቃል
ቁርጥ ያጠግባል ተስፋ ያታልላል
ቁቅም ከፈስ ተቆጠረች
ቁና ለመስፈሪያ ብርብራ ለማስከሪያ
ቁንጥጫ ይሻላል ከግልምጫ
ቁንጫ ለትልቅ ሰው ይበረታል ይባላል
ቁንጫ መሄድ ሳትማር መዝለል ትማራለች
ቁንጫ ሞኝ ናት ቀን ትበራለች ተለቃቅማ ታልቃለች
ቁንጫ ውሀ ወረጅ ቢሏት ስፈናጠር የሰው ዶጬ እሰብር አለች
ቁጥቋጦም ሲያድግ ዛፍ ይሆናል
ቁጥቋጦ ሲያድግ ዛፍ ይሆናል
ቁጥቋጦ ያለዛፍ አይሆንም
ቁጩና ብስጩ አልማችሁ ፍጩ
ቁጭትና መረቅ ለጊዜው ይጣፍጣል
ቁጭትና መጠጥ ለጊዜው ይጣፍጥ
ቁፍ ቁፍ አሰኘሽ እንደቁብ ዶሮ ለመከራ ላሳርሽ ኖሮ
ቂል ሲረግሙት የመረቁት ይመስለዋል
ቂል አይሙት እንዲያጫውት
ቂልን ለብቻው ስደበው ራሱን ባደባባይ እንዲሰደብ
ቂልን አንድ ጊዜ ስደበው ሲሰደብ ይኖራል
ቂልን ድንጋይ ተማትቶ ጌታና ሎሌ ተሟግቶ የማይሆን ነው ከቶ
ቂል ከጠገበበት አይወጣም
ቂል ያገኘው ፈሊጥ ውሻ የደፋው ሊጥ
ቂምህን አትርሳ የወደቀን አንሳ
ቂም ይዞ ጸሎት ሳል ይዞ ስርቆት
ቂም ይዞ ጸሎት ጭድ አዝሎ ወዘት
ቂጡን የተወጋ ውሻ እንደልቡ አይጬህም
ቂጡ የቆሰለ ውሻ እንደልቡ አይጬህም
ቂጥ ቢወድል ፈስ አያድን
ቂጥ ቢያብጥ ልብ አይሆንም
ቂጥኛም ከውርዴ ይማከራል
ቂጥኛም ከውርዴ ይውላል

ቂጥ ገልቦ ክንብንብ
ቂም ቂም ያሰኘሽ እንደዶሮ ለካስ ለመከራሽ ላሳርሽ ኖሮ
ቂፍ ቂፍ ያሰኘሽ እንደ ቆብ ዶሮ ለመከራሽ ላሳርሽ ኖሮ
ቃልህ ሳይዘጋ እግርህ ሳይዘረጋ
ቄሱም ዝም መጽሀፉም ዝም
ቄስ ለኑዛዜ ፍቅር ለሚዜ
ቄስ ምን ይሻል ጠላ ነገር ምን ይሻል ችላ
ቄስ ኤርክሶን መምህሩ እናት አያስቀብሩ
ቄስ እበር አረመኔ ከማህበር
ቄስ ካናዘዘው እድሜ ያናዘዘው
ቄስ ካፈረሰ ዲያቆን ከረከሰ
ቄስና ንብ እያዩ እሳት ይገባሉ
ቄስና ንብ እያየ እሳት ይገባል
ቄስ ያዘዘህን አድርግ እንጂ ቄስ ያደረገውን አታድርግ
ቅል ባገሩ ድንጋይ ይሰብራል
ቅል ባገሩ ደንጊያን ይሰብራል
ቅልና ድንጋይ ተማትቶ ሎሌና ጌታ ተሟግቶ
ቅልና ድንጋይ ተማትቶ ሎሌና ጌታ ተሟግቶ የማይሆን ነው ከቶ
ቅልና ድንጋይ ተማትቶ ጌታና ሎሌ ተሟግቶ የማይሆን ነው ከቶ
ቅልውጥ አሳስቦ ይጥላል ዘመቻ
ቅምሙ የበዛበት ወጥ አይፋጅ አይኮመጥጥ
ቅማል እንኳን ካቅሟ ጥብጣብ ታስፈታለች
ቅማል ውሀ ውረጅ ቢሏት ስንዳሰስ ለመቼ ልደርስ ቁንጫ ውሀ ውረጅ ቢሏት ስፈናጠር የሰው ዶጮ እሰብር አሉ
ቅማል በጥፍር ቢድጧት ራስ ደህና አለች
ቅማል ከአካላት ምስጢር ከቤት
ቋንጣና ባለሟል ሳያር አይቀርም
ቅዝምዝም ወዲያ ፍየል ወዲህ
ቅርብ ያለ ጠበል ልጥ ይነከርበታል
ቅርናታም ለቅርናታም ሰንቡሌ ሰንቡሌ ይባባላል
ቅርንጫፉ እንደዛፉ
ቅቤ መዛኝ ድርቅ ያወራል
ቅቤ ሲለግም ወስፌ አይበሳውም
ቅቤ ተነጥሮ ለመብላት ያባት የናት
ቅቤና ቅልጥም ወዴት ግጥምጥም
ቅቤ ይፍሰስ ከገንፎ አይተርፍ
ቅቤ ይፍሰስ ከገንፎ አይለፍ
ቅል በአገሩ ድንጋይ ይሰብራል
ቅናት ያደርሳል ከሞት
ቅናት ጥናት አያገናኝ ካባት ከናት
ቅናት ጥናት አይገኝም ከናት ካባት
ቅና ያለው በአባቱ ከረባት ይቀናል
ቅና ያለው በናቱ ብልት ይቀናል
ቅን በቅን ከማገልገል ፊት ለፊት ማውደልደል
ቅንቡርስ የት ትሄዳለህ መተማ ትደርሳለህ ልብማ
ቅንነት ለነፍስ መድህኒት
ቅንድብ ለአይን ጥቅሻ አስተማረች
ቅዝምዝም ሲወረወር ጎንበስ ብለህ አሳልፈው

ቅዠት ተፈርቶ ሳይተኛ አይታደርም
ቀላና ደጋ እመቤትና አልጋ
ቀሎ ለዘር እንዶድ ለድግር አይሆንም
ቀሎን ቢቀረጥሙት እንጂ ቢያሹት አያልቅም
ቀመው የሰቀሉትን ቁጭ ብለው ለማውረድ ይቸግራል
ቀማጣ ቤት አንድ ጣት ብርቅ ናት
ቀማጣ ብለው ያው ቁምጥና ነው ሌላ ምን ይመጣል አለ
ቀማጣን ቀማጣ ካላሉት ገብቶ ይፈተፍታል
ቀሩ መቀበሪያው ያው ፈሩ
ቀሩ በማን ምድር ትለፋ
ቀርሶ ያላጎረሱትን ቀዶ ያላለበሱትን ብላቴና ማዘዝ አይገባም
ቀቀ ወዲሀ ቀዝምዝም ወዲያ
ቀንጆና እሸት አይታለፍም
ቀዳ ማንጓጓቱን ስሱ መጓጓቱን
ቀዳ ማንጓጓቱን ስሱ መጓጓቱን አይተውም
ቀዳ ሲወደድ በሬሀን እረድ
ቀጥሮ የማይሰጥ ሌባ ቀጥሮ የማይቀበል ሌባ

## በ

በሃምሌ ጎመንና አሞሌ
በሀምሌ ጤፍ ይዘሩ ቤት ይሰሩ
በለፈለፋ በአፍ ይጠፋ
በልቶ የማይበርደው የሰው ነገር የማይከብደው ሁለቱ አንድ ነው
በልጁ ቀዳ ተጠቅልሎ የተቀበረ የለም
በመስከረም ሊያብድ ያለ ክረምቱ ላይ ጨርቁን ይጥላል
በሙቅ ውሀ የታጠበ በሰው ገንዘብ የቸረ
በማን ላይ ቀመሽ እግዜርን ታሚያለሽ
በሞኝ ክንድ የዘንዶ ጉድጓድ ይለኩበታል
በራቸውን ክፍት ትተው ሰውን ሌባ ነው ብለው ያማሉ
በሬ ሆይ በሬ ሆይ ሞኙ በሬ ሆይ ሳሩን አየሀና ገደሉን ሳታይ እልም ካለው ገደል ወደቅክብን ወይ
በሬ ቀባቱን በቀልጥሙ ይዞ ይኖራል ለምንህ ቢሉት ኋላ ለገዛ ቁርበቴ ማልፊያ ይሆነኛል አለ
በሬ ካራጁ ቢላ ተዋሰ
በሬ ካራጁ ይውላል
በርበሬን ከላመ ከሞተ አግኝተሽው ዋጥ ስልቅጥ አድርገሽ ከምኔው ጨረሽው
በሰው ምድር ልጁን ትድር
በሰው ቁስል እንጨት ስደድበት
በሰፈሩት ቁና መሰፈር አይቀርም
በሴትና በውሀ የማይርስ የለም
በሰራህ ደሀ አትበድል ነጋሪት ባይኖረው እንባ አለው ውሀ ሆኖ ቢኮል ያለ ሞረድ የተሳለ ነው
በሽታውን የደበቀ መድሀኒት አይገኝለትም
በሽታውን የደበቀ መፍትሄ  አያገኝም
በሽታውን የደበቀ ተፋተሸ
በሽታውን የደበቀ ቫይረሱ አለበት
በቅሎ ማሰርያዋን በጠሰች  ለራስዋ አሳጠረች
በቅሎ አባትህ ማነው ቢሉት እናቴ ፈረስ ነች አለ
በቅሎ ገመድ በበጠሰች በራሷ አሳጠረች

በቅሎ ግዙ ግዙ አሞሌ ላያግዙ
በቅርብ ያለ ጠበል ልጥ መንከሪያ ይሆናል
በቆፈሩት ጉድጓድ መቀበር አይቀርም
በበጋ አሞኝ ቤት ተንጋጋ በክረምት እቤትህ ተከተት
በባዶ ቢቀጡ በጨለማ ቢያፈጡ
በቤቷ ቀጋ በውጪ አልጋ
በትር ለገና ነገር ለዋና
በትር ለገና ውሀ ለዋና
በአህያ ቆዳ የተሰራ ድንኳን ጅብ ሲጮህ ይፈርሳል
በአንድ ጣት ፊት አይታጠብም
በአደባባይ ወተት በቤት ውስጥ ጉጠት
በአጎረስኩኝ ተነከስኩኝ
በአጎረስኩኝ እጄን ተነከስኩኝ
በአፉ ቅቤ አይሟሟም
በአፍ ይበሉበታል እንጂ ክፉ አይናገሩበትም
በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ
በእውር ቤት አንድ አይና ብርቅ ነው
በእውር አገር ጠንባራ ንጉስ ነው
በእውሮች ከተማ አንድ አይና ንጉስ ነው
በእጅ ያለ መዳብ እንደወርቅ ይቆጠራል
በእጅ ያለ ወርቅ እንደ መዳብ ነው
በእጅ ያለ ወርቅ ከመዳብ ይቆጠራል
በካፊያ የሚርስ
በክረምት በርኖስክን አታውል እቤት
በወተት ላይ ውሀ መጠጣት ያበዛዋል ያነጣዋል
በውሻ ሆድ ቅቤ አያድርም
በዘጠና ገዝቶ በዘጠና መሸጥ ትርፉ እንዘጥ እንዘጥ
በየወንዙ ሀሌ
በደረቅ አበሳ እርጥብ ይነዳል
በደንባራ በቅሎ ቃጭል ተጨምሮ
በጅብ ቆዳ የተሰራ ከበሮ ቅኝቱ እንብላው እንብላው ነው
በጅብ ቆዳ የተሰራ ከበሮ ሲመቱት እንብላው እንብላው ይላል
በጋለሞታ ቤት ሁሉ ይጣላበት
በግ ከበረረ ሞኝ ካመረረ አይመለስም
በጠራ ተሻገር በተሳለ ምተር
በጥቅምት አንድ አጥንት
በጫጩት ፊት ስለ ፈንግል አይወራም
ቡና እና ማሽላ እየሳቀ ያራል
ቡዳ በወዳጁ ይጠናል
ቡዳ ቤት ሰላቢ ገባ
ቢዋደዱ ጾም ገደፉ ቢጣሉ ተዋረፉ
ቢደፏት ቂጥ የላት ቢገለብጧት ጡት የላት
ቢጠሩሽ አትሰሚ ቢጠቅሱሽ አታዩ ሪጋ ብለሽ ሂጂ ብር ብር አትበዪ
ባህታዊ እንደናፈቀ ይሞታል
ባህያ ማገር የተሰራ ቤት ይበጣጠሳል ጅብ የጮኸ ለት
ባህያ ቆዳ የተሰራ ቤት ብትንትን ይላል ዥብ የጮኸ ለት
ባለቤቱን ካልናቁ ሚስኮል አያደርጉ
ባለቤቱን ካልናቁ አጥሩን አይነቀንቁ

ባለቤቱን ካልናቁ ውሻውን አይነኩ
ባለቤቷን ያመነች በግ ላቷን ውጭ ታሳድራለች
ባለቤቱ ያቀለለውን ባለእዳ አይቀበለውም
ባለቤት ያቀለለውን አሞሌ ባለእዳ አይሸከመውም
ባለቤት ካልጨኸ ጎረቤት አይረዳም
ባለጌን ተነስ አይሉትም
ባለጌን ከወለደ የገደለ ጸደቀ
ባለጌ ያለበት ሸንጎ ዝንብ የገባበት አርጎ
ባለጌ ያለዉ ቻት ሩም እሾህ ያለዉ አሳም ነገሩም ልዋጥህ ቢሉት እሺ አይልም
ባለጌ የጠገበ እለት ይርበው አይመስለውም
ባቄላ አለቀ ቢሉ ፈስ ቀለለ
ባለፈ ክረምት ቤት አይሰራም
ባሏን እጎዳው ብላ መንታ ልጅ ወለደች
ባሏን እጎዳው ብላ እንትኗን በእንጨት ወጋች
ባል ሳይኖር ውሽማ
ባልሽ ቀላ ወርዶ ሰማይ ሰማይ ሲያዪ አንቺ ከኔ ጋራ ሰበር ሰካ በዪ
ባልና ሚስት ካንድ ባህር ይቀዳል
ባልና ሚስት ከአንድ ባህር ይቀዳሉ
ባለጌ ባለሟል ልብስ ገልቤ ልይ ይላል
ባል ነበር ይቻል ነበር
ባልና ሚስት ሊተዋወቅ የሰርገኛ ልብ ይውለቅ
ባልና ሚስት ከአንድ ባህር ይቀዳል
ባልን ወዶ ምጥን ፈርቶ
ባርያና ቃርያ ጌታውን እንዳቃጠለ ይኖራል
ባጎረስኩ እጄን ተነከስኩ
ባጎረስሁኝ ጣቴን ተነከስኩኝ ባፍ ይጠፋ በለፈለፋ
ባልዋን ጎዳሁ ብላ ትምህርት ቤት ገባች
ባልዘፈንሽ ከዘፈንሽም ባላሳፈርሽ
ባልዘፈንሽ ከዘፈንሽም ባላፈርሽ
ባለጌን ካሳደገው የገደለው ይጽድቃል
ቤተ ሰሪ የተሰረቀ ቦታ አይገዛም
ብላ ያለው ቀርቦ ተሸከም ያለው ተከማችቶ ይጠብቀዋል
ብልህ ሚስት ለባሏ አክሊል ናት
ብልጥ ለብልጥ አይን ብልጥጥ
ብልጥ ሲለግም አመድ በዱቄት ይለውጣል
ብርሌ ከነቃ አይሆንም እቃ
ብርቅና ድንቅ  አላንድ ቀን አይደምቅ
ብርድ ቢያብር ለቁርጥማት ይዳርጋል
ብቀጥንም ጠጅ ነኝ
ብቻውን የበላ ብቻውን ይሞታል
ብዙ ከብት ለማርባት አልቅትን ጠብቀ ውሀ ማጠጣት
ብድሩን የማይመልስ ልጅ አይወለድ

## ተ

ተሁለት ዛፍ የወደቀ
ተሁሉም ያው ወንድም ቢከፋም ቢበጅም
ተለመደና ዶሮ መከሸከሸ እኝህ እናትሽ ሀሙስ ከች

ተለማማጭ አልማጭ
ተለማበት የተጋባበት
ተለጣጭ የጎረቤቷን ድልህ ሿጣጭ
ተለጣጭ የጎረቤቷን ድልህ አሿጣጭ
ተላም የዋለ በሬ ተሴት የዋለ ገበሬ
ተላም የዋለ በሬ ከጋለሞታ የዋለ ገበሬ
ተሌባ ሌባ ቢሰርቀው ምን ይደንቀው
ተልባ መስሎሽ ሰናፍጭ ትቀምሽ
ተልባ በቅባ ኑግ ለሰሚው ግራ ለበይው መልካም ነው
ተልባ በጥባጭ ሳለች ጎመን ቀንጣሹዋን ምች መታት
ተልባ በጥባጭ እያለች ጎመን ቀንጣሹዋን ምች መታት
ተልባ ቢንጫጫ ባንድ ሙቀጫ
ተመልከት አላማህን ተከተል አለቃህን
ተመልከኛ ዳኛ መልካም ፈራጅ
ተመምሩ ደቀመዝሙሩ
ተመመራመር ይገኛል ነገር
ተመመራመር ይገኛል ቁምነገር
ተመሞት ይሻላል መስንበት
ተመረቅሁ ብለህ ተተረገመ አትዋል
ተመረቅሁ ብለህ ከተረገመ አትዋል
ተመርቄያለሁ ብለህ ከተረገመ አትዋል
ተመሮጥ ማንጋጠጥ
ተመሮጥ ማንጋጠጥ ይሻላል
ተመንግስት አመልጣለሁ ለሞት እድናለሁ ማለት ዘበት
ተመክሮ ልብ ተሽምቶ ድልብ አይሆንም
ተመዋረድ ጌታን መውደድ
ተሿጋች - እኔ እረታ ይመስለኛል ሰውም ይመለከተኛል
ተሙጃ መሀል የወጣች ቁጤማ ወይ ለወፍ ወይ ለባላ
ተማሪ ዘኬ ለቃሚ
ተማሪ ውሻ ቀባሪ
ተማሪና ዶሮ በሞቱ ክብሩ ነው በቁመናው እራቱ ጥሬ ነው
ተማሪና ዶሮ በሞቱ ክቡር ነው በቁመናው እራቱ ጥሬ ነው
ተማክረው የፈሱት ፈስ አይገማም
ተማክሮ የፈሱት ፈስ አይገማም
ተምሮ የማይጸፍ አክፍሎ የማይገድፍ
ተምሮ ያላስተማረ ዘርቶ ያላጠረ
ተሞተች ሚስቴ ምን አለኝ ካማቴ
ተሞኝ ደጅ ሞፈር ይቀረጣል
ተረታን እንዳይሉ ይግባኝ ይላሉ
ተረቴን መልስ አፌን በዳቦ አብስ
ተረት ለነገር ይሆናል መሰረት
ተራራ ለጥናት ውሀ ለጥማት
ተራስ በላይ ንፋስ
ተራጋሚ ራሱን ደርጋሚ
ተርጅናና ተሞት ቢሽሹ አያመልጡ
ተሰብሮ ቢጠገን እንደነበረ አይሆን
ተሰብሮ ቢጠገን እንደድሮው አይሆን
ተሰው አለሁ ብዬ ከጅብ ተዳብዬ

ተሰው አለሁ ብዬ ከጅብ ጋር ተዳብዬ
ተሰግዳዳ ቦታ ታዳጊ ጌታ
ተሰሰታም አንድ ያንቀው አንድ ይወድቀው
ተሰፋ መስጠት እዳ መግባት
ተሰፋ መስጠት እያዩ እዳ መግባት
ተሰፋ ርቆ የተሰቀለ ዳቦ ነው
ተሰፋ ቀርጠ አንድ ላይ ከመቆም ይሻላል በተሰፋ ሲጓዙ መክረም
ተሰፋ ያልቆረጠ መነኩሴ ምናኔ ሲሄድ ሴቲቱን ይሰናበታል
ተሰፋ ያድናል ክህደት ያመነምናል
ተሰፋ የተሰቀለ ዳቦ ነው
ተሽፋፍኖ ቢተኙ ገልጦ የሚወጋ ጌታ አለ
ተሽፋፍኖ ቢተኙ ገልጦ የሚያይ አምላክ አለ
ተሹሞ ከመታለል ጥሎ መክብለል
ተሺ ምስክር የታቦት እግር
ተሻገር ከወንዙ ጉድ እንዳያበዙ
ተቀመጥ በወንበሬ ተናገር በከንፈሬ
ተቀማጭ አፋ ምላጭ
ተቀማጭ የሌለው ተሟጋች ስልቻ የሌለው ቧጋች
ተቀማጭ የሌለው ተሟጋች ስልቻ የሌለው አንጋች
ተቀምጠው የሰቀሉት ቆመው ለማውረድ ያስቸግራል
ተቀባሪ ወዲያ ማን ያርዳ
ተቀዳዳ ይሻላል ጨምዳዳ
ተቁመቱ ማጠር የልቡ መጠጠር
ተቁመትህ ማጠሩ ሆድህ መጠጠሩ
ተቁም ዶሮ ከሸክላ ማሰሮ
ተቂል አትጫወት አይንህን ያወጣል በእንጨት
ተቅበላ ጥጋብ የስቅለት ጦም ማደር ይሻላል
ተቆብ ላይ ሚዶ
ተበድሮ ቅቤ ታርዞ ጎፈሬ
ተባለ ቀትር አትቀታተር
ተባቄላ አይጠፋም ዲቃላ ከጠላ አይታጣም አተላ
ተተሳለ የማይበርድ ተታዘለ የማይወርድ
ተተናገረ አያባራ አፋቸው ከያዘ አይለቅ ምንቸታቸው
ተተናገረ አያባራ አፋቸው ከያዘ አይለቅ እጃቸው
ተተያዙ ብዙ ነው መዘዙ
ተተያዙ ወዲያ ቂስ ጥሩልኝ ማለት ላያደላድሉ በሺ ብር ጭነት
ተታመሙ መክሳት ካጡ መንጣት
ተናት ቀን ይሻላል
ተናካሽ ውሻ የጅብ መቋደሻ
ተናካሽ ውሻህን ተዋጊ በሬህን እሰር
ተናካሽ ውሻ የጅብ መደገሻ
ተናዞ ይሞቷል አምኖ ይሟገቷል
ተናገር በከንፈር ተቀመጥ በወንበር
ተናግሮ አናገረኝ ይወደኝ ይመስል ሄዶ ተናገረ የላክሁት ይመስል
ተናግሮ አናገረኝ ይወደኝ ይመስል ሄዶ ተናገረ የላኩት ይመስል
ተናግሮ አናግሮ የሆድን ጨርሶ ጠላት ይሆናል ወዳጅ ተመልሶ
ተናግሮ ከማሰብ ተከንፈር መሰብሰብ
ተናግሮ ከማሰብ ከንፈርን መሰብሰብ

ተናግሮ ከመጨነቅ የቀልቀሎዬን አፋን እንቅ
ተናግሮ ያጣ ሰው ሶስት ጊዜ ሞቱ ነው
ተንከትክተሽ ስትስቂ የጥርስሽ ወገብ እንዳይቀጭ
ተንኮለኛ መበለት በጾም ዶሮ በፋሲካ እልበት
ተንኮለኛ የሰይጣን አርበኛ
ተንኮለኛ ተሰባብሮ ተኛ
ተንኮለኛ ናቸው አርቃችሁ ቅበሩዋቸው
ተንኮለኛ ገደል ዝንጀሮ ይጥላል በሬ ያሳልፋል
ተንጋሎ ቢተፉ ተመልሶ ካፉ
ተኺ ብልሽ አትነሺ እልኩሽ(ን)
ተኛ ወዲያ ጎራሽ እህል አበላሽ
ተከበሩ ሰው አይፈሩ
ተከብሮ ያደርጋል ደንቆሮ
ተኩብት እንስት ተሀብት ርስት
ተከተማ ወደዱር ተአልጋ ወደምድር
ተከናንቦ የሚበላውን ተጎንብሰህ ግባበት
ተከፊት ያለው ጉሮሮ ጠም አያድርም
ተኩላ እንደ አንበሳ እጨሀ ብላ ተተረተረች
ተኩላ ፍየል በላ
ተኩሶ ጣለ ወጋ ነቀለ
ተኳሽ በሁለት አይኑ አያነጣጥርም
ተክፉ ተወልጄ ስፈጭ አደርኩ
ተክፉ ጎረቤት አይሰሩም ደህና ቤት
ተኮሰ ጣለ ወጋ ነቀለ
ተወደዱ ወዲያ ገደሉ ሜዳ
ተወገብ በላይ ታቦት ከወገብ በታች ጣኦት
ተወገብ በላይ ጥጋብ ተወገብ በታች ራብ
ተወጭት አፍ የወንጭት አፋፍ
ተወጭት አፍ ተወንጭት አፋፍ
ተወፈሩ ፈጣሪን አይፈሩ ሰውን አያፍሩ
ተዋርዶ ከማግኘት ኮርቶ ማጣት
ተዋቅሶ ወዳጅነት የቂም ጠባሳ ባንገት
ተዋሰኝ ግዝት ይሆነኝ አበድረኝ አይማረኝ
ተዋጊ በሬ ተጭድ ይጣላል
ተዋጊ በሬህን ተናካሽ ውሻህን ያዝ
ተው አትርሳ ተሰርቶልሀል የሳት ገሳ
ተው ፈረሴን ለጉም አይዘነጉም ለሴትና ለጉም
ተዝካር ያየ ተማሪ ሽቀጥ ያየ አጣሪ
ተዝካር ያየ ተማሪ ሽቀጥ ያየ አጣሪ አይን የለውም
ተይዛ ትዘፍን ጠጣ
ተይዞ ከመለማመጥ አርፎ መቀመጥ
ተደርቦ መጣላት ስራ ማጣት
ተደብቃ ትጸንሳለች ሰው ሰብስባ ትወልዳለች
ተደብቃ ትጸንሳለች በሰው ስብሳብ ትወልዳለች
ተድረው ቢመለሱ የውሀ መንገድ ረሱ
ተድረው ቢመለሱ የውሀን መንገድ ረሱ
ተዳኛ ተሟግቶ ታዲያማ ተዋግቶ
ተዳኛ ተሟግቶ ላያደማ ተዋግቶ

ተጀመሩ መጨረስ ካራገዱ ማልቀስ
ተጀ በጉንጩ
ተገናኝተናል መሳ ለመሳ አንቺም እውር ነሽ እኔም አንካሳ
ተገናኝተው ሳሉ ምን ጊዜ እንገናኝ ይላሉ
ተገዳዩም ሟቹ ይጣደፋል
ተጋበዙና ብሉ ሀይ በሉ ከልክሉ
ተጋፊ ውሀ ሽቅብ ይሄዳል
ተጋፊ ውሀ አሻቅቦ ይፈሳል
ተግደርዳሪ ጠም አዳሪ
ተግደርዳሪ በልቶ ሽሮ ተበዳሪ
ተግደርዳሪ ቀላዋጭ ቀባጣሪ
ተጎሽ እበት ተንጨት ሽበት
ተጎንብሶ የሚበላን ተኝተህ ቀላውጠው
ተጠማኝ ቢሰነብት ባለርስት ይሆናል
ተጠንቀቅ ወደል እንዳትገባ ገደል
ተጥዶ የማይፈላ ተሹሞ የማይበላ
ተጥዶ የማይፈላ ተሹሞ የማይበላ የለም
ተጠረኛ ስንቅ አይደባልቁ
ተጠጣ የዋለ ጉሬዛ እህል ፊጅቶ ገባ
ተጨንቆ ኩራት ተንጠራርቶ ራት
ተጫውቶ መማረር አለ ጉዳይ መብረር
ተፈጣሪ ሙርጥ ጫሪ
ተፈጣሪ ይበልጣል ቂጥ ጫሪ
ተፈጥሮን  ተመክሮ አይመልሰውም
ተፈጭቶ ያልተነፋ ዱቄት ተበራይቶ ያልተመረተ ምርት
ተፈጥሮ ሞት ተሾሞ ሽረት
ተፈጥሮን ተመክሮ አይመልሰውም
(ጠያቂ) ታድያስ (መላሽ) አለን በአዲዳስ ያውም ሳንዋስ
ታጥቦ ጭቃ
ታላቅ ወንድም እንደ አባት ይቆጠራል
ታላቅ ጠር ባይወጉበት ያስፈራሩበት
ታለቀ መቆጠብ ተሞተ መንጠብጠብ
ታላረፋ መከራ ነው ትርፋ
ታላቁን ነገር እየተመኘሁ ቢከፍቱት ተልባ ሁኜ ቀረሁ
ታላወቀ ዘዴ በለው በጎራዴ
ታልተናገሩ አይከፈት በሩ
ታልቻኮሉ ቀስ በቀስ ይገኛል ሁሉ
ታሞ የተነሳ እግዜርን ረሳ
ታሞ የተነሳ እግዚሄርን ረሳ
ታሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ
ታረጂ ወዲያ ጎፈሬ አዝመራ የሳተው ገበሬ
ታልጠገቡ አይዘሉ ካልዘለሉ አይሰበሩ
ታረጁ አይበጁ
ታሪክን የረሳ ስህተት መድገሙ አይቀርም ይባላል
ታርቂ ተመርቂ ታጥቤ ተለቃልቂ
ታርቆ ሙግት በልቶ ስት
ታሳጭ ማራኪ ይሻላል
ታሳጭ መካሪ ይሻላል

ታስሮ ከመማቀቅ ይሻላል መጠንቀቅ
ታቀበት በረዶ ተቁልቁለት ዘንዶ
ታባ ቁፍር እሸት ተበልቶለት
ታባቱ የተረፈ ተጠለፈ
ታቦተ ክፉ አጸደ መልካም
ታቦት በራሱ ቃጭል በጥርሱ
ታከረሩት ይበጠሳል
ታየው ትመለከተው ትታነቀው ትሞተው
ታዝበው ኪጠሉህ ታዝበው ይውደዱህ
ታዝበው ሲጠሉህ ታዝበው ይወደዱህ
ታዳጊ ያለው በግ ላቱን በውጭ ያሳድራል
ታጉል ጉልበት እዩልኝ ስሙልኝ ማለት
ታጉል ጥንቀላ የጨዋ ልጅ መላ
ታጥቦ ጭቃ
ታጥቀህ ታገል እንዳትንገላታ አስተውለህ ተሟገት እንዳትረታ
ትለብሰው የላት ትከናነበው አማራት
ትላንት ልጄን ዛሬ እናቴን ምን ይበጃል ዘንድሮ አለ አውራ ዶሮ
ትልቁ አሳ ትንሹን አሳ ይውጣል
ትልቁ ዳቦ ሊጥ ሆነ
ትልቅ ብልሀት ለንጉስ መገዛት
ትልቅ ብልሀት ለትምህርት መትጋት
ትልቅ ጥቃት ለምኖ ማጣት
ትልና መጋዝ በሽተኛና ጓዝ
ትምህርትም እንደ ኮት ፋሽኑ አለፈበት
ትምህርት በልጅነት አበባ በጥቅምት
ትምህርትን ለፈጠረ ጥይት በርጨን ላገኘ ገነት
ትምህርት ከሚሉት ነቀርሳ ኤድስ ከሚሉት በሽታ ያውጣን
ትምህርት የማያልቅ ምርት
ትምህርት የማያልቅ ሀብት
ትሻልን ትቼ ትብስን አገባሁ
ትተውት የማይሄዱትን ባልንጀራ አይቀድሙትም
ትናንሽ ልጆች ትናንሽ ሀብቶች
ትንሳኤ ትንሳኤ ቢሉኝ ጸሎተ ሀሙስ መሰለኝ
ትንሽ ምላጭ አገር ትላጭ
ትንሽ ሰው ትንሽ ነው
ትንሽ ስጋ እንደ መርፌ ትወጋ
ትንሽ ሽሮ ባገኝ ጨው የለኝም እንጂ ተበድሬ ወጥ እሰራ ነበር
ትንሽ ልጅ ከሰራው ሽማግሌ የጎበኘው
ትንሽ ቀሎ ይዞ ካሻሮ ጠጋ
ትንሽ ቀሎ ያደርሳል ካሻሮ
ትንሽ አበላሽ
ትንሽ ሰው ትንሽ ነው
ትንሽ ጎልማሳ ትቢያ ታነሳ
ትንቢት ይመራል ልጓም ይገራል
ትንኝም ለሆዱ ዝሆንም ለሆዱ ወደ ወንዝ ወረዱ
ትንኝም ለሆዱ ዝሆንም ለሆዱ ተያይዘው ወደ ወንዝ ወረዱ
ትንሽ በመናገር እውነት ትከበር
ትኩስ ሬሳ ደረቁን አስነሳ

ትንሽ ጭላንጭል ታስይዛለች ምንጭር
ትእቢትን ከስስት ምን አገናኝቶት
ትእግስተኛ ከፈለገበት ይደርሳል
ትእግስት ፍራቻ አይደለም
ትካዜ ሲመጣ መከፋት ጓዝ ይሆናል
ትገርም ሻሽመኔ ትብስ ኮፈሌ
ትጸድቅ ትኮነን ቢለው ቀይ መክሬ አስታውቅህለሁ አለ
ትፈጭ የነበረች ማንጓለል አቃታት
ትፈጭ የነበረች ማንጓለል ተሳናት
ቶሎ ቶሎ ቢቆጡ አብረው አይቀመጡ
ቶፋ በማን ምድር ትለፋ
ቶፋ መቀበሪያው ያው ፈፋ

## ቸ

ቸር ተመኝ ቸር እንድታገኝ
ቸርን ቢያጠቁት ቢስ ይሆናል
ቸር ይመጸውታል ጠላት ያጠፋል
ቸኩለው ያፈሱታል ተቀምጠው ይለቅሙታል
ቸኩሎ ከተጠቀመ ዝግ ብሎ የተጎዳ ይሻላል
ቻቻታ የለመደ ሰው አባይ ዳር ቅበሩኝ ይላል
ችኩል ሰው ጠንቋይ ይጠይቃል
ችኩል ቅቤ ያንቀዋል
ችኩል አደንጓሬ ሳይበሉት ሆድ ያሟል
ችኩል አፍ ሞትን ይጠራል
ችኩል እግር ከዘንዶ ጉድጓድ ይገባል
ችኮ የጠም ስጋ
ችግረኛ ሲናገር ውሸት ሲደነፋ እውነት
ችግር ለወዳጅ ሲያዋዩት ይቀላል
ችግር በቅቤ ያስበላል አለች ዉሻ
ችግር ነው ጌትነት
ችግር የገረፈው ውጤቱ ያማረ ካልተንቀባረረ

## ነ

ነቅናቂ ሳለ ማን ጥሩ ይጠጣል
ነበረ እንጂ ይኖራል የሚባል ፍጡር የለም
ነበርንበት አትኩሩበት
ነቢያት በመደመዱ ሀዋርያት ገደገዱ
ነቢያት በቀየሱ ሀዋርያት ገሰገሱ
ነቢዩ ቢኖር በከበረ ነበር
ነቢዩ ባገሩ አይከበርም
ነብር ቢያንቀላፋ ዝንጀሮ ጎበኘው
ነብር ባየለበት ዘመን ድመት ይበረታል
ነብር ባየለበት ዘመን ድመት ይኮርታል
ነብር ሳይገድል ቆዳውን ያስማማል
ነብር አየኝ በል
ነብር አይኑን ታመመ ፍየል መሪ ሆነ

ነብር የሞተ እለት ፍየል ልጅዋን ትድራለች
ነዋሪ ለዘላለም አለ አምላክ የለም
ነውር ለባለቤቱ እንግዳ ነው
ነገረኛ ሰው ከቤቱ አይሞትም
ነገረኛ ቃሞ አይተኛ
ነገረኛ ናቸው አርቃችሁ ቅበሩዋቸው
ነገረኛ ናቸው አጥልቃችሁ ቅበሩዋቸው የተነሱ እንደሆን ብዙ ነው ጣጣቸው
ነገረኛ ዝንጀሮ ውሻ ታረባለች
ነገሩ ነገር ነው ውስጡ ጥቅንጥቅ ነው
ነገሩ ነገር ነው ውስጡ ጉራንጉር ነው
ነገሩ ነው እንጅ ቢላዋ ሰው አይጎዳም
ነገሩ ነው እንጅ ጩቤ ሰው አይጎዳም
ነገሬ በሆዴ መንገዴ ባመዴ
ነገሬ በከንፈሬ
ነገር ለበለጠ ውድማ ለመለጠ
ነገር ለበለጥ ውድማ ለመለጥ
ነገር ለሰሚ ውሀ ለሎሚ
ነገር ለጀማሪው እሳት ለጫሪው
ነገር ሲበዛ ይሆናል ዋዛ
ነገር ሲያመልጥ ራስ ሲመለጥ
ነገር ሲያመልጥ ራስ ሲመለጥ አይታወቅም
ነገር ሲያመልጥ እራስ ሲመልጥ አይታወቅም
ነገር ሲጀመር እህል ሲከመር
ነገር ሳያውቁ ሙግት ሳይጎለብቱ ትእቢት
ነገር ሳያውቁ ሙግት አቅም ሳይኖር ትእቢት
ነገር ስንት ነው ሁለት ምን ያበዛዋል ውሸት
ነገር በሆዴ መንገድ በአመዴ
ነገር በሆዴ እየተመኘሁ ቢከፍቱት ተልባ ሆኜ ተገኘሁ
ነገር በለዛው ጥሬ በለዛዛው
ነገር በልክ ሙያ በልብ
ነገር በመልከኛ ጠላ በመክደኛ
ነገር በምሳሌ ጠጅ በብርሌ
ነገር በምሳሌ ጠጅ በብርሌ መዝሙር በሀሌ
ነገር በምሳሌ ጠጅ በብርሌ ዜማ በሀሌ
ነገር በቀጠሮ ዘፈን በከበሮ
ነገር በትኩሱ ጨዋታ በወዙ
ነገር በነገር ይጠቀሳል እሾህ በእሾህ ይነቀሳል
ነገር በእርቅ መንገድ በድርቅ
ነገር በእርቅ ወይፈንን በድርቅ
ነገር በወቀሳ በደል በካሳ
ነገር በዋስ እህል በነፋስ
ነገር በዋና ሚዶ በእረኛ
ነገር በዋና ሜዳ በእረና
ነገር በዋና ዘፈን በገና
ነገር በዋናው ንብ በአውራው
ነገር በዳኛ ሚዶ በእረኛ
ነገር ቢሳሳት ከጥንቱ ሰይፍ ቢመዘዝ ካፎቱ
ነገር ቢሳሳት ከጠዋቱ ጥጃ ቢሳሳት ከእናቱ

ነገር ቢበዛ ባህያ አይጫንም
ነገር ባዋቂ ብረት በጠራቂ
ነገር አለኝ ከማለት ስራ አለኝ ማለት
ነገርን አድምጠ እህልን አላምጠ
ነገር እንደዛፉ ዛፉ እንደቅርንጫፉ
ነገር ከመጀመሪያው እህል ከመከመሪያው
ነገር ከመጀመሪያ ፍለጋ ከመሻገሪያ
ነገር ከመጀመሪያው ውሀ ከመሻገሪያው
ነገር ከሰነበተ ቅራሪ ከሆመጠጠ
ነገር ካምጨ ውሀ ከምንጨ
ነገር ከስሩ ውሀ ከጥሩ
ነገርን ከስሩ ውሀን ከጥሩ
ነገር ከእብድ ይገኛል
ነገር ከእጅ ይገኛል
ነገር ከዋሰ ምላስ ከጥርስ
ነገር ከዋሰ ምላስ ከጥርስ አያልፍም
ነገር ከውሉ ጋሻ ከንግቡ
ነገር ከግቡ ጋሻ ከእንግቡ
ነገር ከፊቱ ዱቄት ከወንፊቱ
ነገር ካንሹ ስጋ ከጠባሹ
ነገር ካንሺው ስጋ ከጠባሺው
ነገር ካጀማመሩ እህ ል ካከማመሩ
ነገር ወዳድ ሰው ከመንገድ ዳር ቅበሩኝ ይላል
ነገር ወዳጅ ሰው ከመንገድ ዳር ቅበሩኝ ይላል
ነገር ወዳጅ ከቤቱ አይሞትም
ነገር ወዴት ትሄዳለህ ጎንደር መጨረሻህ ታገር
ነገር ያለዳኛ ትብትብ ያለመጫኛ
ነገር የሚከረው ጎንጓኙን ሲያገኝ ነው
ነገር የሻ ዳኛ አምጡ ይላል የዶሮ ሻኛ
ነገር የዋለበት ዳኛ ያውቃል ከብት የዋለበት እረኛ ያውቃል
ነገር የፈራ ይቃጠራል አውሬ የፈራ ያጥራል
ነገር ያለዳኛ ተረት ሰማይ ያለ ደመና ብረት
ነገር ፈጣሪውን እሾህ አጣሪውን
ነገር ነገርን ያነሳል ጥጋብ ሞትን ያስረሳል
ነገርህና ነገሬ ልክ ነው ሰው መስማቱ ትርፍ ነው
ነገር ነገርን ያመጣል ድግር አፈር(ን) ያወጣል
ነገርህን በጠጄ ርስትህን በልጄ
ነገር በነገር ይወቀሳል እሾህ በሾህ ይነቀሳል
ነገርም ይበረክታል ባለጋራም ይታክታል
ነገርኩት መሰዬ እንዲመሰለው ብዬ
ነገር መጫኛ እንዳሳጠሩት ወይም እንዳስረዘሙት ነው
ነገርና ገመድ አለውሉ አይፈታም
ነገርን በእርቅ ወይፈንን በድርቅ
ነገር እንዲጠፋ ዳኛውን ግደል
ነገር ነገርን ይወልዳል
ነጋሪ የሌለው ይታማ አይመስለው
ነጋዴ ወረቱን ዘላን ከብቱን ገበሬ ምርቱን
ነጋዴን ተዘማች ምን አቀላቀለው

ነጻነት ያኮራል ስራ ያስከብራል
ነጭ ሽንኩርት በመሽተቱ እራሱን ቀብሮ ይኖራል
ነጭ ድሀ ነጭ ማር ይከፍላል
ነጭ እንደሽማ ትክል እንደትርሽማ
ነጭ እንደሽማ ትክል እንደአክርማ
ነፋስ በተነሳበት ጊዜ እሳት አይጭሩም
ነፋስ ሲነሳ እሳት አይጫርም
ነፍጥ ቢያጓራ የጌታውን ጎን ይሰብር
ነፍጥ ቢያጓር የጌታውን ጎን ይሰብር
ነፍስ በፈጣሪዋ ሴት ባሳዳሪዋ
ኑር ባገር ጥፋ ካገር
ኑሮ በዘዴ አቶ ዘወልዴ
ኑሮ በዘዴ ጾም በሁዳዴ
ኑሮ በደጋ መተኛት ባልጋ
ኑሮ ቢያምርህ ችላ ጥጋብ ቢያምርህ ባቄላ
ኑሮ ከማናደድ ሄዶ መመስገን
ኑሮ ከማናደድ ሄዶ መናፈቅ
ኑሮ ካሉት መቃብር ይሞቃል
ኑሮ ካሉት የጤፍ ቅጠል ሁለት ሰው ያስተኛል
ኑሮ ካሉት ፍሪጅ ይሞቃል
ኑሮ ካሉት ፍሪጅ ይሞቃል አለ የቢራ ጠርሙስ
ኑ ባይ ከባሪ እንቢ ባይ ቀላይ
ኑሮ ኑሮ ከመሬት ዙሮ ዙሮ ከቤት
ኑሮ ኑሮ ከመሬት ዙሮ ዙሮ ከቤት አይቀርም
ኑሮ ያዷኑራል ህግ ያከባብራል
ናቂ ወዳቂ
ና ብላ ሳይሉት ከወጡ አውጡልኝ
ና ያሉት እንግዳ እራቱ ፍሪዳ
ናዳ መጣልህ ቢሉት ተከናንቤአለሁ አለ
ናዳ መጣልህ ቢሉት ተከናንቤአለሁ ልቀቀው አለ
ንቡን አባሮ ማሩን
ንብ ላጥር ሳያረዳ አይሄድም
ንብ ሲሰማራ አጥሩን ተመልከት
ንብ ቢሄድ ካጥር ሰው ቢሄድ ካገር
ንብ ቢሄድ ካጥር ሰው ቢሰደድ ካገር
ንብ ባውራው ገበሬ ባዝመራው
ንብን አይተህ ተገዛ ብሎዋል እግዜር
ንካ ያለው አይቀርም
ንዳማ ቢአጭዱት ክምር አይሞላም
ንጉሱ በድንኳናቸው እኔ በጎጆዬ
ንጉሱ በድንኳናቸው እኔ በጎጆዬ ንጉስ ነን አለ ድሀ
ንገስ ቢሉት ሳልዋጋ አልነግስ አለ
ንጉስ ለብያኔ አቡን ለኩነኔ
ንጉስ በመንግስቱ እግዜር በመለኮቱ ጎልማሳ በሚስቱ
ንጉስ በመንግስቱ ጎልማሳ በሚስቱ አምላክ ባምላክነቱ
ንጉስ በግንቡ ይታማል
ንጉስ በግንቡ ገበሬ በርስቱ ቢገቡባቸው ቀናተኞች ናቸው
ንጉስ ከግንቡ ውጭ ይታማል

ንጉስ በዘውዱ ድሀ ባመዱ
ንጉስ ቢቆጣቀስ ብለህ ውጣ
ንጉስ ሲቆጡ ቀስ ብላችሁ ውጡ
ንጉሱ ቢሞቱ ከማን ይሟገቱ
ንጉስ ቢያተርፍ ሁሉ ይተርፍ
ንጉስ ሲሞት ግንቡን ብልህ ሲሞት ልቡን
ንጉስ አንጋሹን ቤተክርስቲያን ቀዳሹን
ንጉስ አይከሰስ ሰማይ አይታረስ
ንጉስ አይከሰስ ሰማይ አይታረስ አባት አይወቀስ
ንጉሱ ከሸመው ማረሻ የሸመው
ንጉስ ከተነፈሰ አይን ከፈሰሰ
ንጉስ ከተነፈሰ ውሀ ከፈሰሰ
ንጉስ ይተክላል ንጉስ ይነቅላል
ንጉስ የቆረጠው እጅ ካለ ይቆጠራል
ንጉስ የፈረደበት መርከብ የተሰበረበት
ንጉስ የፈረደበት መርከብ የተሰበረበት (አንድ ነው)
ንጋትን ዶሮ ያውቃል ወፍ ያረጋግጣል
ንጋትን አውራ ዶሮ ያውቃል ወፍ ያረጋግጣል
ንጋትና ጥራት እያደር ይታያል
ንጉስ የሰቀለው አንበሳ የሰበረው
ንፉግ ለግሶ ቢሰጥ እጁ ይንቀጠቀጥ
ንጉስ የወደደው ዘመን የወለደው
ንጉስ ያላቸው ንቦች ማር ይበላሉ ንጉስ የሌላቸው ዝንቦች ጥንብን ይልሳሉ
ንጉስ ይሞግትልህ ንጉስ አይሞግትህ
ንግግር ሲበዛ ይጠፋል ማር ሲበዛ ያስተፋል
ንፍጥ ለባለቤቱ ቅቤ ነው
ኖረሽ አልጠቀምሽን ሞተሽ አለቀቅሽን
ኖሮ ኖሮ ከሞት ዞሮ ዞሮ ከቤት

## አ

አሁን ሊደርቅ ውሀ አደረገኝ ድሀ
አሁን እዩኝ እዩኝ ኋላ ደብቁኝ ደብቁኝ
አሁን የሚያልፍ ውሀ አደረገኝ ድሀ
አህያ ለማኝን አህያ ለማኝ ቀደመው
አህያ ለሰርዶ ባላገር ለመርዶ
አህያ ለሰርዶ ድሀ ለመርዶ
አህያ ለአህያ ጥርስ አይሳበርም
አህያ ለአህያ ቢራገጥ ጥርስ አይሳበር
አህያም እንደአባቱ ይፈርጥጥ ጅብም እንደአባቱ ይዘርጥጥ
አህያም የለኝ እርግጫም አልፈራ
አህያም የለኝ ከጅብ አልጣላ
አህያ ሞተች ተብሎ ጉዞ አይቀር
አህያ ሰባ ካልተበላ ምን ረባ
አህያ ሰባ ምን ረባ
አህያ ሰባ አልታረደም ምን ረባ
አህያ ሲረግጥህ መልሰህ ብትረግጠው አንተም አህያ ነህ
አህያ ሲጠግብ አምቦ ልጅ ሲጠግብ ሸንጎ

አህያ ሲጠግብ ከጅብ ይጫወታል
አህያ ሲግጥ ደብተራ ሲያላግጥ ይሞታል
አህያ ሲጭኑ ሶስት ሆኖ መንገድ ሲሄዱ ሁለት ሆኖ
አህያ ቀንድ ቢያወጣ ቁራ እንዴት በነጣ
አህያ በሞተች ባመቷ ኩርኩር
አህያ ቢሞት ጉዞ አይቀሩም ገዥ ቢጠፋ ተገዥ አይጠፋም
አህያ ቢረግጥህ መልሰህ ብትረግጠው አህያው አንተ እንጂ እሱ አይደለም
አህያ ተማሎ(ተማምሎ) ጅብን አወረደ
አህያ ታመዱ ሰው ተዘመዱ
አህያ አታመካኝብኝ ትበላኝ እንደሁ እንዲያው ብላኝ አለች
አህያ እንኳን በወለደች ታርፋለች
አህያ እንደምትታለብ ከላሞች ፊት (ለፊት) ትቅለበለብ
አህያ እጅብ ለቅሶ ሄደች
አህያና ጓያ በአምሳያ
አህያና ፋንድያ አራዳና ገበያ
አህያን ስጋ ጭነህ ጅብን ንዳ ብለህ እንጃ ይሆን ብለህ
አህያን በመንገድ ካህንን በመርገድ
አህያን በመንገድ ካህንን በማርገድ
አህያን ባመድ ካህንን በማእድ
አህያን አባትህ ማን ነው ቢሉት ፈረስ አጎቴ ነው አለ
አህያ ከመሞቷ መጎተቷ
አህያ የሌለው በቅሎ ያንኳሰሳል
አህያ የሌለው በቅሎ ይንቃል
አህያ የሌለው ቤቢ ፊያት ይንቃል
አህያ የተጫነችውን አትበላም
አህያ ያለእውቀት እጅብ ቤት ገባች
አህያ ወደ ሜዳ ጅብ ወደ ጓዳ
አህያውን ቢፈሩ መደላድሉን ሰበሩ
አህያውን ቢፈሩ ዳውላውን መቱ
አህያውን አመሰግን ብሎ ፈረሱን አዋረደ
አህያውን ፈርቶ ዳውላውን
አህያው ፈረሱን አህያ ነህ ብሎ ሰደበው
አህያ ፈሳች ብሎ ማን አፍንጫ ይይዛል
አህያ ፈሳች ተብሎ አፍንጫ አይያዝም
አህያ የሌለው በቅሎ ይንቃል
አለሌን በጉማሬ መንገድን በወሬ
አለ መባ ቤተ ክርስቲያን አትገባ
አለ መባ ቤተ ክርስቲያን አትግባ
አለመንገድ እየሄዱ ጅብን ነገረኛ ያደርጉታል አሉ
አለመኛ እንትን ቅቤ ቀቡኝ አለች
አለማረፍ የተርብ ቤት መቀስቀስ
አለማወቄ በላሁ ተጨንቄ
አለማወቄ ከዘመድ መራቄ
አለም ሀላፊ መልክ ረጋፊ
አለም ተልባ ነው ይሸትብሀል
አለም ተልባ ነው ይንሸራተታል
አለም አታላይ እንደ በቅሎ ኮብላይ
አለራቱ አይቆርስ አለረጀቱ አይወርስ

አለስራ አይበላ እንጀራ አለባል ቀጥ አይሰራ
አለ ሲል ባለቤት ሞተ ይላል ጎረቤት
አለቃ ለራሱ አይበቃ
አለቃ ለራሱም አልበቃ
አለቃ ቢለቅ ለሻለቃ ምንዝር ቢለቅ ላለቃ
አለቃ የሌለው ህዝብ አውራ የሌለው ንብ
አለቃ የሰጠው አጣሪ የሻጠው
አለቃ ያውቃል ድሀ ይጠይቃል
አለቅትና ድሀ ውሀ ለውሀ
አለቅን! አለቅን! አለች የእንትን ቅማል
አለ በለኝ ቀለቤን ሞተ በለኝ ከፈኔን
አለ በል ቀለቤን ሞተ በል ከፈኔን
አለባለቤቱ አይነድም እሳቱ
አለባል ሴት ወይዘሮ አለማንገቻ ከበሮ
አለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ
አለብልሀት ገደል መግባት አለ ጉልበት ውሀ መግባት
አለአቡን ቄስ አለዘውድ ንጉስ
አለአቡን ክህነት አለንጉስ ሹመት
አለ አባት ጎመን በአጓት
አለ አሽከር በቅሎ አለወንድማማች አምባ ጓሮ
አለ አቁማዳ መጫኛ አለ ከብት እረኛ
አለአቅማቸው እንዋጋ ቢሉ ጀግኖችን አስገደሉ
አለ አቻ ጋብቻ ቆይ ብቻ ቆይ ብቻ
አለአንድ የላት በዘነዘና ትነቀስ
አለ እህል አቁማዳውን ይሞላሉ አለ ዘር ይቀራሉ
አለት ለረገጠ ፍለጋ የለው ውሀ ለጠጣ ሽታ የለው
አለት ለረገጠ ፍለጋ የለው ውሀ ለጠጣ ሽታ የለውም
አለኩያ ጋብቻ ቆይ ብቻ
አለኩያ ጋብቻ ቆይ ብቻ ቆይ ብቻ
አለ ነገር ፒያሳን ስንሻገር
አለንጉስ ሰላም አለ ደመና ዝናብ የለም
አለንጉስ ዘውድ አለ ምሳር ግንድ የለም
አለንጉስ ዘመድ አለ ምሳር ግንድ የለም
አለንጋ ለፈረስ ጅራፍ ለሰነፍ
አለንጋ እስኪመጣ በክርን ያዝግሙብኝ
አለንጋ እስኪገዙ በክርን ይተክዙ
አለኝ ብሎ ከማፈር የለኝም ብሎ መድፈር
አለኝ እንጂ ነበረኝ አይጠቅምም
አለ ወንድም ጋሻ አለ ድግር እርሻ
አለዋንጫ አይሰማት አለቀንጠፋ አይሰባት
አለዋዛው ቅቤም አያወዛ
አለዋዛው ዋዛ ማቄን ትቀጂአለሽ
አለዋዛው ዋዛ ቅቤም አያወዛ
አለው አለውና ሳይመታው ቀረ
አለዳኛ ሙግት አለገመድ እክት
አለዳኛ ቀጠሮ አለቅቤ ዶሮ
አለዳኛ አይከሱ አለጥርስ አይነክሱ
አለዳኛ አይካሱ አለጥርስ አይነክሱ

አለጉልበት ሰኮና አለራስ ጉተና
አለ ድሀ ዘውድ አለ ገበሬ ማእድ
አለ ድሀ ዘውድ አለ ገበሬ ማእድ አይገኝም
አለጨለማ ፍራት አለዘመድ ኩራት
አለፊ በዋዛ ልብ ሳልገዛ
አለፊ በዋዛ ልብን ሳልገዛ
አለፉቱ አይቀርሱ አለረጃቱ አይወርሱ
አሉ ባለ እዳ አዎን ባለ ሜዳ
አሉ ባሉ እዳ አዎን ባሉ ሜዳ
አሉባልተኛ ሌት ተቀን አይተኛ
አሉ ብለህ ካላሉህ አትገኝ
አሉ ብሎ የተረታ መሀል አገዳውን የተመታ
አሉን ያህል ነገር ማሉን ያህል ምስክር
አላህ ወይ ውረድ ወይ ፍረድ
አላርፍ ያለች ጣት አር ትጠነቁላለች
አላርፍ ያለች ጣት አር ጠንቁላ መጣች
አላርፍ ያለች ጣት አር ጠንቁላ ትወጣለች
አላርፍ ያለች ጣት አር ጠንቁላ ወጣች
አላርፍ ያለች ጣት ክሰ ተመሰረተባት
አላርፍ ያለች ጊደር ጅቦች ሰፈር ታነጅባለች
አላርፍ ያለ ውሻ ላፉ ሊጥ ለጀርባው ልጥ አያጣም
አላሸከር በቅሎ አለወንድም አምባ ጓሮ
አላቂማዳ መጨኛ አለከብት እረኛ
አላቅሙ ጥሬ መቃሙ
አላቻ ጋብቻ ቆይ ብቻ ቆይ ብቻ
አላባት ቢዛቁን ይባክን
አላባት ነገር ዝንጀሮን ከባህር አሳን ከገደል
አላባት ጎመን በአጓት
አላባት ጀሮ በጡጫ
አላንኮበር ሾላ ሜዳ አይገኝም
አላንድ የላት ጥርስ በዘነዘና ትነቀሰ
አላዋቂ ለባሽ ልብስ አበላሸ
አላዋቂ ሳሚ ንፍጥ ይለቀልቃል
አላዋቂ አጉራሽ አፍ ያበላሻል
አላዋቂ አጉራሽ አፍ ያበላሸ
አላዋቂ ካረደው አዋቂ ያወራረደው
አላዋቂ ካረዳው አዋቂ ያወራረደው
አላዋቂ ዎርማፕ እድፍ ያወጣል
አላውቅም አስገድሎ አያውቅም
አላየናት እንዲያው ገበያ ናት
አላጋጭ አልማጭ
አላጋጭ ገበሬ ይሞታል በሰኔ
አሌ ብሎ የተረታ መሀል አገዳውን የተመታ
አልሞት ባይ ተጋዳይ
አልሰሜን ግባ በለው
አልሰሚ የናቱን ተዝካር ይበላል
አልበላ አልጠጣ ጎንደር ሂዶ ቀረ እንደወጣ
አልቀባም ብትል ትመሰክር

አልቀትና ድሀ ውሀ ለውሀ
አልሸሹም ዘወር አሉ
አልጠግብ ባይ ሆዱ አይሞላም
አልነገርኩሽም ወይ ባጥር ተንጠልጥዬ ውሻ በቀደደው ጅብ ይገባል ብዬ
አልነገርኩሽም ወይ ባጥር ተንጠልጥዬ ትግሬ ውሸማ እንጂ ባል አይሆንም ብዬ
አልጋ ቢያብር ለሆቴል ይጠቅማል
አልጋው ሲገኝ ባሉ አይገኝ
አልጠግብ ባይ ሲተፋ ያድራል
አመሌ አወጣኝ ከማህበሬ
አመልህ በጥፊ ይበልህ
አመልህን በጉያ ስንቅህን በአህያ
አመልህ በጉያ ስንቅህ በአህያ
አመል ላይቀር ቅጣት ሞት ላይቀር ፍራት
አመል ቤት አይጠብቅ
አመልና ጅራት ከወደኋላ ነው
አመልና ጅራት በስተኋላ ይበቅላል
አመል ያላት አገልጋይ ከእመቤቷ እኩል ትቀባለች
አመል ያስወጣል ከመሀል
አመል ያገባል ከመሀል
አመራር ያጣ ትግል ተቀባይ ያጣ ድል
አመስጋኝ አማሳኝ
አመት አርሶ አያጎርስ አመት ፈትላ አትለብስ
አመት አስቦ ለልደት
አመት የማያበላ አመት ያጣላ
አመት ዘመን መክሳት መመንመን
አመንዝራ ስታረጅ አቃጣሪ ትሆናለች
አመንዝራ ካሏት ብትቆርብም አያምኗት
አመካከት ዝንጀሮን ተመልከት
አመድ በዱቄት ሲስቅ ልቡ በንፋስ ውልቅ
አመድ በዱቄት ይስቃል
አመድ ባለበት በስመአብ ማለት የተኛ ጋኔን መቀስቀስ ነው
አመድ ያጠለቀው ጉልቻ የላቀው
አመጸኛ ሎሌህን በሰው ፊት አትዘዘው
አሙኝ ብለህ ካሙህ አትገኝ
አማቱን ምታ ቢለው ሚስቱን በየት አልፌ አለ
አማትና ምራት ሳይስማሙ መሬት
አማትና ምራት እሳትና እራት ሳይስማሙ መሬት
አማቻችን አፈኛ ቢመለስ ወደኛ ወይ እኛ እንሁን አሳረኛ
አማቻችን አፈኛ ይመለስ ወደኛ
አማች የበላው እሳት የበላው
አማችና ቂጥ ትርፍ ነው
አማችና ጋሻ ካልሰጎዱት አይወድም
አማጭ ለልማዱ የበቅሎ ክበድ የሀር ገመድ አለኝ ይላል
አማጭ ረማጭ
አምላክ የተቆጣው በረዶ ከድንጋይ ላይ ወርዶ
አምራለሁ ብላ ተኩላ አይኗን አጠፋች ቸኩላ
አምሳ ሆነው አምሳ በግ ፈጁ
አምሳ ሎሚ ለአንድ ሸክም ነው ለአምሳ ጌጥ ነው

አምሳ ሎሚ ላምሳ ሰው ጌጡ ነው ላንድ ሰው ሸክሙ ነው
አምሳ ሰማ ጅሮ ገማ
አምሳ ዳቦ ከመላስ አንዱን መቅመስ
አምሳ ዳቦ ከመላስ አንዱን መጉረስ
አምሳ ዳቦ ከመላስ አንዱን መግመጥ
አምባ ያለው ፈሳሽ ወንዝ ያለው መላሽ
አምነው የሞገቱት አያስረታ ዝግ ብለው የታጠቁት አይፈታ
አምና ላሞቹ ዘንድሮ ጥጆቹ
አምና እረኞቹ ዘንድሮ በጎቹ
አምኖ ለሚሟገት ረቺ የለው ብቻውን ለሚሮጥ ቀዳሚ የለው
አምኖ ይሟገቷል እጠገቡበት ይሸምቷል
አሞራ ሲበሉ ስሙን ጅግራ ይሉ
አሞራ በበላ ጥፍጥሬን በዱላ
አሞራ በዛፍ ውርርድ በጫፍ
አሞራና ቅል ተጋቡ አሞራው በረረ ቅሉም ተሰበረ
አረመኔ በጭካኔ ሙግት በውጣኔ
አረምና ጥላት ሳይዘሩት ይበቅላል
አረጉን ሲሰቡት ዛፍ ይወዛወዛል
አራስ የእጅዋን ድመት የልጅዋን
አራስ የእጅዋን ድመት የልጅዋን ትበላለች
አራት ቁና አጃ ቢጠፋባት ሁለት ቁና ስንዴ ይዛ ከጠንቋይ ቤት
አር ሲቀብጥ እንግላል ይወድቃል
አርሶ ያልበላ ሆነ ነሁላላ
አርሶ ያልጠገበ ነግዶ
አር ቢሰበሰብ ግድግዳ ይሆናል
አርባ አመት ቢቀመጥ በደል አያረጅም
አርባ አመት ከሆነው ጋር ምክር ከሰላሳ አመት ልጅ ጋር መክት
አር የነካች ጣት ገማች ተብላ ተቆርጣ አትጣልም
አርጂ ጥኑ ነው
አሮጌ መጥረጊያ ቤት አያጠራም
አሮጌ ማሳ ያረሰ ለእንጀራ ልጅ ያጎረሰ
አሮጌ ውሻ በከንቱ አይጮህም
አሰሩት ተበተቡት በኋላ ሊፈቱት
አሰተኛ ሲናገር ይታወቃል በሶ ሲበሉት ያንቃል
አሰት ሲናገሩ ውቃቢ ይርቃል
አሰት አያድንም መራቆት መልክ አያሳምርም
አሰትና እውነት የቱ ይረታ ጠዋት
አሰድ ያየውን አይሰድ
አሳ ለወጋሪ ነገር ለጀማሪ
አሳን መብላት በብልሀት
አሳ መብላት በብልሀት ነው
አሳምር ያሉት አያክፉ ጠብቅ ያሉት አያጥፉ
አሳ ጎርጓሪ ዘንዶ ያወጣል
አሳ ብለምነው ዘንዶ ዝናም ብለምነው በረዶ
አሳብ የለሽ ወጧ ጣፋጭ ነው
አሳ በልቶ ውሀ መጠጣት መልሶ ከነበረው ማግባት
አሳ በወንዙ ይታረዳል የጨዋ ልጅ በቤቱ ይፈርዳል
አሳ የጌቶች ምሳ የገረድ አበሳ

አሳን መብላት በብልሀት
አሳ ያለበት ባህር እውር ያለበት ደብር ሳይበጠበጥ አያድር
አሳ ከውሀ ወጥተህ ኑር ቢሉት ምነው የምልሰው ድንጋይ የምቀመው አሸዋ ነው አለ
አሳ ብለምነው ዘንዶ ዝናም ብለምነው በረዶ
አሳ አሳን ይበላዋል ወንድም ወንድሙን ይጠላዋል
አሳ ግማት ካናቱ
አሳ ጎርጓሪ ዘንዶ ያወጣል የሰው ፈላጊ ራሱን ያጣል
አሳውም እንዳያልቅ ውሀውም እንዳይደርቅ
አሳው እንዳይሞት ውሀው እንዳይደርቅ አድርጎ ነው እርቅ
አሳማ በበላ ጉፍጠራን በዱላ
አሳም በበላ ጎፍናኔን በዱላ
አሳሳች ከላይ ሲሉት ከታች
አሳይቶ መሳሳት የሰጭ ቅሌት
አሳይቶ መሳሳት የሻጭ ቅሌት
አሳቀኝ ገንፎ ከምሳዬ ተርፎ
አሳቀኝ ገንፎ ከእራቴ ተርፎ
አሳዳጊ ለበደለው ለክፋት ያደለው
አሳዳጊ ለበደለው ፊትህን አትስጠው
አሳፋሪ ሎሌህን እሰው ፊት አትላከው
አሳፋሪ ሎሌህን እሰው ፊት አትዘዘው
አስራ ሁለት ሆኖ አንድ ነብር ፈጃት
አስር የሚመጥ አንድም አያገኝ
አስብ ያለው የመገዘዝ አይጥ ምን ትበላለች እያለ እንቅልፍ ያጣል
አስብ ሁለቴ ከመናገር አንዴ
አስቀድሞ ማመስገን ለሀሜት ያስቸግራል
አስተማሪ ችጋር ጠሪ
አስተካክሎ ይቀደል ለእግዚአብሄር ብሎ ይፈርዷል
አስጨነቀኝ ገንፎ ከራቴ ተርፎ
አስቸጋሪ እንግዳ ተዘቅዝቆ ይተኛል
አስፍቶ ከማረስ ከተቀላቢው መቀነስ
አስፍቶ ከማረስ ከበላተኛው መቀነስ
አሽከሩን አይዳኝ በገናውን አይቃኝ
አሽከር ባንደበቱ ውሻ በጅራቱ
አሽከር ባንደበቱ ውሻ በጅራቱ ይታወቃል
አሾክሻኪ አነካኪ
አቀማመጥ ያላወቀ ከባልና ሚስት መካከል ይቀመጣል
አቀበት ያደክማል እርሻ ያዳግማል
አቀፈ አዘለ ለባለቤቱ ያም ሸህም ነው
አቀፈ አዘለ ለባለቤቱ ያም ይህም ሸህም ነው
አቋራጭ ነው ብለህ በገደል አትግባ
አቃቢ በተልባ በበላች ገበዙን ተጋረፈው
አቃቢ ኮሶ ቢጠጡ ቀሰ-ገበዙን አሻራቸው
አቅለው ብለው ቆለለው
አቅሙን አያውቅ ቶሎ አይታረቅ
አበልጂ አትቁም ከደጂ
አበበን ጥራ ቢሉት እራሱ መጣ
አበቢላ የመስከረም ጠላ
አበባ እያገርህ ግባ

አበሻና ጉንዳን ክፋቱ እንጂ ደግነቱ አይወራም
አበሻ አይቀድም ወይ አያስቀድም
አበድረኝ አይማረኝ ተዋሰኝ ግዝት ነኝ
አበድረኝ አይማረኝ ተዋሰኝ ግዝት ይሁነኝ
አበጀሁ ያላሰብኩት ጀሮዬ ደነቀረ
አቡን ቄስ ናቸው ወይ ቢሉት ተርፎዋቸው ይናኛሉ አለ
አቡጊዳ የተማረ እዳ
አቡክቶ አሳብ
አባ ላዩ ዳባ ውስጡ ደባ
አባ በሌሉበት ተዝካር ተበላ
አባ ቢዘሉ እስከ ንፍሮ
አባ ከበሉ እመን አነሳቸው
አባም ሰው ሆኑና ፋኖ ገደላቸው
አባሪ ተነባባሪ
አባቱ ሲላጨው እናቱም ስታቅፈው
አባቱ ዳኛ ልጁ ተጫዋች
አባቱን አያውቅ አያቱን ናፈቀ
አባቱ ዳኛ ልጁ ቀማኛ
አባቱን ሳይመስል የተወለደ ልጅ ከጎረቤት ያሳማል
አባቱን አያቅ አያቱን ናፈቀ
አባቱን የጠላ የሰው አባት ይሰድባል
አባቱን ያላወቀ አያቱን ናፈቀ
አባቱ ያልበላውን ኑግ ልጁ አማረው ቅባ ኑግ
አባት ሳለ አጊጥ ጀምበር ሳለ ሩጥ
አባቱን የጠላ የሰው አባት ይሰድባል
አባቱ ያልበላውን ኑግ ልጁ አማረው
አባት ያበጀው ለልጅ ይበጀው
አባቱን ረስቶ ላማቱ ይነጭ አማቱን ገድሎ እናቱን ያስፈጭ
አባቱን ረስቶ ላማቱ ይነጭ አማቱን ጋርዶ እናቱን ያስፈጭ
አባቱን ገድሎ ላማቱ ይነጭ አማቱን ገድሎ እናቱን ያስፈጭ
አባቱን ገድሎ ላማቱ ይነጭ አማቱን ጋርዶ እናቱን ያስፈጭ
አባቴ ሲሞት እናቴን ያገባ ሁሉ አባቴ ነው
አባቴ ትንሽ ነው ብልቴ ትልቅ ነው የሚል የለም
አባት ሲታማ ልጅ አይስማ
አባት አይከሰስ ሰማይ አይታረስ ውሀ አይጠበስ
አባት በነውሩ ይከሰሳል ሰማይ በመብረቅ ይታረሳል ውሀ በምንቸት ይጠበሳል
አባት ካነሰው ምግባር ያነሰው
አባት የሌለው ልጅ መዝጊያ የሌለው ደጅ
አባት የያዘውን ልጅ ይወርሳል እጅ የያዘውን አፍ ይጎርሳል
አባት ያጠፋው ልጁን ያለፋው
አባት ያቆየው ለልጅ ይበጀው
አባት ጨርቋን በጎረሰ የልጁ ጥርስ አጠረሰ
አባትና ጋሻ ምስክርም አያሻ
አባትና ጋሻ በውጭ ያስታውቃል
አባትና ጋሻ አይሸሸግም
አባድር ጾም አታሳድር
አባያ ቢቀና ቤት ያቀና
አባያ ከሰው ሁሉ ፊት ይተኛል

አባይ ለለቱ ደስ ማሰኘቱ
አባይ ማደሪያ የለው ግንድ ይዞ ይዞራል
አባይን በጭልፋ
አባይን ያላየ ሄዶ ይይ
አባይን ያላዩ ቡዳ ነው
አባይ አንተ አየኸኝ ከደረት እኔ ያየሁህ ከጉልበት
አባይን ያላየ ሄዶ ማይት ይችላል
አባይን ያላየ ምንጭ አይቶ ይስቃል
አባይን ያላየ ምንጭ አይቶ ይደነቃል
አባይን ያላየ ምንጭ ያመሰግናል
አባይ ማደሪያውን ሳያውቅ ግንድ ተሸክሞ ይዞራል
አባይ ማደሪያ የለውም ግንድ ይዞ ይዞራል
አባይ ማደሪያ የለው ግንድ ይዞ ይዞራል
አባይ በቃሉ ያስታውቃል በጇ ሲበላ ይታነቃል
አባይ ቢሞላ ተሻገር በመላ
አባይ ነፍስ አስገዳይ
አባይ አንተ አየሀኝ ከደረት እኔም አየሁህ ከጉልበት
አባይ አንተ አየሀኝ ከደረት እኔ ያየሁህ ከጉልበት
አባይ ጠንቋይ ቤት ያስፈታል
አባት ጭብጦዬን ከወሰደብኝ ወዲያ አላምነውም
አባይና ስንቅ እያደር ይቀላል
አብ ሲነካ ወልድ ይነካ
አብሎ መብላት በእሳት
አብስሎ መብላት በእሳት
አብረህ ብላ ቢሉት ቆሞ አጉርሱኝ አለ
አብረው የበሉ አብረው ይሙቱ
አብረው የተጠመዱ አብረው ይፈቱ
አብራ የተኛችው እያለች በቀዳዳ ያየችው አረገዘች
አብሮ መብላት ያናንቃል
አብሮ ማደግ ያናንቃል
አብሮ ማደግ ያሳስቃል
አብሮ የበላን ቅዱስ ዮሀንስ አይሸረውም
አብን ያየ ወልድን አየ
አብዝቶ ከማረስ ከተቀላቢ መቀነስ
አቦን አይጠምቅ ወር አይጾድቅ የለም
አቦን አይጠምቅ ፍልሰታን አይጥድ የለም
አተር መዝራት አቦ በብልሀት
አተር ቢጎድል ሽንብራ ይበረክትልናል
አተርፍ ባይ አጉዳይ
አተርፍ ባይ አጉዳይ አልሞት ባይ ተጋዳይ
አታላይ ለጊዜው ያመልጣል በኋላ ይሰምጣል
አታላይ ጉድባ ዘላይ
አታላይ ባለሟል ባቄላ አሽቶ ይበላል
አታላይን ማታለል አጠፌታ ያለው ደስታ ነው
አታላይ ወደ ታች ሲሉት ወደ ላይ
አታላይ እታች ሲሉት እላይ
አታማርጭው አንዱን አምጭው
አታምጣው ሲለው ቀለለው አሉ

አታርፍ አትሰራ አትጾም አትበላ
አታስለምዳቸው አትከልክላቸው
አታበድር እንዳትቸገር
አታበድር ካበደርክም አታስቸግር
አታንቀላፋ ነቅተህ ተኛ ይህ ሁሉ መንገደኛ
አታግባና የሰው አጥር ዝለል
አታወላውል እንዳትቀር ከመሀል
አትሩጥ አንጋጥ
አትንገር ብየ ብነግረው እንዳትነግር ብሎ ነገረው
አትክልት በውሀ ይለመልማል እህል ከፈጬት ይልማል
አትማታ በበትር ተከራከር ባጤ ስር
አትረፍ ያለው በሬ ቆዳው ከበሮ ይሆናል
አትቁም ያሉት ለማኝ ከሰጡት አንድ ነው
አትቁም ያሉት ለማኝ ከሰጡት እኩል ነው
አትትረፊ ያላት ወፍ በጥቅምት ትሞታለች
አትናገረው ምሰህ ቅበረው
አትኩራ ገብስ ጎመን ባወጣው ነፍስ
አትክልት በውሀ ይለመልማል እህል ከፈጬት ይልማል
አትዋል ይዋሉብህ አትምከር ይምከሩብህ
አትዋል ይዋሉብህ አትምከር ይምከሩብህ እንዲያው ያወጣህል ቅን ከሆነ ልብህ
አትዋልባቸው ይዋሉብህ አትምከርባቸው ይምከሩብህ
አትግደርደሪ ጠምሽን እንዳታድሪ
አትጥላኝ በወሬ ሳይጣራ ነገሬ
አትጥላኝ በወሬ ሳታጣራ ነገሬ
አትፍራ ጋብዘኝ አትናገር ሸኘኝ
አትሩጥ አንጋጥ
አነሰ ሲሉት ተቀነሰ
አነሰ ሲሉት ተቀነሰ
አነክስ ብዬ በቅሎ ገዛሁ አይኔ ጠፋ ብዬ መሪ አበጀሁ ያላሰብሁት ጀሮዬ ደነቀረ
አነር ጉድባ መዝለል ስላቃተው ከናቱ ከነብር ተለየ
አነሰ ሲሉት ተቆረሰ
አነሰ ስትዪ ሽሮ ስትጨምሪ ወፈረ ስትዪ ወሀ ስትጨምሪ ሞላ ገነፈለ ወዴት ታማስዪ
አነጋገሩ ባህታዊ አወሳሰዱ እንደነአባይ
አነጋገራችን እንደ ጠባያችን
አነጋገር ቢያምር አሟሟት ይከፋል
አነጋገር አያውቅ ምርቃት ያበዛል
አንቃ ለራሱ አይበቃ
አንበሳ ላንበሳ ቢያገሳ ሞቱ ለኮሳሳ
አንበሳ ሲያረጅ የጅብ መጫወቻ ይሆናል
አንበሳ ሲያረጅ የዝንብ መጫወቻ ይሆናል
አንበሳ ሳይገድሉ ቆዳውን ያስማማሉ
አንበሳ የሰበረው ለጅብ ይተርፈው
አንበሳ የሰበረው ለጅብ ይተርፋል
አንበጣና ፌንጣ ሰንጠረዥና ገበታ
አንቃ ለአንቃ ቢደጋገፍ ተያይዞ ዘፍ
አንተ ሰው ና ግንቡን ጣሰው
አንተ ቀውላላ መኖህ ባቄላ
አንተ አስበህል ስላሴ ያውቁልሀል

አንተ አብጀው አስቤም አልፈጀው
አንተ አብጀው ጌትዬ አንተ አብጀው እኔማ አስቤም አልፈጀው
አንተ ውለታ ቀጣሪ ቢለው አንተ ውለታ አስቀጣሪ አለው
አንተ ውለታ ቀጣሪ ቢለው አንተ አስቀጣሪ አለው
አንተ ግፋኝ ከላይ እኔ እውድቃለሁ ከስጋ ላይ
አንተ ግፋኝ እስጋ ላይ እኔም እውድቃለሁ ከላይ
አንተም ሌባ እኔም ሌባ ምን ያጣላናል በሰው ገለባ
አንተም አራዳ እኔም አራዳ ምን ያጣላናል በሰው በረንዳ
አንተን ብዬ መጣሁ አንተን አጣሁ
አንቱ ትተረጉሙ አንቱ ትደረግሙ
አንቱ ትራገሙ አንቱ ትደረግሙ
አንቺ ምን ቸገረሽ ሁለት አባት አለሽ አንዱ ቢሞትብሽ ባንዱ ትምያለሽ
አንቺ ምን አለብሽ ሁለት ባል አለሽ አንዱ ቢሞትብሽ ባንዱ ታለቅሻለሽ
አንቺ ምን አለብሽ ሁለት ባል አለሽ አንዱ ቢሞትብሽ ባንዱ ትምያለሽ
አንቺ ምናለብሽ ሁለት አባት አለሽ አንዱ ቢሞትብሽ ባንዱ ትምያለሽ
አንችም አበዛሽው እርጎውን በቅቤ ፈትፍተሽ በላሽው
አንቺ ምን አለብሽ ሁለት አባት አለሽ አንዱ ቢሞትብሽ ባንዱ ትምያለሽ
አንቺም ማመን ጉም መዝገን
አንተን ያመነ ጉም የዘገነ
አንተን ያመነ ሁሉ ዳነ
አንችው ታመጭው አንችው ታሮጭው
አንቺ ክምር አለሁ ብለሻል ተበልተሽ አልቀሻል
አንቺን ቢጠሉሽ አጥመዝምዘው ጣሉሽ አለቻት ትኋን ለቁንጫ
አንቺማ ታቦኪያለሽ ውሻ ይደፋብሻል
አንቺን ጣመሽ እንጂ እኛንስ አስረጀን
አንቺው ሲሳይ የተጫንሽው ሲሳይ አለ ጅብ
አንቺ ስትጎተቺ አህያ ቀንድ ታወጣለች
አንካሳ በልቡ ኢየሩሳሌም አሳቡ
አንካሳ ያለው ደብር አዞ ያለው ባህር ሳይበጠበጥም አያድር
አንካሳን ማገም ድንጋይ መቆርጠም
አንደበቱ ከጸሎት እጁ ከምጽዋት (ያልተለየ)
አንደኛው ልብ አብርድ ሁለተኛው ልብ አንድድ ሶስተኛው ነገር ቀስቅስ አራተኛው ጎራዴ ምዘዝ
አንደበቱ ሰውን ከመበደል እጁ ሰውን ከመግደል
አንድ አይን ያለው ባፈር አይጫወትም
አንድ እንጀራ የጣለው አምስት እንጀራ አያነሳውም
አንድ በሬ ሰቦ  አንድ ሰው አስቦ
አንድ እግር ያለው በከና አይማታም
አንድ ጥርስ ያላት በዘነዘና ልትነቀስ አማራት
አንዱ ሊበላ አንዱ ያገበግባል
አንዱ ልብ መካሪ አንዱ ቃል ተናጋሪ
አንዱ ሲሻር አንዱ ይሾማል
አንዱ ሲናገር ያፈዝ አንዱ ሲናገር ያደነዝዝ
አንዱ ሲናገር ያፈዝ አንዲ ሲናገር ያደነግዝ
አንዱ ባንዱ ሲስቅ ጀምበር ጥልቅ
አንዱን ሳይዘው ደረሰ ጊዜው
አንዱን ጥላ አንዱን አንጠልጥላ
አንዳንድ ጊዜም በዋልድባ ይዘፈናል
አንዴ ያበደረ ሁሌ ተከበረ

አንድ ሎሌ ለሁለት ጌታ አይገዛም
አንድ ምስክር አያስደነግጥ አንድ አይን አያስረግጥ
አንድ በሬ ስቦ አንድ ሰው አሰቦ
አንድ በቀል አብሮ በቀል
አንድ ሰኔ የተከለው ካመት አተረፈው
አንዳ ሰኔ የገደለውን ሶስት ሰኔ አያድነውም
አንድ ሰኔ የጣለውን አምስት ሰኔ አያድነውም
አንድ ሲናገር ሁሉ ይሰማል ሁሉ ሲናገር ማን ይሰማል
አንድ ቀን ቢሳሳቱ አመት ይጸጸቱ
አንድ ቀን ቢሳሳቱ ዘላለም ይጸጸቱ
አንድ ቅማል ሱሪ ያስፈታል
አንድ አመት እንዳይማሩ ሰባት አመት ያፍሩ
አንድ አመት እንዳይማሩ ሰባት አመት ይደነቁሩ
አንድ አመት እንዳይማሩ እድሜ ልክ ይደነቁሩ
አንድ አመት ሰርተት አንድ አመት ሸርተት
አንድ አመት ሰርተት አንድ አመት ከርተት
አንድ አመት በደመወዝ አንድ አመት በወዝ
አንድ አመት ወር ድንጋይ ጠጠር (አይሆንም)
አንድ አይነድ አንድ አይፈርድ
አንድ አይና በእንጨት አይጫወትም
አንድ ያላት እንቅልፍ የላት
አንድ አይና ባፈር አይጫወትም
አንድ አይና በግ ሄደች በአንድ አይኗ እንቅልፏን ትፈጃለች በአንድ አይኗ ጊዜን ትጠብቃለች
አንድ እግረኛ ያወራውን አንድ ፈረሰኛ አይመልሰውም
አንድ ወሬኛ አገር ይፈታል አንድ ቅማል ሱሪ ያስፈታል
አንድ ወናፍ ሁለት አፍ
አንድ ያላት እንቅልፍ የላት
አንድ ጣት በቆማጣ ቤት ብርቅ ናት
አንድነት ያገባል ገነት
አንድ ፋሲል ነበረ እሱም ተመተረ
አንድም ምረጥ አንድም ቁረጥ
አንገት ለምን ተሰራ ዞሮ ለማየት
አንገት ደፊ አገር አጥፊ
አንገቷን ደግፈው ቢያዘፍኗት ያለች መሰላት
አንጋጣጭ ዱላ ዋጭ
አንድ ግንድ ለሺ.ህ አይከብድም
አንጣሪያ ላንጣሪያ ቢደጋገፍ ተያይዞ ዘፍ
አንድ ጣት ቁንጫ አይገድልም
አከፋፈል ለእለት አሳሳብ ለጥንት
አከፋፈል ለእለት አሰባሰብ ለጥንት
አካሄዱን አይተህ ጭብጠውን ቀማው
አካሄዱ እባበኛ አኮራኮሩ ድንገተኛ
አካል የወለደው ዘመድ የወደደው
አካልና ክብት ሚስትና ቁርበት
አካልና አምሳል
አክንባሎና እዳ ተሸራርፎ ያልቃል
አወላለድ ያለው አከፋፈል አይቸግረው
አውቀሽ ከተደፋሽ ቢረግጡሽ አይክፋሽ

አውቀሽ ከተደፋሽ ቶሎ ተነሽ
አወቅሽ አወቅሽ ቢሏት መጽሀፍ አጠበች
አወቅሽ አወቅሽ ቢሏት የባሏን መጽሀፍ አጠበች
አወቅሽ አወቅሽ ቢሏት ቦይፍሬንድ አበዛች
አውቆ የተኛን ቢቀሰቅሱት አይሰማም
አኘከህ አኘከህ ወደዘመድህ ዋጥ
አወይ ልጅ በማን እጅ አለች ቀማጣ
አወይ ብልሀት ለንጉስ መገዛት
አዋቂ ሲበዛ በሽተኛ ይሞታል
አዋቂ ሲበዛ አስታራቂ ይሞታል
አዋቂ ይርዳኝ ሽንጎ ይፍረደኝ
አዋቂ አስታራቂ
አዋጅ ቢነግሩ ልዩ ነው ምክሩ
አዋጅ ቢያስነግሩ ልዩ ነው ምክሩ
አውራ ዶሮን አውራ መንገድ ላይ መኪና ገጨው
አውራ የሌለው ንብ አለቃ የሌለው ህዝብ
አውሬ ከዋሻ በሬ ከርሻ
አውቀው በድፍረት ሳያውቁ በስህተት
አውቆ መተው ነገሬን ከተተው
አውቆ መተው ለእግዜር ይመቸው
አውቆ የሚያጠፋ ኑሮው ምን ይከፋ
አውቆ የተኛን ቢጠሩ አይሰማም
አውድማ እንደ ንፋስ አገር እንደ ንጉስ
አውጣን አውርደን (ነው)
አዎን ማለት መረታት አለመመከት መመታት
አዎን ባይ እዳ ከፋይ አሉ ባይ ሞት ተቀባይ
አዎን ባይ እዳ ከፋይ አሌ ባይ ሞት ተቀባይ
አዎን ብለህ ተሟገት ከጠገበበት ሸንት
አዎን ብለህ ተሟገት ከተጠገበ ሽምት
አዎን ብሎ የተረታ መሀል አገዳውን የተመታ
አዎን ያለች ምላስ እናት የሌላት አራስ
አዎን ያለ አያሟግቱ እሺ ያለን አይመቱ
አዘለም አቀፈም ተሸከመ ነው
አዘለም አቀፈም ያው ተሸከመ ነው
አዘለም አሟቀለም ያው ተሸከመ ነው
አዘኑ ላይለቅህ ድግሱ አያምልጥህ
አዘኑ ላይለቅህ ድግሱ አይራቅህ
አዘንጊ ወጥ ከእንጀራ ይተርፋል
አዘዞ አንድም ተናዞ አንድም ስንቅን ይዞ
አዘዞ አንድም ተናዞ አንድም ስንቅ ይዞ
አዙሮ ላየው ብላም ነገር ነው
አዛኝ ቅቤ አንጓች
አዛውንት ዳዊት ሲደግም እንጂ ሲያስፈራራ ተሰምቶም አያውቅ
አዛዩን ነካሽ
አዝኜ ባሳድረው ሰርቆኝ ሄደ
አዝመራ በቁንጥጫ ሰማይ በጡጫ
አዝነ ባቅፋት እንቅልፍ ወሰዳት
አዞ ሲውጥ ያለቅሳል

አዞ ያለው ባህር አንካሳ ያለው ደብር ሳይበጠበጥ ውሎ አያድር
አየሁ ያለ ጣጣ ያመጣል አላየሁም ያለ ከጣጣ ያመልጣል
አያያዙን አይቶ ገንዘብ አበደረው
አያያዙን አይቶ ጭብጦውን ቀማው
አያ ጅቦ ሳታመኻኝ ብላኝ
አያያዙን አይተህ ጭብጦውን በቲራ ብለህ ቀማው
አያ ተዋሰኝ ስትሄድ አሳንሰኝ
አያተርፍ አይነግድ አይተች አይፈርድ
አያ ጅቦ ሳታመሀኝ ብላኝ
አያርም አራሽ አያጥብ ለባሽ አይረታ ከሳሽ
አያርስ አይነግድ አይተች አይፈርድ
አያስብ ቀበኛ ተንኮለኛ
አያስገባ ኮሶ የት ደርሶ
አያስገባ ኮሶ የታባቱ ደርሶ
አያውቅ ቢዳኝ ከቤቱ ይናኝ
አያውቅ እንደኛ የበግ እረኛ
አያድሩበት ቤት አያምሻሹበት
አያድርስ የባል ቢስ አያቅፍ አያንተርስ
አያድን አግሬ ጎድን ያሰብራል
አያድን አግሬ ጎድን ያሰብር
አያድን ጋሻ ቂጥ ያስወጋ
አያገባት ገብታ አያወዛት ተቀብታ
አያጥብ ለባሽ አይረታ ከሳሽ
አያጥብ ለባሽ አይረታ ከሳሽ አያርም አራሽ
አዬ ሌላ ወዬ ሌላ
አዬ ጉዴን አታበላሽ ለባሰ ቀን ይሆናል
አዬ ጉድን አታበላሽ ለባሰ ቀን ይሆናል
አዬና ወዬን ምን አገናኘው
አይሆንም እንጂ ከሆነማ ከመጋዞ ይሻላል ጉልማ
አይ ልጅነት አይ ሞኝነት
አይመረው አይተኩሰው ውጠ ውጠ ጨረሰው
አይመጣምን ትተሽ ይመጣልን በያዝሽ
አይረቢትን አረቧት
አይሰጥ አዛኝ ከነፍስ ገዳይ አንድ ነው
አይበላ የለ አይጠጣ የለ
አይበላ የለ አይወጣ የለ
አይበላ ዳኛ በእግት ይመረር
አይበላ ዳኛ በሙግት ይመረር
አይቡ ዳኛ ቅቤው መልከኛ
አይቡን ሲያዩት አጓቱን ጨለጡት
አይቡን ሲያዩት አጓቱን ጠገቡት
አይቡን ሲያዩ አጓቱን ጨለጡ
አይብ ሲያድር አጥንት ይሆናል
አይብ ከአጓቱ ልጅ ከእናቱ
አይብ የጠላ ጎመን ይበላ
አይተህ ቁረስ ከጥርስህ እንዲደርስ
አይተፋሽ ማር ነሽ አይውጡሽ ምርቅ ነሽ
አይታ የማታውቀው የሰው ጃኖ ለብሳ ተመለሺ ቢኗት ወዴት ተመልሳ

አይታፈሩበት ቤት ገላጋይ አይሆንም
አይቶ አጣ ቤት ጎመን የተቀቀለ ለት ሲጨበጨብ ያድራል
አይቶ አጣ ጠምዶ ፈታ
አይችሉት ድንጋይ ቢሸከሙት ከፍ ብሎ ደረት ይመታል ዝቅ ብሎ እግር ይቆርጣል
አይችል ዳኛ በቤቱ ይናኝ
አይነ ደረቅ ሌባ ከነቃጭሉ ይገባ
አይነ ደረቅ መልሶ ልብ ያደርቅ
አይነጋ መስሏት በቋት አራች
አይነጋ መስሏት እቋት አራች
አይኔን ሲያመው ጥርሴን አታስቀጣው
አይኔን ሲያመው ጥርሴን አሳቀው
አይን ሁል ጊዜ ክታለቅስ አንድ ቀን ብቻ ታልቅስ
አይን ህመም ልግም ይወዳል
አይን ህመም ክሱት ነው የሆድ ህመም ስውር ነው
አይን ሲያይ ብረቱ ጆሮ ሲሰማ መስኮቱ
አይን አይቶ ልብ ይፈርዳል
አይን አይፈስ እርቅ አይፈርስ
አይን አፋር ልጃገረድ ከወንድሟ ታረግዛለች
አይን አፋር ልጃገረድ ከወንድሟ ትወልድ
አይን ከጥርኝ አፈር በቀር የሚያጠግባት የለም
አይንህና አገርህ አይጠግቡም
አይንህና አገርህ አይጠገቡም
አይን ካላዩበት ግንባር ነው
አይን የማያየው ልብ የማይስተው (እውነት አለ)
አይኗን ቢያጠፋት ቅንድቤን አደራ (አለች)
አይን ያጣ ጠምዶ የፈታ
አይዋስ ቢዋሰኝ ከባለዳው ባሰኝ
አይወጋ ብላቴና አይዘንብ ደመና
አይዋጋ ብላቴና አይዘንብ ደመና
አይዋጥ አይተፋ መላው የጠፋ
አይዞህ አይዞህ ማለት ከመውደቅ ያድናል
አይመጣምን ትተሽ ይመጣልን ያዥ
አይመጣምን ትተሽ ይመጣል ባሰብሽ
አይነስውር ቤት ፊልም መስራት ተጀመረ
አይነጋ መስሏት በቋት አራች
አይነጋ መስሏት ድመት ናይት ወጣች
አይኔን አታስቀው ጥርሴስ ልማዱ ነው
አይናፋር ልጃገረድ ከወንድሟ ታረግዛለች
አይነጋ መስሏት ቁርሷን ማታ በላች
አይ ሰው ሞት አነሰው አለች ዝንጀሮ
አይታ የማታውቀውን የሰው ጃኖ ለብሳ ተመለሽ ቢሏት ወዴት ተመልሳ
አይን ግጥጥ ጥርስ ፍጥጥ
አይንህን ያምሀል አንተ ገመምተኛ እንዳይቀረቁርህ ተው ተመለስ ተኛ
አይጥፍ ደብተራ ክንፍ የለው አሞራ
አያ ጅቦ ሳታመካኝ ብላኝ አለች አህያ
አይነጋ መስሏት ቁርስዋን ማታ በላች
አይጠቅም ጠላ ባልና ሚስት ያጣላ
አይጠቅም ጠላ ከጎረቤት ያጣላ

አይጥ ሹሩባ ተሰርታ ባለጊዜ ሆነች
አይጥ ለሞቷ የድመት አፍንጫን ታሽታለች
አይጥ ለሞቷ የድመት አፍንጫን ማሽተቷ
አይጥ በበላ ዳዋ ተመታ
አይጥ በበላ ዳዋን በዱላ
አይጥ በድመት አፍንጫ ወርዶ አህያ ታስሮ በሰርዶ
አይጥ በድመት አፍንጫ ወርዶ አህያ ታስሮ ከሰርዶ
አይጥ በጉድጓዱ ሰው በዘመዱ
አይጥ ነሽ እዩት ክንፌን ወፍ ነሽ እዩት ጥርሴን
አይጥ ወልዳ ወልዳ ከጅራቷ ሲደርስ ሲጥ አለች
አይጥ ወልዳ ወልዳ ጅራቷ ሲቀር ሲጥ
አይጥ ወልዳ ወልዳ ጅራቷ ደርሶ ሲጥ
አይጥ ወልዳ ወልዳ ዲቪ ደረሳቸው
አይጥ ወልዳ ወልዳ የድመት ሲሳይ አደረገቻቸው
አይጥ ጣረ ሞት ይዟት ትጫወታለች ድመት
አይጧ ጣረ ሞት ይዟት ድመቷ ትጫወታለች
አይጥም ጠላ ባልና ሚስት ያጣላ
አይጥም ጠላ ከጎረቤት ያጣላ
አይጥ ለሞቷ የድመት አፍንጫ ታሽታለች
አይጥና ዝሆን ቢዋደዱ አሳ ወለዱ
አይጥና ድመት ታገሉ ማናቸው ጣሉ
አይጥና ፍልፈል ሽክላና ገል
አይጽፍ ደብተራ ክንፍ የሌለው አሞራ
አይጥ ዝሆን አክል ብላ ፈንድታ ሞተች
አይፈስ ውኃ አይሰደድ ድኃ የለም
አደራ ቢሏቸው ይብሳሉ እሳቸው
አደራ ጥብቅ ሰማይ ሩቅ
አደባባይ አይውልም አባይ
አደባባይ አይውል አባይ
አደናግር እንደ ነብር
አደን ያስረሳል ኃዘን
አደንጓሬ የእህል አውሬ
አዲስ ወጠ ሰሪ ዝንጅብል ታበዛለች
አዳኝ ውሻ ጭገር ባፏ በትር ትርፏ
አድል አልኩህ እንጂ ጨልጥ አልኩህ
አድላዊ ዳኛ አምጡ ይላል የዶሮ ሻኛ
አድረው ሊለዩ አመል አያሳዩ
አድረው ሊለያዩ አመልን አያሳዩ
አድራሽ ተመላሽ ቀበኛ ደንጊያ ላሽ
አዶላ ወርቅ በየወንዛወንዙ እንደድመት ግልገል ሹሞቹ ባይበዙ
አጃ ወቅጦ ቢዘሩ ተመልሶ ከዘሩ
አጃ ፈልፍለው ቢዘሩ ተመልሶ ከዘሩ
አገርህ ወዴት ነው ማርያም ውህ እንግያው ወንድሜ ነሃ
አገርህ ወዴት ነው ማርያም ውህ እንግያው ዘመዴ ነሃ
አገር የጋራ ነው ሀይማኖት የግል ነው
አገሩ ሩቅ ስንቁ ደረቅ
አገሬ ሩቅ ጭብጦዬ ደረቅ
አገር ላጣ ሰሜን ምግብ ላጣ ጎመን

አገር ሲያረጅ ጃርት ያፈራል
አገር በጤና ለማኝ በጭራ
አገር ቢጠላህ አልፈህ አልፈህ ታረቅ
አገር ቢያከብር ለንጉስ ያስቸግር
አገር አላት ይበሉኝ ማህደረ ማርያም ቅበሩኝ
አገር የሌለው ለጌታ አዳሪ ማጭድ የሌለው መስክ ሰፋሪ
አገር የሌለው ለጌታ አዳሪ ማጭድ የሌለው ወራሪ
አገር ያለምክር ቤት ያለማገር
አገር ያደረው ዘንዶ የወደረው
አገር ያጣ ስሜን ምግብ ያጣ ጎመን
አገር ጥሎ ቁርበት ጠቅሎ
አገው ልቡ ዘጠኝ ስምንቱን ደብቆ ባንዱ አጫወተኝ
አገባሻለሁ ያለ ላያገባሽ ከባልሽ ሆድ አትባባሽ
አገኘሁ ብልሀት አርሶ መብላት
አገኝ ባይ ልብ የለህም ወይ
አጉሊንጥ ባልንጀራ እንብላ ሲሉት እንራ
አጉል መጋባት መጋማት
አጉል ንግግር ያደናግር
አጉል ፍቅር ያመናቅር
አጉል መንፈራገጥ ለመላላጥ
አጉል ልጅ ከመውለድ ነጉላ ልጅ ከመውለድ ይሻላል ማስወረድ ደግሞም ከማስወረድ ይሻላል ሴት መውለድ
አጉራሹን ነካሽ የበላበትን ወጪት ሰባሪ
አጋም ተደግፎ ይዋጋል እንባጮ
አጋምን የተጠጋ ቁልቋል ሲያለቅስ ይኖራል
አጋሰስ በጭነት ወገብ በመቀነት
አጋዘን ሲጠግብ የነፍጠኛ ጎጆ ይታከካል
አጋጨው እንደ ነጋዴ ጨው
አግባኝ አግባኝ ብለው ሊሽጠኝ አሰበ
አግኝቶ ከመዋረድ አጥቶ መኩራት
አጓት ጠጦ የሰከረ ካሳ በልቶ የከበረ የለም
አጎንብሶ በላን ተኝተህ ቀላውጠው
አጎንብሶ የሚበላን ተኝተህ ቀላውጠው
አጣሪ እንደ ለጋስ ከመንገድ ዳር ትቀመጣለች
አጣቢ ነበርን አለቅላቂ አዘዙብን
አጣቢ ነበርኩኝ አለቅላቂ ላኩብኝ
አጤ ከሞቱ በማን ይሟገቱ
አጤን መደብ እቴጌን ገደብ
አጤን ያሻል ቀላጤ
አጥልቆ የሚያርስ ከብሮ የማይጨርስ
አጥልቆ የማያርስ አጥርቶ የማይጨርስ
አጥልቆ የማያርስ ጀምሮ የማይጨርስ
አጥር ጥሶ ቅጥር አፍርሶ
አጥባቂ ደን ጠላቂ
አጥባቂ ደን ጠባቂ
አጣባቂ ፈረስ ከገደል ያደርስ
አጥብቀህ ጎርስህ ወደ ዘመድህ ዙር
አጥብቀህ ጉረስ ወደ ዘመዶችህ ተመለስ
አጥብቀህ ጉርስ ወደ ዘመዶችህ ምልስ

አጥብቆ ጠያቂ የናቱን ሞት ይረዳል
አጥብቆ ያሰረ ዘቅዝቆ ይሸከማል
አጥንት የሚያለመልም ወሬ ሰማሁላችሁ ዛሬ
አጥንት የሚያለሰልስ ወሬ ሰማሁላችሁ ዛሬ
አጥንትና ጅማት በአከላት
አጥፊና ጠፊ ወናፍና አናፊ
አጥፊው አልሚ መስሎ ይታየዋል ለሰው
አጥፍቶ ይርቋል አልምቶ ይሞቋል
አጩለው በለው
አጭር አህያ ሁልጊዜ ውርንጭላ
አጭር ባይኮራ ረጅም ባይፈራ
አጭር ባይኮራ ነፋስ በወሰደው ነበር
አጬላቂ ሰራቂ
አጬላቂ አጭላጊ
አፈ ምላጭ በደረቅ ይላጭ
አፈረች ድብኝት አከለች
አፈር ማሽ በአንድ እጁ አፈር መላሽ
አፈር ብለው አያፈሱህ እህል ብለው አያፍሱህ
አፈር ፈጭ ዝርዝር ቁጭ
አፈኛ ባፉ ሀይለኛ በመዳፉ
አፉ ቅቤ ልቡ ጩቤ
አፉ ከኛው ልቡ ከወሬኛው
አፉ ከኛ ልቡ ከነኛ
አፉን የረቱ እጁን የመቱ
አፉን ጠቅሞ ወርቁን ቅሞ
አፍላ ያለወጉ ፈላ
አፍልተው ቢጠጡት ወተት አይፋጅም
አፍራ ያለው ማሽላ ተኝቶ ያፈራል
አፍ ሲነድ ሆድ ይነድ
አፍ ሲናገር ልብ ይንቃል
አፍ ሲናገር አፍንጫ ያሽሟጥጣል
አፍ ሲከዳ ከሎሌ ይብሳል
አፍ ሲከፈት ጭንቅላት አብሮ ይከፈታል
አፍ ሲከፈት ጭንቅላት ይታያል
አፍ ሲያመልጥ ጸጉር ሲመለጥ አይታወቅም
አፍ ሲያርፍ ወዳጁን ያማል
አፍ ሲያብል ልብ ዳኛ ነው
አፍ ሲዋሽ ሆድ ይታዘባል
አፍ ሲድጥ ከእዳ እግር ሲድጥ ከአንጋዳ
አፍ ቢሳሳት እዳ እግር ቢሳሳት አንጋዳ
አፍ ነገር አይን አገር አያጣም
አፍና ቅብቅብ ሁሌ አያበላም
አፍና እጅ አይን የላችው ምነው አለመሳሳታቸው
አፍና እጅ እጅና ፍንጅ
አፍና እጅ እግርና ፍንጅ
አፍንጫ ሲመታ አይን ያለቅሳል
አፍንጫ ሲነካ አይን ያለቅሳል
አፍንጫን ሲመቱት አይን ያለቅሳል

አፍ እላፊ ያስከትላል ጥፊ
አፍ እኩል ጉልበት ስንኩል
አፍ ካልተናገሩበት እዳሪ ነው
አፍ የሚጎርሰውን እጅ ይመጥነዋል
አፍ ያለው ያግባሽ ከብት ያለው
አፍ ያለው ጤፍ ይቆላል
አፍ ያለው ጤፍ ይቆላል ራሱ ተናግሮ ሰውን ያናግራል
አፍ ያበዛ ጥበቡ ዋዛ
አፍ ዳገት አይፈራም
አፍጣኝና አቅጣኝ እመዳሮው እንገናኝ
እሄድ ባይ ስንቅ ፈጅ
እህሉ አንድ ሴቱ አስር ነው
እህል ለቀጠና ወርቅ ለዝና
እህል ላራሽ ርስት ለወራሽ
እህል ላበደረ አፈር ወርቅ ላበደረ ጠጠር
እህል ሲያጡ የናት ልጅ ያጡ
እህል ሲገኝ ወፍጮ ይሟልጣል
እህል ሲጠፋ ወፍጮ ይሰላል እህል ሲገኝ ወፍጮ ይደንዛል
እህል ሲጠፋ ወፍጮ ይቀራል
እህል በቀርበቦ እንቁላል በወታቦ
እህልን በጥቅምት ልጅን በጡት
እህል ባሳደገ ደመኛ አይደለም
እህል ከበዩ ሰው ከገዳዩ
እህል ከባዶ ልጅ ከጎዶ
እህል ከዘባጣ ልጅ ካርጣጣ
እህል ከውድማ ብቻውን ዋለ አያሌ ሰዎችን እንዳልገደለ
እህል ከዱር ልጅ ካጉል
እህል ሲያጡ የናት ልጅ ይጡ
እህል የበቀለበት ያስታውቃል
እህል ያለውሀ ንጉስ ያለድሀ
እህል አይገፋም
እህልን አላምጠ ነገርን አዳምጠ
እህል ወዳጁን ይጎዳል
እህል የያዘ ፈርዛዛ ወርቅ የያዘ ቀበዝባዛ
እህል ያለ ውሀ ንጉስ ያለድሀ
"እህ" ትበል እናትሽ እኔን አይታ የዳረችሽ አለ ቆማጣ
እለት ቀይቶ ላመት
እልልታ ደስታ
እልልታ ለደስታ እሪታ ለርዳታ
እልከና መኸገር ከላም ጡት ተጣብቆ ይገኛል
እልክ ምላጭ ያስውጣል
እልፍ ሲሉ እልፍ ይገኛል
እልፍ ሲሉ እልፍ ይገኛል ድሀ ሞኝ ነው ሞቱን ይመኛል
እልፍ ካሉ እልፍ ይገኛል ደሀ ሞኝ ነው ሞቱን ይመኛል
እማን ላይ ቆመሽ እግዜርን ታሚያለሽ
እማኝ ሲገዙ ነገር አያበዙ
እምዬ ኢትዮጵያ ሞኝ ነሽ ተላላ የሞተልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ
እምነት እስከ ሞት

እምን ላይ ቆመሽ እግዜር ታሚያለሽ
እረባዳ ቤቱ ገራም ሚስቱ
እረኛ ቢያኮርፍ ራቱ ምሳው ይሆናል
እሩቅ አሳቢ እቅርብ አዳሪ
እሪ በከንቱ ማን ሊሰማ ነው ጩኸቱ
እሪ በከንቱ ማን ሊሰማው ነው ጩኸቱን
እራሴን መተው እግሬን ቢያሻሹኝ መች ይገባኛል
እራቁቱን ለተወለደ ልጅ ጥብቆ መች አነሰው
እራት ሲበሉ የመጣ እንግዳ እራቱ ፍሪዳ
እራት ሲበሉ የመጣ ይቆጠራል ፍሪዳን እንዳመጣ
እራት የሌላት ደግሞ ምሳ አማራት
እሬትን ያልቀመሰ የማር ጣእምን አያውቅም
እራት የሌለው ቁስ እንደ ልቡ አይቀድስ
እሬት ለቀመሰው እንጂ ላልቀመሰው አይመርም
እራስ ከተመለጠ ነገር ካመለጠ
እራትን ቢንቁ አንድ እጅ ይለቃለቁ
እራትን ቢንቁ አንድ እጅን ይለቃለቁ ዳኛን ቢንቁ ከመከራ ይወድቁ
እርም ለትሀትና
እርግማን ያነሰው ገበያ ይፈሳል
እራትና መብራት አማትና ምራት
እራት የለሀም ቢሉት ከወጡ አውጡልኝ አለ
እራት የስማይ መብራት
እርሟን ብታፈላ አንድ ቁና አተላ
እርሟን ብታፈላ ጋን ሙሉ አተላ
እርሟን ብታፈላ ጀበናው ሙሉ አተላ
እርሟን ጠምቃ ፈጀችው ጠልቃ
እርሱ አይወደኝም መከራው አይለቀኝም
እርሱ ካለው ላያልፍ በሽተኛው ባይለፈለፍ
እርሱ ካለው ላያልፍ ምነው በሽተኛው ባይለፈልፍ
እርሷ ሰንፋ ራቷን ገንፎ አድርጋ ቢያጎርሷት ተኮሳት
እርሷ ወልዳው አልመሰለም እርሷም ጋግራ አልበሰለም
እርሱ ራሱ ጊዜ መሆኑን ባያውቀው ጊዜ ጊዜ ይላል ሞኝ ሰው
እርስ በርሱ ስጋን በኩበት ጠበሱ
እርስ በርሱ የተከፋፈለ ቤት አይቆምም
እርስ በርሱ ያልተደጋገፈ ግርግዳ አይቆምም
እርሻ ለባለ ከብት ርስት ለባለ ርስት
እርሻ ሲሉ ሞፈር ቆረጣ
እርሻ ላጥማጅ መሬት ለተወላጅ
እርሻ ቢያለሰልሱት እህል ያሳምራል ገንዘብ ቢያከማቹት ያኮራል
እርሻ ቢያርሱ እንደልብ ያጎርሱ
እርሻ ያውቋል ያጠብቋል
እርሻ ደጉ ሳያደገድጉ
እርሻ ጋራ ዞሮ የጎረቤት ዶሮ
እርሻው ቢያምር ዳቦውም ያምር
እርቅ ቢፈርስ ካስታራቂው ድረስ
እርቅ አይፈርስ አይን አይፈስ
እርቅ አፍራሽ ቤተክርስትያን ተኳሽ
እርቅ ከወርቅ ዛላ ከምርቅ

እራቂቱን ለተወለደ ልጅ ለምድ አነሰው ወይ
እርቅ ደም ያደርቅ
እርቅ የሰው ደም ያደርቅ
እርቅ የፈለገ ንጉስን ገበሬ ያስታርቀዋል እርቅ ያልፈለገ ገበሬን ንጉስ አያስታርቀውም
እርቅና ስንቅ ከቤትህ ሳለህ ይጠላል
እርኩም ይህን እስክበላ እድሜ ስጠኝ ይላል
እርሻው ሲያምር ዳቦውም ያምር
እርኩም ጉድ ባይ ጠጣ አታላይ
እርያ በሬ አይደለም
እርጅና ብቻህን ና
እርጉዝ ላም ያለው ሰው ደረቅም አያንቀው
እርጉዝ ሲያርዱ በወዳጅ ይፈርዱ ሆድ መርበድበዱ
እርጎውን ለውሻ እርሱን ለውርሻ
እርጉዝን ያቅፉ ይደግፉ
እርጥቡ ሬሳ ደረቁን አስነሳ
እሰራለሁ ብላ ሄዳ ተላጭታ መጣች
እሰር በፍንጅ ጣል በደጅ
እሱሱሱሱስ አለ ጎማ መነፋቱን ሳያውቀው
እሱ ቀርቶ ሌላ ዘፈን ወጥቶ
እሱ አይወደኝ መከራው አይለቀኝ
እሱ እርጥብ ነገሩ ደረቅ
እሷ ጣፋጭ ልጅቷ ቀንጣጭ
እሳት ለፈጀው ምን ይበጀው
እሳት መጣብህ ቢሉት እሳር ውስጥ ገብቻለሁ አለ
እሳት ቢቀርቡት ያሳክካል መነኩሴ ቢቀርቡት ይልካል
እሳት ቢያንቀላፉ ገለባ ጎበኘው
እሳት በሌለበት ጢስ አይኖርም
እሳት ቢዳፈን የጠፋ ይመስላል
እሳት ቢዳፈን የጠፋ ይመስላል ሞት ቢዘገይ የቀረ ይመስላል
እሳት ቢፈጃት ወደ ልጅዋ ጣለች
እሳት አመድ ወለደ እንዲሉ
እሳት ካየው ምን ለየው
እሳት እና ጌታ ብርቱ ነው
እሳት የሌለበት ቤት ጭስ አይወጣውም
እሳትን ምን ብትወደው ከጉያ አይሸጎጥ ወይ ጣራ አታወጣው
እሳት አለ እንጨት አይለማ ጀሮ እዳውን አይሰማ
እሳት ያለ እንጨት አይለማ ጆሮ እዳውን አይሰማ
እሳት አመድ ይወልዳል
እሳት ከበላው ወራሪ የዘረፈው
እሳት ከበረበረው ሴት የመከረው
እሳት ከበረበረው ሴት የበረበረው
እሳት ካባረረው ሴት የመከረው
እሳት ካልነደደ አያበራም
እሳት ካየው ምን ለየው
እሳት የገባ ቅቤ
እሳት ጭሮ ከነፋስ ላይ
እሳትና ነገር ትንሽ ይበቃዋል
እሳትና ነገር ቢያጋንኑት ይጋነናል

እሳትና ነፋስ ማርና መላስ
እሳትና ድሀ ሲነካኩት አይወድም
እሳትና ጥል የቀረበውን ያቃጥል
እስኪያልፍ ያለፋል
እሷ ሰርቃ እሷው ታፈርሰዋለች
እሷ ሰንፋ ራቷን ገንፎ አድርጋ ቢያጎርሳት ተኮሳት
እሷ በፈሳችው በኔ አላክከችው
እሷ ነፍጋ ራቷን ገንፎ አድርጋ ቢያጎርሷት ተኮሳት
እሷው ሙታ እሷው መርዶ ጠርታ
እስሩ ባርፍ ደክሞኝ ዋርካ በፍሬው ፈነከተኝ
እስራኤልና ጸሀይ የማይደርሱበት የለም
እስቲ ይሁና እናያለን አለች እውር
እሺ ባይ አክባሪ እምቢ ባይ አሳፋሪ
እሺ ባይ አክባሪ እምቢ ባይ አቅላይ
እሺ ይበልጣል ከሺ
እሺና ገለባ አይከብድም
እሾህ ለረጋጩ ነገር ላምጪው
እሾህ ላጣሪው ስራ ለሰሪው
እሾህ በሾህ ይነቀሳል ገንዘብ በገንዘብ ይመለሳል
እሾህ በሾህ ይወጣል ሰው በሰው ይመጣል
እሾህ አጣሪውን ነገር ፈጣሪውን ይጎዳል
እሾህን በእሾህ
እሸት በወረት እህል መውቃት በክብት
እሸት አድርገህ ቅዳው እንዳይጎሽ ጠላው
እቃ እንደመጣ ይውጣ
እበላ ባይ ቃል አቀባይ
እበላ ብዬ ተበላሁ
እበላ ብዬ ተበላሁ ምነው ሳልበላ በቀረሁ
እበላ ያለ ዳኛ እገድል ያለ መጋኛ
እበትም ትል ይወልዳል
እበት ትል ይወልዳል
እበት ትል ይወልዳል ድሀ እብለትን ይወዳል
እበትና ኩበት ወገንና ክብት
እባብ ለእባብ ይተያያሉ ካብ ለካብ
እባብ ለእባብ ይተያያል ካብ ለካብ
እባብ ላይበላው አብላላው
እባብ ሲያዩት ይለሰልሳል ጌታ ቢጫወት ባልንጀራ ይመስላል
እባብ ስለሆዱ ይሄዳል በሆዱ
እባብ ቀጭን ነው ተብሎ ራሱ አይረገጥም
እባብ በመርዙ መሬት በወንዙ
እባብ በራሱ ጠመጠመ ከሰይፍ ላይ እግሩን አቀመ
እባብ በእግርህ በትር በጅህ
እባብ ከእግርህ ብትር ከእጅህ አለች ቀበሮ
እባብ አፈር ያልቅብኛል ብሎ ሲሰስት ይኖራል
እባብ እንደ መለሰለስሽ ቅናተ ዮሀንስ በሆንሽ
እባብ እንደ መለስለሱ መታጠቂያ በሆነ እሱ
እባብ ከምድር ተጋድሞ ሰው በትር ይዞ ቆሞ
እባብ የልቡን አይቶ እግር ነሳው

አባብ የሚገድለው በምላሱ እኮ ነው
አባብን ያየ በልጥ በረየ
አባብ ያየ በልጥ በረየ
አባብ ጉድጓዱን አይስት
አባብ ጉድጓዱን ውሻ ጌታውን
አባብ ግደል ከነበትሩ ገደል
አባብ ጥበስልኝ ይብረድልኝ
አባብና ጓጉንቸር ባንድ ይኖራሉ
አባብን ሞተ ብሎ እራሱን መርገጥ መቅበጥ
አባክህ አታጋልጠኝ ለጠላት አትስጠኝ
አባክሽ ያሏት ጎረቤት ትሆን እመቤት
አቤት ሆኖ ካሰበ ሄዶ ያልሰጠ በለጠ
አቤት ዶሮ ሲታረድ አዱር ቀቅ ይያዛል
አቤት ዶር ሲታረድ አዱር ቀቅ ይይዛል
አብድ ለአብድ አብሮ ይነጉድ
አብድ ቢጨምት እስከ እስኩለቀን
አብድ ቢጨምት እስከ እስኩለቀን ነው
አብድ ከወፈፍተኛ ቤት ያድራል
አብድ እህል ገዝቼ ሚስቴን አሳበድኳት
አብድና ብርድ ያስቃል በግድ
አብድና ሰካራም የልቡን ይናገራል
አብድና ዘበናይ የልቡን ይናገራል
አብድና የዘመኑ ፖሊስ ህግ አያቅም
አብድ የያዘው መልክ አይበረክትም
አብድ ለአብድ ቀን ይባጅ
አብድ ቀን አይመሽም
አታከል ተግመል
አተካከል ተግመል
አቴ ከሆንሽ ካለስሚ አታልቅሽ
አቺን ዘዴ ለጋሽ ዘውዴ
አቺውም ቂጥ ሆና ተፈሳባት አሉ የኔታ
አቺም ቂጥ ሆና ስንጥቅ ተበጀላት
አቺ እንጣጥ እንጣጥ አምፖል ለማውለቅ ነዉ
እናቱ የሞተችበትና ውሀ የወረደችበት እኩል ያለቅሳሉ
እናቱ የሞተችበትና ገበያ የሄደችበት እኩል አለቀሱ
እናቲቱን አይተህ ልጅቷን አግባ
እናቲቱ ዶሮ ልጅዋን ይዛ ጓሮ ለጓሮ
እናቴ ቤት ጠላ እጠጣለሁ ብላ የቤቷን ውሀ ትታ ወጣች
እናቴን ላሀል ዘጠኝ ወር ቀረኝ አለች
እናቴን ሳይ ሴት ማግባቴ ቤትን ሳይ ትምባሆ መጠጣቴ
እናቴን ያገባ ሁሉም አባቴ ነው
እናት ለልጇ ነቢይ ናት
እናት ለልጇ ልጅ ለነገዬ
እናት ትረገጣለች እንደ መሬት
እናትዋን አይተህ ልጅቷን አግባ
እናት የሌለው ልጅ ቀላል እንደ ጌሾ ሳይበላ የበላ ሳይናገር ዋሾ
እናት የሌለው ተጓዳጅ እርሻ የሌለው ጠላ ወዳጅ
እናትየዋን ሲከጅሉ ልጅቷን ይስሟሉ

እናቴ ቤት ጠላ እጠጣለሁ ብላ የቤቷን ውሀ ትታ ወጣች
እናቷ  ዘንድ ሄዳ ከመጣች ከእንብላው በቀር ስራ አጣች
እናንተ ቤት ያለው እሳት እኛ ጋርም አለ
እናያለን ሲሉ ይታያሉ እናማለን ሲሉ ይታማሉ
እኔ ልብላ አንተ ጦም እደር
እኔ ሙቼ እኔው ቄስ ጠርቼ
እኔም አለኝ ቁስል ያንተን የሚመስል
እኔም አራዳ አንቺም አራዳ ምን ያጣላናል በሰው በረንዳ
እኔም ፊጣጣ አንቺም ፊጣጣ ምን ያጣላናል በሰው ሰላጣ
እኔ በልጄ ሳዝን ልጄ በልጁ ያዝን
እኔ ባልኩ ይልኩና ይላኩ
እኔ ሳጣ ልጄ ጥርስ አወጣ
እኔ ከሞትኩ ሀብቴ ለከዝኔ
እኔ ከሞትኩ ማዘር ታብዳለች
እኔ ከሞትኩ ምርጫው ይሰረዛል
እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል አለች አህያ
እኔ ከሞትኩ እቃ እንዳታውሽ
እኔን ሲፈጀኝ ልጄን ያቃጥለው
እኔን አይተህ ተቀጣ በጉድህ እንዳትወጣ አለ ሌባ
እኔን የወደደ ካንጀት ልጄን የወደደ ካንገት
እኔን ያለ ካንገቱ ልጄን ያለ ካንጀቱ
እኔ አለኝ ቁስል ያንቱን የሚመስል
እኔ አይገባኝ አር ላይ ቁጭ ብሎ ፈስ ገማኝ
እኔ እበላው ሳጣ ልጄ ጥርስ አወጣ
እኔ እውነት እናገራለሁ ሌላውን አስኮንናለሁ
እኔ የምሞተው በእለት ህልሜ የሚደርስው በአመት
እኔ የምበላው ሳጣ  ልጄ ጥርስ አወጣ
እኔው ሞቼ እኔው ቄስ ጠርቼ
እኔው ሞቼ እኔው ቄስ ጠርቼ አለች ሴትዮ ቢመራት
እኔው ተቀርድጄ እኔው ተቀቅዬ ባወጣሁት ነፍስ ተንጎራደደብኝ ባለ ዘጠኝ ልብስ
እኔ ያለሁት እዚህ አንተ ያለኸው ሽሬ በምን አውቀህ በወሬ
እኔ የምሞተው ዛሬ ማታ ገብሱ የሚደርሰው ለፍልሰታ
እንብላም ካላችሁ እንብላ እንብላም ካላችሁ እንብላ አለች አያ ጅቦ
እንብዛም ብልሀት ያደርሳል ከሞት
እንብዛም ስለት ይቀዳል አፎት
እንቁራሪት ዝሆን አክል ብላ ተሰንጥቃ ሞተች
እንስራዋን ረስታ ውሀ ወረደች
እንስራዋን ጥላ ወንዝ ወረደች
እንቅልፍ ታበኸ ከነብር ትፋዘኸ
እንቅልፍና ሞት እሬትና ሀሞት
እንቅልፍ የጠላ ውሻ ያሳድጋል
እንበለ ገንዘብ መዝናናት ያመጣል ውርደት
እንባ ሲሻኝ አይኔን ጢስ ወጋኝ
እንኳን ለሙቅ ለገንፎም አልደነግጥ
እንኳን ለራሱ ለሰው ይተርፋል እሱ
እንኳን ለቤቱ ይተርፋል ለጎረቤቱ
እንኳን ለእህቴ ለሌላውም ይዘፍናል አንገቴ
እንኳን ለገንፎ ለሙቅም አልደነግጥ

እንኳን ሊያበሉኝ ገርፈው ሰደዱኝ
እንኳን መሞት ማርጀት አለ
እንኳን ተልባ ሽቶሽ እንዲያም ዘጠኝ ቂጣ ትፈጃለሽ
እንኳን አመነኩስ አልከናነብም
እንኳን እናቴ ሙታ እንዲያውም አልቅስ አልቅስ ይለኛል
እንኳንስ ዘንቦብሽ እንዲያውም ጤዛ ነሽ
እንኳን ዘንቦብሽ ድሮም ጤዛ ነሽ
እንኳን ከፎከረ ያድናል አምላክ ከወረወረ
እንኳን ከፎከረ ያድናል ከወረወረ
እንኳን እስቀው አገጠው የለኝ
እንኳን የሸመተ ያረሰም አይችልሽ
እንኳን ይችን የዝምብ ጠንጋራ እናውቃለን
እንኳንስ ዘንቦብሽ እንዲየውም ጤዛ ነሽ
እንኳንስ ዘንቦብሽ እንዲየውም ጤዛ ነሽ አሉ እትዬ ዘነቡ
እንደ ልብ የለም ነዳጅ እንደ ልብ የለም በራጅ
እንደ ልጅ በቀለበት እንደ ድመት በወተት
እንደ መረብ ሽፍኖ እንደ እንቁላል ደፍኖ
እንደ ሚስቴ አንጂ እንደእናቴ ሀሳብ አታውለኝ
እንደ ርግብ የዋህነት እንደ እባብ ብልህነት
እንደ ሰው ትመጪ እንደ አውሬ ትሮጪ
እንደ ሳር ነጭቶ እንደ ውሀ ተጎንጭቶ
እንደ ሸሸ ተነጥፎ እንደ ቅጠል ረግፎ
እንደ ሽመላ በሁለት ይበላ
እንደ ቆጫት ተነስታ የሰው ለቅሶ አጠፋች
እንደ በሶ አንቆ እንደ እርጉዝ አስጨንቆ
እንደ ተተከለ ትርሽማ እንደ ተሰጣ ሽማ
እንደ አባት ስቶ እንደ ንጉስ አውቆ
እንደ አገሩ ይኖሩ እንደ ወንዙ ይሻገሩ
እንደ አንድ ልብ መካሪ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ
እንደ አጤ ስርአት እንድ አብርሀም እራት
እንደ አጥር እንደ ቅጥር
እንደ አይን ፈሪ እንደ እግር ደፋር የለም
እንደ እንቁላል ድፍን እንደ መረብ ሽፍን
እንደ እሸት ፈልፍዬ እንደ ዘንግ መልምዬ
እንደ እንግዳ ደራሽ እንደ ውሀ ፈሳሽ
እንደ እንግዳ ጥልቅ እንደ ውሀ ፍልቅ
እንደ እውር አፍጣጭ እንደ ጎግ ቀላዋጭ
እንደ ካህን ናዝዞ እንደ ንጉስ አዝዞ
እንደ ንብ ቀስሞ እንደ ወጥ ቀምሞ
እንደ ንጉሱ አጎንብሱ
እንደ ወርቅ አንከብሎ እንደ ሽማ ጠቅሎ
እንደ ወንድማማች ተበዳደሩ እንደ ባእዶች ተቆጣጠሩ
እንደ ወይን መልምዬ እንደ እንጨት ተክዬ
እንደ ውሀ ይፈስ እንደ ጋዝ ይነፍስ
እንደ ውሌ ደጃዝማች ባሌ
እንደ ዝንጀሮ በአፋፍ እንደ ጠጣ በዛፍ
እንደ ዳኛ በውል እንደ ምሰሶ በመሃል
እንደ ገና ይመታል በገና

እንደ የቤቱ ብዙ ነው ብልሀቱ
እንደ ጸሀይ የሞቀ እንደ ጨረቃ የደመቀ እንደ አበባ ያሸበረቀ
እንደ ጴጥሮስ ብጽላሎተ ርእስ እንደ ጳውሎስ በዘፈረ ልብስ
እንደ ፈረስ ጆሮ እንደ ሰላጢን ጉሮሮ
እንደ ፈታሂነቱ ሁላችን እንኮነናለን እንደ መሃሪነቱ ሁላችን እንማራለን
እንዲህ ሊታረፈን ለሚስቴ ነፈግኋት
እንዲህ ልጠግብ በሬዩን አረድኩት
እንዲህ ነድጄ ልሙት የፊቱን በኋላ አድርጎት
እንዲያውም በመላ ፈስ ዳለቻ ነው
እንዲያው ብትመለሺ የገንፎ እንጨት ላሺ
እንዲያው ከምትቀሪ ምንቸቱን አንቅሪ
እንዳልበላ በአፌ እንዳልበር በክንፌ
እንዳልተወው ወለድኩ እንዳልሰው ነደድኩ አለች ላም
እንዳትበላ ለጎሚት እንዳትሄድ ቀየዷ ት
እንዳትሄድ ቀየዳት እንዳትበላ ለጎማት
እንዳየን ጤፍ አጋየን
እንዳዩ መብላት ሆድ ያሰፋል
እንዳዩ መጉረስ እድህነት ያደርስ
እንዳያማህ ጥራው እንዳይበላ ግፋው
እንዳያማ ጥራው እንዳይበላ ግፋው
እንዳይወልዱ ይመነኩሱ እንዳይጸድቁ ይልከሰከሱ
እንዳገሩ ይናገሩ
እንዶድ በገርነቱ ውሀ ወሰደው
እንዴት ዋልሽ ለእህቱ ግንድ ለሚስቱ
እንጀራ ለራብ ድንጋይ ለካብ
እንጀራ ለባእድ መከራ ለዘመድ
እንጀራ ምን ይጨርሰዋል መጉረስ
እንጀራ በማየት አያጠግብም
እንጀራ በሰፌድ አሞሌ በገመድ
እንጀራን ከባእድ መከራን ከዘመድ
እንጀራ የለም እንጂ በወተት አምገሀ ትበላ ነበር
እንጀራ ያለወጥ ቤት ያለ ሴት ከብት ያለበረት
እንጀራ ያለው ክቡድ እንጀራ የሌለው እብድ
እንጀራ ይጋግሩዋል እማድ ቤት መላ ያማክሩዋል ለሴት
እንጀራው ሳይኖር ከወጡ አስነኩልኝ
እንጇ በሰማያት በምድርስ የለም ምክንያት
እንግዲህ ነገሬን በከንፈሬ
እንግዳ ደራሽ ውሀ ፈሳሽ
እንግዳ ሆነህ ብትመጣ ሳይሰለቹህ ውጣ
እንግዳ ሲወደስ ባለቤቱን ያጎርስ
እንግዳ ሲያዘወትር ቤተሰብ ይሆናል
እንግዳ ሲያፍር ባለቤት ይጋብዛል
እንግዳ ይጋብዛል ባለቤት ሲያፍር
እንግዳ ደራሽ ውሀ ፈሳሽ
እንግዳ ፊት ወርቅ ኋላ ብር ኋላ ብረት
እንግዳ ፊት ወርቅ ኋላ ብር ኋላ ብረት ኋላ ጨርቅ
እንግዳና ሞት በድንገት
እንጎቻ የበላ ከራት ይታገሳል

እንጣጥ እንደ ፌቆ ሙልጭ እንደ ስብቆ
እንጥስ ቢሉ ቅንጥስ
እንጨት ሞልቶ ዛቢያ አይገኝበት
እንጨት ቢጠርቡት ይቀጥናል ሰው ቢበልጡት ይቀናል
እንጨት ቢያነዱት አመድ ቃጫ ቢፈትሉት ገመድ
እንጨት አይሸከሙ ላመድ አሮጊት አያገቡም ላትወልድ
እንጨት አይሸከሙም ላመድ አሮጊት አያገቡም ላትወልድ
እንጨት ካልነሱት እሳት አይጠፋም
እንጨት ካልነፈጉት እሳት አይጠፋም
እኖራለሁ ብለህ እጅግ አትበርታ እሞታለሁ ብለህ ስራ አትፍታ
እኖር ባይ ተጋዳይ
እኖር ባይ ተጋዳይ እድን ባይ ተከላካይ
እኛ ባገራችን ዳቦ ፍሪዳችን
እኛ ያልፈሳንበት ዳገት የለም አለች አሉ አህያ
እኛ ምን አገባን በሰው ፖለቲካ እኛንም አይንኩን እኛም ሰው አንነካ
እኛ ባገራችን ዳቦ ፍሪዳችን
እከከኝ ልከክህ
እከክ የሰጠ ጌታ ጥፍሩን አይነሳም
እከክን ያመጣ ጥፍርንም አላሳጣ
እከክ የሰጠ ጥፍር አይነሳም
እከሌ እባብ ነው መሄጃው አይታወቅም
እኩሉ በዶሮ እኩሉ በሽሮ
እኩሉን ተላጭታ እኩሉን ተቀብታ
እካስ ያለ ታግሶ እጸድቅ ያለ መንኩሶ
እወቁኝ ደብቁኝ
እወቁኝ ያለ ደብቁኝ
እወቅ ያለው ባርባ ቀኑ ያውቃል አትወቅ ያለው ባርባ ዘመኑ
እወደዋለሁ እንጂ ይወደኛል አትበል
እወዳለሁ እያለ የሚጠላ እጾማለሁ እያለ የሚበላ
እውር ምን አይቶ ደንቀሮ ምን ሰምቶ
እውር ምን ይሻል ብርሀን ነጋዴ ምን ይሻል መዳን
እውር ምን ይሻል ብርሀን በሽተኛ ምን ይሻል መዳን
እውር ሲቀናጣ ምርኩዙን ወርውሮ ይፈልጋል
እውር ሲቀናጣ ምርኩዙን ወርውሮ ፍለጋ ይገባል
እውር ሲቀናጣ ምርኩዙን ይጥላል ብሬክ ይደንሳል
እውር ሲወበራ በሽማው ላይ እራ
እውር ሲወበራ በትሩን ይጥላል
እውር ሲወበራ ከመሪው ይጣላ
እውር ሲጠግብ ከመሪው ይጣላል
እውር ነገ አይንሽ ይበራል ቢሏት ዛሬን እንዴት አድሬ አለች
እውር በበዛበት አንድ አይና ይነግሳል
እውር በዘንጉ ነጋዴ በወርቁ
እውር ቢሸፍት ከጓሮ አያመልጥ
እውር ቢጠግብ ዘንጉን ይወረውር
እውር ቢፈርዱ እውር ይወልዱ
እውር ተመሪው ሞኝ ተመካሪው
እውር ተመሪው ሞኝ ተመካሪው ይጣላል
እውር ተመሪው ሞኝ ተመካሪው አይጣላም

እውር ከመሪው ሞኝ ከመካሪው
እውርን እውር ቢመራው ተያይዞ ገደል
እውር አያፍር ፊሪ አይደፍር
እውር እውርን ቢከተል ተያይዘው ገደል
እውር አያፍር ፊሪ አይደፍር
እውሻ ሆድ ቅቤ አያድርም
እውነተኛ ሚስት ባሏን ትወዳለች
እውነቱን ተናግሮ እመሸበት ያድራል
እውነት ለግዜር ውሸት ለሳጥናኤል
እውነት ትዘገያለች እንጂ አትቀርም
እውነት የተናገረ በመርከብ የተሻገረ
እውነት የሀሰት ባህር ብትሰምጥ ትሟሟለች እንጂ አትጥፋም
እውነት ይመስላል ልብን ያቀስላል
እውነትና ሀቅ አያደር ይጠራል እንደ ወርቅ
እውነትና ንጋት እያደር ይታያል
እውነትና ንጋት አያደር ይጠራል እንደወርቅ
እዚያው ሞላ እዚያው ፈላ
እዚያው ዘንቦ እዚያው ያባራ
እዛም ቤት እሳት አለ
እየሰለሉ እድሜ መቁጠር
እየቀሉ ጥሬ
እየቀረጣችሁ አንበሳውም ሄደ ነብሩም ሞተላችሁ
እየበለቱ ሳይሆን እየቢለቱ
እየቤትህ ግባ እየራስህ ተቀባ
እየተፈጨ እየተቦካ እየሞተ እየተከካ
እየታጠቡት ያድፋል እየመከሩት ያጠፋል
እየወገንህ ቢሉት የመቶ አመት ቀዳ ከብት ተራ ቀመ
እየወገንህ ቢሉት አክንባሎ ጋጥ ገባ
እየነገርናቸው እያረጉት ዋዛ ከተለበለበው የተላጠው በዛ
እዩኝ እዩኝ ያለች ደብቁኝ ደብቁኝ ታመጣለች
እዩኝ እዩኝ ያለ ደብቁኝ ደብቁኝ ይላል
እየጠጡ ዝም የጋን ወንድም
እየፈለገው እወቀኝ ብሎ መጣ
እየፈለገው እወቀኝ እወቀኝ ብሎ መጣ
እየፈጩ ጥሬ
እያለው የማይከፍል ጭኖ የማያደላድል
እያወቁ ቢስቱ ምንድር ነው መድኃኒቱ
እያጫወትኳት ታንቀላፋለች
እያየህ ተናገር እየዋኘህ ተሻገር
እያየኋት የምታስቀኝ ሚስት አገባሁ
እያየኋት የምታስቅ ሚስት አገባሁ
እያደር ይቃቃር
እያደፈ በእንዶድ እየጎለደፈ በሞረድ
እዬዬም ሲዳላ ነው
እዬዬ ሲደላ ነው
እዬዬ ሲዳላ ነው
እደ ልቡና ለጸሎት እደ ሰብእና ለመስዋእት
እደን ገብተህ አምሳያህን ቁረጥ

እዳ ለቤት ምስጢር ለጎረቤት
እዳሪ ሳያወጣ የበላ እዳውን ሳይከፍል ጎታውን የሞላ
እዳሪ ያረሰ ለልጁ አጎረሰ
እዳ ሰርጉ ነውር ማእረጉ
እዳ ቢያምርህ ዋስትና ኩነኔ ቢያምርህ ግብዝና
እዳ ከሜዳ ሲለኝ አደረ
እዳ አለብኝ ብለህ አትቸገር እዳ የለብኝም ብለህ አትከበር አይታወቅም የአምላክ ነገር
እዳውን ከፍሎ የከተተ ጌታውን የተሰናበተ
እዳው ዶሮ መጋቢያው ዳወሮ
እድለ ቢስ ሲዳር ውሀ ይሞላል በጥር
እደለ ቢስ አሞራ አንበጣ ሲመጣ አይኑ ይጠፋል
እደለ ቢስ አሞራ አሸን ሲመጣ አይኑ ይጠፋል
እድላም አሞሌ በቅሎ ይለውጣል
እድላም አሞሌ በዶላር ይሸጣል
እድላም አሞሌ የምርጫ ምልክት ነው
እድል ተርታውን እጣ ፈንታውን
እድል የሌለው የሚለፋው ለሰው
እድል ፈንታ ጥዋ ተርታ
እድሜ ለንስሀ ዘመን ለፍስሀ
እድሜ ያልመከረው ሽማግሌ ከውሀ የገባ አሞሌ
እድሜ ካላነሰው ጊዜ አለው ለሰው
እድሜና መስታወት አይጠገብም
እድሜና ቁረንጬ ተበጣጥሶ ያልቃል
እድሜና ጨርቅ ሲበጣጠስ ያልቅ
እድሜና ጨርቅ በደህና አያልቅ
እድር እስከ በጌምድር
እጁ ተበትር አፉ ከነገር
እጁን በሰንሰለት እግሩን በብረት
እጇን በእጇ ቆረጥኩት
እጇ ከበትር አፌ ከነገር
እጅ ለነግር ያግዛል ልብ እንደ ንጉስ ያዛል
እጅ ላፍ ሚዛኑ ነው ባፍ የገባ ለእጅ ሀይሉ ነው
እጅ ሲነድ ልብ ይነድ
እጅ እሽሀን ይነቅሰዋል ጥጋብ ሞትን ያስረሳዋል
እጅ እያጠቡት ያድፋል ልጅ እየነገሩት ያጠፋል
እጅ ከልብስ ምላስ ከጥርስ
እጅ ከበትር አፍ ከነገር (ይቆጠብ)
እጅ ይዘው ያስገቡት እጅ ይዞ ያስወጣል
እጅህን ከባህር አግባ ብታገኝ አሣን ታወጣለህ ባታገኝ ታጥበህ ትወጣለህ
እጅና አፍ አይተጣጡም
እጅና አፍ አይተጣጣም
እጅና ጭራ አፍና እንጀራ
እጅና ጭራ ስጋና አሞራ
እጅግ ማግኘት ያመጣል ትእቢት
እጅግ ስለት ይቀዳል አፎት
እጅግ ብልሀት ያደርሳል ከሞት
እሪ በከንቱ ማን ሊሰማ ነው ጩኸቱ
እገሌን ሲያማ ለኔ ብለህ ስማ

እገሌ የዋለበት ሸንጎ አይጥ የገባበት እርጎ እርጎውንም ለውሻ እርሱንም ለውርሻ
እግረ መንገዳቸውን ይሸጣሉ በሬአቸው
እግረ ቀጭን እንደ ሰሳ ልበ ሙሉ እንደ አንበሳ
እግረ ቀጭን ይሞታል ሲሉ እግረ ወፍራም ይሞታል
እግረ ቀጭን ይሞታል ሲሉ እግረ ደንዳና ይሞታል
እግሩን ለጠጠር ግንባሩን ለጦር
እግሩ ለጠጠር ግንባሩ ለጦር
እግር ሄዶ ሄዶ ካር ጉድጓድ ይገባል
እግር ሲደርስ እግት ይመለስ
እግር ቢሳሳት ከአንጋዳ አፍ ቢሳሳት ከእዳ
እግር ተርካብ እጅ ተዛብ
እግር ከእርካብ እጅ ከዛብ
እግር ከሸሸ ልብ ሸሸ
እግር የላት ክንፍ አማራት
እግር ዜጋ ነው
እግርህን በፍራሽህ ልክ ዘርጋ
እግርና እራስ እኔ እለብስ እኔ እለብስ ይጣላሉ
እግርህን ለጠጠር ደረትን ለጦር
እግዚአብሄር ለፍጥረቱ ሰው ለሰውነቱ
እግዚአብሄር ለፍጥረቱ ሰው ለሰውነቱ ያስባል
እግዜር ሲሰጥ እንጀራ በወጥ
እግዜር ሲቆጣ በዝናብ አር አመጣ
እግዜር ሲቆጣ በዝናብ አር ያመጣ
እግዜር በትር ሲቆርጥ ቆላ አይወርድም
እግዜር ሲጥል እናት አታነሳም
እግዚአብሄርን ያህል ጌታ ገነትን ያህል ቦታ
እግዜር በመለኮቱ ጎልማሳ በሚስቱ
እግዜር ባወቀ ሰማይን አራቀ
እግዜር እባብን ልቡን አይቶ እግር ነሳው
እግዚአብሄር የተናገረውን አያስቀር የማያደርገውን አይናገር
እግዜርን ሳይጨምር የቀጠረ ሁልጊዜ ሲቆጥር ይኖራል
እግዚሄር ያመነውን ማን ይችለዋል ንጉስ የተከለውን ማን ይነቅለዋል
እጠጣ ሲል ይዋኛል እበላ ሲል ይዳኛል
እጣ ያስታርቃል ሙግት ያዳርቃል
እጣ ያስታርቃል እንጂ አይፈርድም
እጭን ያለ ኮርቻውን እለምን ያለ ስልቻውን
እጸድቅ ብየ ባቅፋት አንቀላፋች
እጸድቅ ብዬ ባዝላት አንቀልባውን በጥርሷ በጠሰችው
እጸድቅ ብዬ ባዝላት ተንጠልጥላ ቀረች
እጸድቅ ብዬ ባዝላት ተኝታ ቀረች
እፍረት ያከሳል ያመነምናል
እፍኝ ቀሎ ይዘህ ከአሻሮ ተጠጋ
ኧረ ሳቁ ናልኝ ጥርሴስ አመሉ ነው
ኧረ ጉዴ ባሌ ገደለ በጎራዴ

ከ

ከሀጻን ጋር አትብላ ድንች ድንቹን ይለቅምብሀል

ከልብ ካለቀሱ ነጻ ምርጫ ይካሄዳል

ከልብ ካለቀሱ እንባ አይገድም

ከልጅ አትጫወት ንፍጥ ይለቀልቅሀል

ከልጅ ጋር አትጫወት ይወጋሀል በእንጨት

ከልጅ ጋር አትጫወት አይንህን ያወጣዋል በእንጨት

ከመሞት መሰንበት

ከመሸም ጋዝ አለ

ከመቶ ሀምሳ ዳዊት የልብ ቅንነት

ከመናገር ደጃዝማችነት ይቀራል

ከመደብደብ ይሻላል ማደብ

ከማትረባ ጉልበት በሀግ አምላክ ይሻላል

ከማን ጋር እንደምትውል ንገረኝ አንተ ማን እንደሆንክ እነግርሀለሁ

ከማያቁት ወዳጅ የሚያቁት ጠላት ይሻላል

ከማያውቁት መልአክ የሚያውቁት ሰይጣን ይሻላል

ከማይረባ ቁርስ የጠዋት ጸሃይ ይሻላል

ከሜዳ ወዲያ ፈረስ ካርባ ወዲያ ቄስ

ከምኔው ሞትሽና አፈር አፈር ሸተትሽ

ከምድር ውስጥ ልቃቂት አይወጣም

ከሞኝ ደጃፍ ሞፈር ይቆረጣል

ከራስ በላይ ነፋስ

ከርሞ ጥጃ አድሮ ቃሪያ ታጥቦ ጭቃ

ከሰው ቀለብላባ ከመሬት ገብጋባ

ከሰው ክፉ ደባል ከጭነት ክፉ አላል

ከሰጠሽ ስጪኝ ካልፈለግሽ ፈግጪው ተቀምጠሽበት ከምትደፈጥጪው

ከቁራ ጋር የዋለች እርግብ ላባዋ ባይጠቁርም ውስጧ ጠቁሮ ትመለሳለች

ከቁርባን ውጭ ክርስትና

ከቁንጫ መላላጫ ያወጣል

ከበሉ አይቀር እንክት ከገሙ አይቀር ጥንብት

ከበሮ በሰው ላይ ታምሪያለሽ ሲይዙሽ ታደናግሪያለሽ

ከበሮ በሰው እጅ ታምር ሲይዙዋት ታደናገር

ከባለቤቱ (በላይ) ያወቀ ቡዳ ነው

ከባልሽ ባሌ ይበልጣል ማይክሮዌቭ አበድሪኝ

ከባልሽ ባሌ ይበልጣል ሸሮ አበድሪኝ

ከባልሽ ጋር ሁኚ ቢኳት የተለመነች መሰላት

ከባቄላ አይጠፋም ዲቃላ

ከባእድ የጠጡት ኮሶ ይወጣል ደም ጎርሶ

ከተኛ አንበሳ ዞርዞር ያለ ቀበሮ ይሻለል

ከነገረኛ ሰው ስንቅ አይደባልቁም

ከነገሩ ጾም እደሩ

ከነገሩ ጾም ይደሩ

ከኑግ ጋር የተገኘ ሰሊጥ በጣም ይጣፍጣል

ከናትዋ ልጅዋ ትብስ ባቄላ አሮባት እጅዋን ትልስ

ከኔ ከወሰድሽው ተቀምጠሽ ልበሽው

ከወንድም ደረቅ ከወጥ መረቅ

ከዘመድ አጠገብ የተዳረች ልጅ ትዳር አትይዝም

ከጠጅ ወዲያ አስካሪ ከባለቤት ወዲያ መስካሪ

ከኛ ወዲያ ጎራሽ  እህል አበላሽ
ከኛ ወዲያ ፉጨት አፍ ለማሞጥሞጥ
ከአህያ የዋለች ሳር መጋጥ ትማራለች
ከአህያ የዋለች ጊደር ለከፋ ጀመረች
ከአህያ የዋለች ጊደር ፈስ ተምራ መጣች
ከአህያ የዋለች ጊደር ፈስ ተምራ ትመጣለች
ከአማት መኖር መጋማት
ከአባቱ ፊት የሚናገር አፍ ለምጽ ይሆናል
ከአብሮ አደግህ ጋር አብረህ አትሰደድ
ከአጋም የተጠጋ ቁልቋል ዘላለም ሲያለቅስ ይኖራል
ከአፈርኩ አይመልሰኝ
ከአፍ የወጣ አፋፍ
ከአፍ የወጣ ቃል ከእጅ የወደቀ እንቁላል
ከዘላለም ፈስ ያንድ ቀን ቅዘን ይሻላል
ከዝንጀሮ ቆንጆ ምን ይመራርጡ
ከዝንጀሮ ቆንጆ አንዷ  ውድድሩን አሸነፈች
ከዳቦ የተገኘ ወጥ አብረህ ግመጥ
ከገሙ አይቀር መጠንባት ነው
ከገሙ አይቀር ቅርንት ነው
ከጠጣ የዋለ ጉሬዛ እህል ፈጅቶ ገባ
ከፈሳም ቤት ቅዘናም ገባበት
ከፍትፍቱ አጉርሱኝ
ከፍትፍቱ አጉርሱኝ ከመረቁ ጾመኛ ነኝ
ከፍትፍቱ ፊቱ
ኩላሊት ካላየ አይን አያይም
ካለመናገር ደጃዝማችነት ይቀራል
ካለቀ መቆጠብ ከመሸ መንጠብጠብ
ካለቀሰ አይቀር በደንብ ምታው
ካለቃና ከጠገራ ፊት ዞር በል
ካለ ፈጣሪ አሚጠሽ ጋግሪ
ካላት ከፍላ ኑ ቅመሱ የምትል ናት ተቃመሱ
ካልቀበጡ አይዘሉ ካልዘለሉ አይሰበሩ
ካልበሉበት ደጃ ሰላም ከበሉበት ቤት ነው
ካልታዘልኩ አላምንም አለች ሙሽራ
ካልደፈረሰ አይጠራም
ካልደፈረሰ አይጠራም ካልጠራ አይጠጣም
ካልፈላ አይገነፍል ካልተጣደ አይበስል
ካረገዘች ክታብ ያዘች ፈሷን ፈስታ ቂጧን ያዘች
ካረጁ አይበጁ
ካረጁ አይባጁ
ካንቺ የተሻለች ሴት ባላገኝ ሌላ እንዳታገቢ ጠብቂኝ
ካንድ ልጃገረድ ይገኛል ሁለት ዘመድ
ካንዠት ካለቀሱ እንባ አይገድም
ካያያዝ ይቀደዳል ካነጋገር ይፈረዳል
ካገሩ የወጣ አገሩ እስኪመለስ ቢጭኑት አህያ ቢጋልቡት ፈረስ
ኳስ ለራስሽ ስተይ ጎል ግቢ አለዚያ ፎሪ ብለው ይጠልዙሻል
ካንጀት በላይ ፍቅር እያደር ያቃቅር
ካንጀት ነው ካንገት

ካዋቂ ጠያቂ
ክረምት ከጭቃ በጋ ከግጫ
ክረምትና በጋ ቆላና ደጋ
ክረምትና ኮሶ ቤት በምሰሶ
ክረምትና ወላድ ሲጠሉት ያከብራል
ክረምትን የፈጀ በጋ አዳውን የፈጀ ዜጋ
ክፉ ሴት በኑሮ ላይ ከባድ ሬሳ ትሆናለች
ክፉ ሴት ጠዋት ወተት ማታ ሬት
ክፉ ባይኖር የመልካም ዋጋ አይታወቅም

ወ

ወልዶ አይስም ዘርቶ አይቅም
ወረቱን የተቀማ ነጋዴ ዋግ የመታው ስንዴ
ወሬኛ ሚስት ዘርዛራ ወንፊት
ወራጅ ውሀ አይውሰድህ ሟች ሽማግሌ አይርገምህ
ወሬ ቢነግሩህ መላ ጨምር
ወሬ ቢያበዙት ባህያ አይጫንም
ወርቅ የያዘ ቀበዝባዛ  እህል የያዘ ፈዛዛ
ወርቅ የጫነች አህያ ስትገባ የማይፈርስ ግርግዳ የለም
ወስፌ ቢለግም ቅቤ አይወጋም
ወንዝ ለወንዝ መቀደስ ያረፈ ሰይጣን መቀስቀስ
ወንዝ ለወንዝ ሩዋጭ የሰው በግ አራጅ
ወንድ ልጅ ተወልዶ ካልሆነ እንዳባቱ ስጡት አመልማሎ ይፍተል እንደናቱ
ወንድ ልጅ እና ቢላዋ ጨማ ይወዳሉ
ወንድ ሊበላ የሴት ሌባ
ወንድ ልጅ በተሸመበት ሴት ልጅ ባገባበት
ወንድ ልጅ ለፈረስ ሴት ልጅ ለበርኖስ
ወንድ ልጅ አንድ ቀን እንደ አባቱ አንድ ቀን እንደ እናቱ
ወንድ ባለ በእለት ሴት ባለች በዓመት
ወንድ እንደያዙት ነው
ወንድ ከዋለበት ከብት ከተስማራበት
ወዛም ገማ ቢለው የነጭ ወሬ ነው አለው
ወይ አበዳሪ ወይ ተበዳሪ ይሞታል
ወይ አታምር ወይ አታፍር
ወይዘሪትነት ያንድ ቀን ርቀት
ወይ ዘንድሮ !አለች ቀበሮ
ወይኖ አረሰው ወይኖ ጎረሰው
ወደሽ ከተደፋሽ ቢረግጡሽ አይክፋሽ
ወደሽ ነው ቀማጢት ንጉስ ትመርቂ
ወደቀ ሲሉ ተሰበረ ነው
ወደው የዋጡት ቅልጥም ከብርንዶ ይጥም
ወዳጅ ይመጣል ከራያ ጠላት ይወጣል ከጉያ
ወገኛ ቀበሌ ወረዳ (ከፍተኛ ) መሆን ያምራታል
ወግ ነው ሲዳሩ ማልቀስ
ወጠጤ ለወጠጤ ቢማከሩ እንዳይታረዱ
ወጡ ሳይወጠወጥ ወስከምቢያው ቂጥጥ
ወጣ ወጣና እንደ ሸንበቆ ተገነደሰ እንደ ሙቀጫ

ወጥን ማን ያውቃል ቢሉ ቀላዋጭ
ወጥን የሚጨርስ መጎራረስ ሴትን የሚያስመታት መመላለስ
ወጪ ያዘዘባት ጥቁር ሴት አንገቷን ትነቀሳለች
ወጭትና ሴት ሲከናነቡ ይሻላል
ወፍ እንዳገርዋ ትጮሀለች
ወፍጮና ሴት መቼም አይሞላለት
ዋቢ ያለው ያመልጣል ዋቢ የሌለው ይሰምጣል
ውሀ ለሚወስደው ሰው በትርህን እንጂ እጅህን አትስጠው
ውሀ ለቀደመ ግዳይ ለፈለመ
ውሀ ለወሰደው ካሳ አይከፍልም
ውሀ ለወሰደው ፍለጋ የለውም
ውሀ ሊያንስ ሲል ይገማል ሰው ሊያንስ ሲል ይኮራል
ውሀ ላነቀው ባለቤቱ ላላወቀው መድሀኒት የለውም
ውሀ ልትቀዳ ሄዳ እንስራዋን ረስታ መጣች
ውሀ መልሶ ውሀ ቀልሶ
ውሀ መመለስ ወደ ሌላ ማፍሰስ
ውሀ ምን ያስጮኸዋል ድንጋይ
ውሀ ምን ያገሳ ድሀ ምን ያወሳ
ውሀ ሲወስድ እያሳሳቀ ነው
ውሀ ሲደርቅ ይሸታል ሰው ሲከዳ ይወሸክታል
ውሀ ሲጎድል ተሻገር ዳኛ ሲገኝ ተናገር
ውሀ በለዘብታ ድንጋይ ይፈነቅላል
ውሀ በብልሀት ይቆላል በእሳት
ውሀ በእሳት ሰስ በዳገት
ውሀ ቢወቅጡት መልሶ እንቦጭ ነው
ውሀ ቢወቅጡት እንቦጭ
ውሀ ቢደርቅ አሳ ያልቅ
ውሀ ቢጠቅምህም ማእበሉን አትመኝ
ውሀና ገደል እያሳሳቀ ይወስዳል
ውሀና ጠጅ እኩል ይጠጣሉ
ውሀን መመለስ ወደ ሌላ ማፍሰስ
ውሀን ምን ያስጮኸዋል ድንጋይ
ውሀ አያንቅ ነገር አያልቅ
ውሀ እድፍን ያጠራል ትምህርት ልብን ያጠራል
ውሀ ከነቁ አባባ ከአጸቁ
ውሀ የሚወስደው ሰው አረፋ ይጨብጣል
ውሀ የጥቅምት ነበርሽ ታዲያ ማን ይጠጣሽ
ውሀ ጭስ ክፉ ሴት ሰውን ያበራሉ ከቤት
ውሀ ጭስና ክፉ ሴት ሰውን ያባርራሉ ከቤት
ውሀውም እንዳይደርቅ አሳውም እንዳያልቅ
ውሀውም እንዳይደርቅ አሳውም እንዳያልቅ አድርጎ ነው እርቅ
ውል አያወላውል ምላት አያሻግር
ውል ያዋውላል ታንኳ ያሻግራል
ውል ያዋውላል ታንኳ ያሻግራል አቧራ ያስላል
ውስጥ ውስጡን ድመትም አውሬ ነች
ውሻ ምን አገባት እርሻ
ውሻ በሰፈሩ ጅብ ነው
ውሻ በቀደደው ድመት ተከተለች

ውሻ በቀደደው ጅብ ይገባል
ውሻ በበላበት ይጮሀል
ውሻን በርግጫ ማለት እንካ ስጋ ማለት
ውሻ የጌታውን ጌታ አያውቅም
ውሽማዋን ብታይ ባልዋን ጠላች
ውጣ ያለው ብር ግርግዳ ሲፍቅ ያድራል
ውጣ ያለው ገንዘብ ግርግዳ ሲቧጥጥ ያድራል
ውጣ ያለው ገንዘብ ግርግዳ ሲጭር ያድራል

## ዘ

ዘላለም ከመፍሳት አንዴ መቅዘን
ዘመነ ግልምቢጥ ውሻ ወደ ሰርዶ አህያ ወደ ሊጥ
ዘመነ ግርምቢጥ ውሻ ወደ ሰርዶ አህያ ወደ ሊጥ
ዘመን እንደንጉሱ አውድማ እንደንፋሱ
ዘመን የሚወልደውን ንጉስ የሚፈርደውን
ዘመን የሚወልደውን ንጉስ የሚፈርደውን የሚያውቅ የለም
ዘመን የሰጠው ቅል ድንጋይ ይሰብራል
ዘመን የወለደው ንጉስ የወደደው
ዘመን ያነሳው ቅል ድንጋይ ይሰብራል
ዘመደ ብዙ ጠላሽ ቀጭን ነው
ዘመደ ብዙ ጠላው ቀጭን ነው
ዘመዱን ያማ ገማ
ዘመዱን ያማ ለራሱ ገማ
ዘመዱን ያማ እራሱ ገማ
ዘመድ ሲጣላ ያረክሳል
ዘመድ ሲፈራ ላሊበላ ሲኮራ
ዘመድ በዘመዱ አይጨክንም ሆዱ
ዘመድ ቢረዳዳ ችግርም ባልጎዳ
ዘመድ ቢረዳዳ ችግርም አይጎዳ
ዘመድና መድሀኒት የተቸገሩ ለት
ዘመድና መድሀኒት በተቸገረ ቀን ይፈለጋል
ዘመድና ሚዛን ከወገብ ይይዛል
ዘመድና እሳት በሩቅ
ዘመድና ሳንቲም ከመንገድ ወድቀው ሳንቲሙን አነሱ ዘመድን ጥለው
ዘመድና ዋንጫ እያለቀሰ ይመጣ
ዘመድና ገንዘብ ሳያስቡት ይገኛል
ዘመድና ፍየል ቤት አጥፊ ነው
ዘመድን ከዘመድ ጋር ማማት ዳቦ እንደመግመጥ ነው
ዘመድን ከዘመድ ጋር ማማት ጮማ እንደመቁረጥ ይቆጠራል
ዘመድን የሚወጉበት ጦር ጀንፎው አይለቀቅም
ዘመድን የሚወጉበት ጦር ጀንፎው አይለቀቅም
ዘመድ ከዘመዱ አህያ ካመዱ
ዘመድ ያረጀ በልቶ ያፈጀ
ዘመዶችዋ ሁሉ ይሿታል ግንድ አልብሰ
ዘምቶ ተወረሰ
ዘምቶ ያረጀ በልቶ ያፈጀ
ዘረፋና ቀን ካልተሻሙበት ያልቃል

ዘሩ የጣቴ ምድሩ ያባቴ
ዘር ልትበደር ሂዳ እህል ሲሸት መጣች
ዘር ከልጓም ይስባል
ዘር ከልጓም ይጠቅሳል
ዘር ከልጓም ይስባል
ዘር ከበረከት ትውልድ ከምርቃት
ዘርቶ መቃም ወልዶ መሳም
ዘርቶ ያልበላ አምላክን ጠላ
ዘር የጣቴ ምድሩ ያባቴ
ዘባራቂ ላባ ቀረሽ እብድ አስተኔ
ዘባራቂ ይወዳል ምራቂ
ዘቅዝቀው ቢቀብሩት ቀና ብሎ አደገ
ዘንዶ የዳገት በረዶ
ዘንጋዳ ከቆረጡት አገዳ ሚስት ከፈቷት እዳ
ዘንጋዳ ተቆረጡት አገዳ እዳኛ ከደረሱ እዳ
ዘንጋዳና ወታደር በመከር ጊዜ ይታይ ነበር
ዘንጋዳ የገለበጠ አባቱን የገላመጠ
ዘንዶ የዳገት በረዶ
ዘንግ ከተተከለ ልብ ተከፈለ
ዘኬውን ሲቋጥር አነቀው ነብር
ዘጠኝም ቢታለብ ለኔ ያው ገሌ ነው
ዘጠኝ ሞት መጣ ቢሉት አንዱን ግባ በለው
ዘጠኝ ሞት መጣ ቢሉት አንዱን ግባ በለው አለ
ዘጠኝ ሞት መጣ ቢሉት አንዱን ግባ በለው አለው
ዘጠኝ ጠጥቶ አስረኛውን የወደደ በሙሉ ነደደ
ዘጠኝ ጠጥቶ አስር የወደደ በሙሉ ተናደ
ዘጥ ዘጥ አቁማዳ ቂጥ
ዘገየች ከረመች ቀይታ መጣች
ዘፈን በበገና ነገር በዋና
ዘፈን በከበሮ አዋጅ በደበሎ
ዘፈን በገና ነገር በዋና
ዘፈን አለ በገና ነገር አለ በዋና
ዘፈን አለ በገና ነገር አለ ዋና
ዘፍኖ አያምር እንኳን አልቅሶ
ዛሬ ጠምቃ ፈጀችው ጠልቃ ጠልቃ
ዛሬ የትላንት ነገ ነበረች ዛሬ ደግሞ የነገ ትላንት ትሆናለች
ዛር ልመና ሳይያዙ ገና ከተያዙ ብዙ ነው መዘዙ
ዛብ የሌለው ፈረሰኛ ምሳ የሌለው ኮሰኛ
ዛፍ ሲወድቅ ከግንዱ ሰው ሲቸገር ከዘመዱ
ዛፍ በሌለበት እንቧጮ አድባር ይሆናል
ዛፍ ዝናብ ያስጥላል ትልቅ ሰው ከዳ ያስጥላል
ዛፍ ያለቅርንጫፍ አይደምቅም ሰው ያለሰው አይከበርም
ዛፎች ቢጠፉ ቁጥቋጦች ተሰለፉ
ዛፎች ቢጠፉ ቁጥቋጦች ዛፎች ነን አሉ
ዛፎች አለቁ እና ግራሮች ዛፍ ሆኑ
ዜማ በሀሌ ነገር በምሳሌ
ዝሆኑ ሳለ ዱካውን
ዝሆን ለቀንድ ባላባት ለትውልድ

ዝሆን ማለት ከሞኝ ያስቀጥራል
ዝሆንም ለሆዱ ድምቢጥም ለሆዱ ወደ ወንዝ ወረዱ
ዝሆን ቂጡን ተማምኖ ግንድ ይውጣል
ዝሆን ቢያንቀላፋ ዛፍ ተደግፎ ነው
ዝሆን እንሆት ፍለጋው ወዴት
ዝሆን እንሆ ፍለጋው ወዴት
ዝሆን ጥርሱን አዝመራ ገብሱን
ዝሆንና ዝሆን ቢጣሉ የሚጎዳው ሳሩ
ዝሆን የዋለችበትን ትመስላለች
ዝም ባለ አፍ ዝምብ አይገባበትም
ዝም ብትል ባትከበርም ችላ ትባልበታለህ
ዝምታ ለበግም አልበጃት አስራ ሁለት ሆና አንድ ነብር ፈጃት
ዝምታ ራሱ መልስ ነው
ዝምታ ራሱን የቻለ መልስ ነው
ዝምታ ወርቅ ነው
ዝምታ ወርቅ ነው መናገር ብር ነው
ዝም አይነቅዝም
ዝም ያለ ተንኮለኛ ይመስላል እንብላ ያለ ስስታም ይመስላል
ዝርክርክ ከወንፊት የባሰ ዝክዝክ
ዝቅ ቢል ከገብርዬ ከፍ ቢል ከዚያ ሰውዬ
ዝባድን ከውሻ እምነትን ከባለጌ አትሻ
ዝናር የሌለው ነፍጠኛ አለንጋ የሌለው ፈረሰኛ
ዝናብ ለዘር ጠል ለመከር
ዝናብ ለዘር ጠል ለመኸር
ዝናብ ሊጥል ሲል ይነፋፍሳል
ዝናብ ሊጥል ሲል ይነፍሳል
ዝናብ ሲያባራ ከዋሻ ምን ሊሻ
ዝናብ ሲያባራ ዋሻ ምን ያሻ
ዝናብ ሳይመጣ ሁሉ ቤት እንግዳ ባይመጣ ሁሉ ሴት
ዝናብ ሳይመጣ ገና የውሀን መንገድ መጥረግ ደህና
ዝናብ ከደመና ነገር ከዋና
ዝናብ ካልጣለ ሁሉ ቤት እንግዳ ካልመጣ ሁሉ ሴት
ዝናብ ካባራ ወደ ዋሻ
ዝናብና ልጅ ሲጠሉት ያከብር
ዝናብ ዘነበ ቢለው ከደጅህ እየው
ዝንብ ሩቅ አይበር ሜዳ አደግ ዱር አይደፍር
ዝንብ ሩቅ አይበር የሜዳ ልጅ ዱር አይደፍር
ዝንብ ሳያቀሙ ዝግን አይቅሙ
ዝንብ ሳይቅሙ ዝግን አይቅሙ
ዝንብ ቢሰበሰብ መግላሊት አይከፍትም
ዝንብ ቢሰበሰብ ጋን አይከፍትም
ዝንብ ካይን ጭራ ከዘባን
ዝንጀሮ መቀመጫዬ ይብሳል አለች
ዝንጀሮ የመቀመጫዬ ይቅደምልኝ አለች
ዝንጀሮ ሰው ነበር ይላሉ ድሮ
ዝንጀሮ ቢሰበሰብ ውሻን አይመክትም
ዝንጀሮ እንሳሳቅ ካልሽ ነዶዬን መልሽ
ዝንጀሮና ጥዋ ካፉ ነው የሚያዝ

ዝንጀሮና ጥዋ ክፉ ነው የሚይዝ
ዝንጀሮን በበግ ለውጠኝ ቢለው ጣፍጩን ትቼ አልማጩን
ዝንጀሮ የራሷን ጠባሳ ሳታይ በባልንጀራዋ ሳቀች
ዝንጀሮ የቂጧን መላጣ ሳታይ በባልንጀራዋ ትስቃለች
ዝንጅብል ማን ቢሉህ ማነኝ ትል
ዞር አሉ አልሸሹም
ዞሮ ዞሮ መዝጊያው ጭራሮ
ዞሮ ዞሮ እራቱ ጥሬ
ዞሮ ዞሮ የዶሮ አንገት በማሰሮ
ዞሮ ዞሮ የዶሮ አንገት ከማሰሮ

## የ

የሀምሌ ብራ የባልቴት ውብራ
የሀምሌን ውሀ ጥም የሀዳርን ራብ የሚያውቅ ያውቀዋል
የሀምሌ ጭቃ ቅቤ ለጋ
የሀር ገመድ የበቅሎ ክበድ
የሀብታም ልጅ ሲጫወት የድሀ ልጅ ይሞታል
የሀብታም ልጅ ወደ ቦሌ የድሀ ልጅ ወደ ባሌ
የሀጢአት ክፉ ጉቦ የበሽታ ክፉ ተስቦ
የሀጥኡ ዳፋ ጻድቁን ያዳፋ
የሁለት ሴቶች ባል ይሞታል ይበላል ሲባል
የሁለት አገር ሰደተኛ
የሁለት እዳ ከፋይ
የኋላ የኋላ አይቀርም ዱላ
የህልም ሩጫ የጨለማ ፍጥጫ
የሆነ አይመለስ እሳት አይጎረስ
የሆድ ማበድ ያስቃል በግድ
የሆድ ምቀኛ አፍ ነው
የሆድ ምቀኛው አፍ ነው
የሆድ ብልሀት የጋን መብራት
የሆድ ነገር ሆድ ይቆርጣል
የለመነ መነመነ
የለመነ ያገኛል የነገደ ያተርፋል
የለመኑትን የማይረሳ የነገሩትን የማይረሳ
የለመደ ለማኝ ቁርንጨፌን ቀማኝ
የለመደ ልማድ ያሰርቃል ከማእድ
የለመደ ልማድ ያሰድዳል ከማእድ
የለመደ መደመደ
የለመደ እጅ ጆሮ ግንድ ያስመታል
የለመደ ፈረሰኛ ዛብ አይጨብጥ እርካብ አይረግጥ
የለመደች ጠጣ ሁልጊዜ ሽምጠጣ
የለማኝ ስልቻ ሲንከባለል ከለማኝ እጅ ይወድቃል
የለማኝ ቅንጡ ይላል በወጥ አምጡ
የለም ቀሪ ካለ ፈጣሪ
የለበሰ የማንንም ጎረሰ
የለበሱት ያልቃል የሰጡት ያጸድቃል
የለጋስ ምስክሩ መስጠቱ

የላሜ ልጅ ያውራዬ ውላጅ
የላም መንጃ የሰማ መከንጃ የማር መቅጃ
የላም ወተቱን የጌታ ከብቱን
የላከ እንደ አፉ ያከከ እንደ እጁ አይሆንለትም
የላይ ለምጡን የውስጥ እብጡን ባለቤቱ ያውቀዋል
የላይ አልጋ የውስጥ ቀጋ
የላይኛው ከንፈር ለክርክር የታችኛው ከንፈር ለምስክር
የላጭ ልጅ ጸጉሩ ድሬድ ሆነ
የላጭን ልጅ ቅማል በላት
የላጭን ልጅ ቅማል በላው ያናጢን ልጅ ጅብ በላው
የሌለው ልብም የለው
የሌለው ልብ የለው ወዳጅ የለው
የሌለው ሚስት የለው ወዳጅ የለው
የሌሊት ግስገሳ የቀን ዘለሳ
የሌላት እራት ደግሞ ምሳ አማራት
የሌባ መኝታው አመድ መታሰሪያው ገመድ
የሌባ ምኝታው ካመድ መታሰሪያው ገመድ
የሌባ ሞኝ ከጎተራ ስር ይገኝ
የሌባ አይነደረቅ መልሶ ልብ ያደርቅ
የሌባ እጁን የፍየል ልጁን
የሌባ ዋሻ የቀማኛ መሸሻ
የሌባን ጠበቃ አደባልቀህ ውቃ
የሌባን ጠበቃ ደርበህ ውቃ
የልመና በሬ ትክክል አይሄድም
የልመና እንጀራ ምንጊዜም ከልመና አያወጣም
የልቡ ሳይደርስ እድሜ ይደርስ
የልቡን ሲነግሩት የኮረኮሩትን ያህል ይስቃል
የልቡን አድራጊ አይናደድም
የልብህን ቢያናግሩህ አለ እዳ ቢለቁህ
የልብህን ቢያናግሩህ አለ እዳ ቢሰዱህ
የልብስ ቀላል ባለቤቱን ያቀላል
የልጅ ልጅ እህል ፈጅ ኋላም ጅብ ያስፈጅ
የልጅ ልጅ ጅብ አስፈጅ
የልጅ መልከ ጥፉ በስም ይደግፉ
የልጅ ሞት የእግር እሳት
የልጅ ስጋ በናቷ ቅቤ
የልጅ ቀላቢ የአህያ ጋላቢ
የልጅ ብልጥ እየቀደመ ይውጥ
የልጅ ብልጥ የፊት የፊቱን
የልጅ ብልጥ የሰጡትን
የልጅ እናት አባይ ናት
የልጅ ተሟጋች በፊት ሰማይ ያያል ኋላ መሬት
የልጅ ተሟጋች ጠዋት ሰማይ ማታ ምድር ምድር ያይ
የልጅ ነገር ሁለት ፍሬ አንዱ ብስል አንዱ ጥሬ
የልጅ ነገር ጥሬ በገል
የልጅ ክፉ ዲቃላ የቤት ክፉ ሰቃላ የልብስ ክፉ ነጠላ
የልጅ ክፋቱ አለመከማቸቱ
የልጅ ጥፉ በስም ይደግፉ

የልጅ ፍቅር የሴት ከንፈር እናትን አያስቀብር
የልጅቷን ስጋ በእናቷ ቅቤ
የልጅ ፍሬ አንዱ ብስል አንዱ ጥሬ
የሎሌ አልቃሽ የሴት ቀዳሽ
የሎሌ አልቃሽ የሴት ቀዳሽ የቄስ አውደሽዳሽ
የመልኳን ሲሏት የጠባዩዋን
የመሬት ሴሰኛ ከመንገድ ዳር ይተኛ
የመሬት እርጥብ እሸቱን ደረቅ ምርቱን
የመስከረም ውስጡ በጋ ያረመኔ ልቡ ቀጋ
የመቀናጆ በሬ ሲመሽ ወደ ቤቱ ይስባል
የመበደሪያ አፍ መክፈያ አይሆንም
የመተሩበት እጅ ይወዛል የተማከሩት ዳኛ ያግዛል
የመታሰር ምልክቱ መጋዝ የመዳኘት ምልክቱ መያዝ
የመነነ ከዱር የሞተ ከመቃብር
የመነነ ከዱር የሞተ ከመቃብር አይወጣም
የመነኩሴ ሎሌ የክረምት አሞሌ
የመንግና የለው ገናና
የመንታ እናት ተንጋላ ትሞት
የመንገድ ዳር እሸት ባል የሌላት ሴት
የመንገድ ዳር እሸት ባል የሌላት ሴት ለማንም ናት
የመንዝ ልጅ እራያ ሂዶ ብልቱን አያወዛውዝም
የመከሩበት ሞተ የወርወሩበት ተሳተ
የመከራ ልጅ ሁል ጊዜ መከራ መስሎ ይታያል
የመከራ ሌሊት አያልቅም
የመከራ ሎሌ መከራ መስሎ ይታያል
የመከራ ውዝፍ ያለበት ነጋዴ ከሚወረር አገር ይደርሳል
የመከራን ጉድጓድ ሚዳቋ  አትዘለውም
የመኮንን ልጅ በከተማ የድሀ ልጅ በውድማ
የመኮንን ልጅ አዘን ቢነግሩት አደን
የመዝሙር መጀመሪያ ሀሌታ የዘፈን መጀመሪያ እስክስታ
የመጠጡት ቅልጥም ከብርንዶ ይጥም
የመጣ ሳይመጣ የውሃ ቦይ ጥረግ
የመጣው ቢመጣ ወይ ፍንክች ያባ ቢላዋ ልጅ
የመጣ ቢመጣ ከቤቴም አልወጣ
የመጥረቢያ ልጅ መዝለፊያ
የመጥረቢያ ልጅ ጥልቶ አይደል የሚባለው
የሙሽራ እድሜ ቢያጥር የሰርጉ ድግስ ሆነ ለተዝካር
የሙት ቀናተኛ ሚስቱን አደራ ይላል
የሙት አልቃሹ የቁም ወራሹ
የሙት አልቃሹ የቁም ወራሽ
የሙት የለውም መብት
የሚሆን ቢሆን ዝሆን ይበላ ቢሆን
የሚሉሽን በሰማሽ ገበያም ሳልወጣሽ
የሚሉሽን በሰማሽ ገበያም ባልወጣሽ
የሚመክተው ጋሻ የሚጠጋበት ዋሻ
የሚመክተው ጋሻ የሚጠጋበት ዋሻ የለውም
የሚመጣውን እንድታውቅ ያለፈውን እወቅ
የሚሞት ልጅ አንገቱ ረጅም ነው

የሚሮጡበት ሜዳ የሚወጡበት ቀዳዳ
የሚሰራ ምንም አያወራ
የሚሰርቀውን ያጣ ሌባ ሰላማዊ መስሎ ይገባ
የሚሰርቀውን ያጣ ሌባ ሰላማዊ መስሎ ይገባል
የሚሰርቅ ሰው አደራ ቢያስቀምጡት እጅ ይነሳል
የሚክድ ሰው አደራ ቢያስቀምጡት እጅ ይነሳል
የሚሰጥም እሾህ ይጨብጣል
የሚሰጥም ገለባ ይጨብጣል
የሚስት መናኝ የእናት አገር ለማኝ
የሚስት አንባሻ የጎረቤት ውሻ የደጅ እርሻ
የሚስት አሳቢ የጥንድ በሬ ሳቢ ይስጥህ
የሚስት ወይዘሮ እርሻው ጋራ ዞሮ
የሚስት ዘመድ የማር አንገት
የሚስት ዘመድ የማር እንጎቻ
የሚሸሹበት አምባ ሲሸሽ ተገኘ
የሚበላው ካጣ ይበላለት ያጣ
የሚበላው ካጣ ይበላበት ያጣ
የሚበጀውን ባለቤት ያውቃል
የሚከርመውም የማይከርመውም ባንድነት ዝናብ ይለምናል
የሚከርመውም የማይከርመውም አንድነት ዝናብ ይለምናል
የሚካኤል ስለት ለገብርኤል ምኑ ነው
የሚካኤል እለት ለገብርኤል ምኑ ነው
የሚወዱትን ሲያጡ የጠሉትን ይቀላውጡ
የሚወዱትን እቅፎ የሚጠሉትን ነቅፎ
የሚወዱትን እቅፍ የሚጠሉትን ንቅፍ
የሚወጋ ጦር ከእጅ ሲወጣ ያስታውቃል
የሚውል ሆድ ማለዳ ያረግዳል
የሚውል ሆድ ማለዳ ይርበዋል
የሚወጡበት ገደል የሚንጠለጠሉበት ቅጠል
የሚጠጉበት ገደል የሚንጠለጠሉበት ቅጠል
የሚዛንን አባይ ለእሳት የዳኛን አባይ ለሰንሰለት
የሚያልቅ እህል ከማያልቅ ዘመድ ያጣላል
የሚያልፍ ቀን የማያልፈውን ስም ያወርሳል
የሚያልፍ ቀን የማያልፍ ስም ያወርሳል
የሚያልፍ ነገር የማያልፍ ስም ይሰጣል
የሚያልፍ ውሀ አደረገኝ ድሀ
የሚያልፍ ውሀ አደረገኝ ድሀ አለች ልጅዋን ጎርፍ የወሰደባት
የሚያልፍ ዝናም አይምታህ የሚሞት ሽማግሌ አይርገምህ
የሚያልፍ ዝናም አይምታህ የሚያድግ ልጅ አይጥላህ
የሚያማ ጠበኛ ዘወር ይበል ከኛ
የሚያስፈራውን ለሚነግርህ የሚያስቀዝነውን ንገረው
የሚያስፈሳውን ለሚነግርህ የሚያስቀዝነውን ንገረው
የሚያብረቀርቅ ሁሉ ወርቅ አይደለም
የሚያድግ ልጅ በእናቱ እጅ
የሚያድግ ልጅ አትበድል የሚሞት ሽማግሌ አታቃልል
የሚያድግ ልጅ አትበድል የሚሞት ሽማግሌ አታቅል
የሚያድግ ልጅ አይጥላህ የሚሞት ሽማግሌ አይርገምህ
የሚያድግ ልጅ አይጥላህ የሚያልፍ ዝናብ አይምታህ

የሚያድግ ዛፍ በቁጥቋጦው ያስታውቃል
የሚያድግ ዛፍ ከቁጥቋጦው ያስታውቃል
የሚያጠግብ ቂጣ ከምጣዱ የሚወጣ ጥጃ ከገመዱ
የሚያጠግብ ቂጣ ከምጣዱ የሚወጣ ጥጃ ከገመዱ ያስታውቃል
የሚያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታውቃል
የሚያፈስ ቤት ጨቅጫቃ ሚስት
የሚዳቋ ብዛት ለነአቶ ውሻ ሰርግ ነው
የሚዳቋ ብዛት ለውሻ ሰርግ ነው
የሚዳቋ ግርግርታ ለውሻ ሰርጉ ነው
የሚዳቋ ግርግርታ ለውሻ ሰርግ ነው
የሚጣፍጥ ምግብ ምንድን ነው ቢሉት ሲርብ የበሉት
የሚጣፍጥ ምግብ ሲርብ የበሉት ነው
የሚጣፍጥ ምግብ ምንድን ነው ቢሉት ሲርብ የበሉት ነው
የሚፈልግ ያገኛል የሚተኛ ያልማል
የሚያፈስ ቤት ጨቅጫቃ ሚስት
የሚፈርስ ከተማ ነጋሪት ቢመታ አይሰማ
የሚፈታ ከተማ አዋጅ ቢነግሩበት አይሰማ
የማህበር አሽከር በልቶም አይጠገን ታሞም አይድን
የማሚቴን እጅ ያላየ በእሳት ይጫወታል
የማሽላ ዘር ከነአገዳው ቸር
የማታ ማታ እውነት ይረታ
የማታ ማታ ጭምት ይረታ
የማታ ምግብ ለእንግዳ የጠዋት ምግብ ለአገዳ የጠዋት መጠጥ ለእዳ
የማታ ሩጫ እንቅፋት ትርፉ
የማታርፍ ጣት አር ጠንቁላ ወጣች
የማታድግ ውርንጫ እናትዋን ትመራለች
የማታድግ ጥጃ እናቷ ን ትመራለች
የማታ አፍ ከጋን ይሰፋል
የማታድግ ፍየል አምስት ትወልዳለች ልጆቹዋም ያልቃሉ እሷም ትሞታለች
የማታፍር ድመት ስሜ ገብረማሪያም ነው ትላለች
የማትሄድ መበለት ዞራ ዞራ ትሰናበት
የማትረባ ፍየል  ዘጠኝ ትወልዳለች ዘጠኙም ያልቁና እሷም ትሞታለች
የማትሰማው ስድብ ከቀረርቶ ይቆጠራል
የማነው እህል ያሰኝሃል ክምር የማነው ቤት ያሰኝሃል አጥር
የማን እርሻ ብለህ እረስ የማን ሚስት ብለህ ውረስ
የማን ገበሬ ሹሩባ ይሰራል
የማን ዘር ጎመን ዘር
የማያልፍለት ዘበኛ ከዋርካ ስር አይጠፋም
የማያልፍ ነገር የለም ምሽትም በማለዳ ይተካል
የማያመሽ ባል ቅንድብ ይስማል
የማያስተኛ ነግረውህ ተኝተው ያድራሉ
የማያስተኛ ነግረውት ሳይተኛ አደረ
የማያበላ ቢገላምጥ አያስደነግጥ
የማያበድር ደመና የማይመልስ ቀማኛ
የማያበድር ገዳይ የማይመልስ አባይ
የማያዋጣ ማህበር በጠጅ ይጀመራል
የማያዋጣ ባል ቅንድብ ይስማል
የማያውቁት ስድብ ከዘፈን ይቆጠራል

የማያውቁት አገር አይናፍቅም
የማያውቁትን መስራት ከጥቅሙ ጉዳቱ ይብስ
የማያውቁት ምን ያውቅ
የማያዛልቅ ጸሎት ለቅስፈት
የማያደርግ እንትትን ከቤተክርስቲያን ይቆማል
የማያድግ ልጅ ባራስ ቤቱ ዳንኪራ ይመታል
የማያድግ ልጅ ታዝሎ ያፏጫል
የማያድግ ልጅ ቅዘን ይበዛዋል የማያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታውቃል
የማያድግ ጥጃ ከበሬ ፊት ይነጫል
የማያግዙ በፈር ያግዛሉ በከንፈር
የማያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታውቃል
የማያፍር እንግዳ ባለቤቱን ይጋብዛል
የማይሆን ነገር የተገላቢጦሽ ያችን ላንቺ ማናለሽ
የማይመለስ ማር ሹመኛ ይበደረዋል
የማይመስል ነገር ለሚስትህ አትንገር
የማይመስል ነገር ለሴት አትንገር
የማይመቱት ልጅ ሲቆጡት ያለቅሳል
የማይመቱት ልጅ ቢቆጡት ያለቅሳል
የማይሰማ ሰው ልቤን አፈረሰው
የማይሰማ ጆሮ ከጎረቤት ያጣላል
የማይሰራ አይብላ የማይረዳ አይጥላ
የማይስማሙ ዝንቦች ጥምብ ይልሳሉ የሚስማሙ ንቦች ማር ይጎርሳሉ
የማይቀርልህን እንግዳ አጥበቀህ ሳመው
የማይቀና ባይወለድ የማያስብ ባይነግድ
የማይቀና ባይወለድ የማያስብ ባይነግድ ይሻላል
የማይቀና ባይወልድ የማያስብ ባይነግድ
የማይቀና ባይወልድ የማያስብ ባይነግድ ይሻላል
የማይበሉት እህል ከአፈር እኩል ነው
የማይበላ የለም የማይጠግብ ባሰ
የማይተማመኑ ባልንጀሮች በየወንዙ ይማማላሉ
የማይተማመኑ ባልንጀሮች እየወንዙ ይማማላሉ
የማይተማመን ባልንጀራ በየወንዙ ይማማላል
የማይተች አይፍረድ የማያተርፍ አይነግድ
የማይቻል ጠላት ስለ ወዳጅ ይቆጠራል
የማይቻል ጠላት ከወዳጅ ይቆጠራል
የማይችሉት ድንጋይ ሲያወጡት ደረት ሲያወርዱት ጉልበት ይመታል
የማይከፍል ባለእዳ የሰጡትን ይቀበላል
የማይነጋ መስሏት እቷቱ ላይ አራች
የማይዘልቅ ማህበር በጠጅ ይጀመራል
የማይዘልቅ ማህበር አሜሪካ ይጀመራል
የማይዘልቅ ባል ቅንድብ ይሰማል
የማይዘልቅ ጸሎት ለቅስፈት
የማይደርሱበትን አያኩም
የማይድን በሽተኛ በጥር እሸት አምጡ ይላል
የማይድን በሽተኛ በበጋ እሸት አምጡልኝ ይላል
የማይድን በሽተኛ የማይመለስ ሀጢአተኛ
የማይድን ባህታዊ ወተት አምጡ የማይድን ፋቅራ ጠላ ስጡ
የማይገባ ሱሪ የማይበቅል ዘሪ

የማይጠረጥር ቤቱን አያጥር
የማይጣሉ መላእክት የማይታረቁ አጋንንት
የማይጽፍ ደብተራ ክንፍ የሌለው አሞራ
የማይፈርስ ምሽግ የለም
የማይፈወስ ድውይ የማይመለስ ጊጉይ
የሚዳ ንስንሱን የቤት ጉስጉሱን
የሚዳ ንስንሱን የቤት ጉዝጓዙን
የምህረት ጎደሎ የባሪያ ወይዘሮ
የምላስ ወለምታ ሪፈር የለውም
የምላስ ወለምታ በቅቤ አይታሽም
የምላስ ጦር ቢታከም አይድንም
የምመክተው ጋሻ የምጠጋበት ዋሻ
የምሮጥበት ሜዳ የምወጣበት ቀዳዳ የለም
የምስራች በቃሏ መላች
የምስራች በቃሏ መጣች
የምበላው ሳጣ ልጄ ጥርስ አወጣ
የምበላው ሳጣ ማእቀብ ሊጣል ነው
የምታሽንፈውን ምታ ቢሉት ወደ ሚስቱ ሮጠ
የምትለብሰው የላት ሻንጣ ቀለፈች
የምትለብሰው የላት የምትከናነበው አማራት
የምትመክተው ጋሻ የምትሰወርበት ዋሻ
የምትሮጥበት ሜዳ የምትገባበት ቀዳዳ
የምትበላው እህል ከማታየው መሬት ይበቅላል
የምትታጠቀው የሌላት የምትከናነበው አማራት
የምትነቃነቅ ግንድና የምትስቅ ሴት ልብ ሩቅ ነው
የምትኮነን ነፍስ ጎረቤት ያውቃታል
የምትጠላው ሰው ፊሱ እሆዱ ውስጥ ሳለ ይሸታል
የምትጠላውን የምትወደውን ሰጥተህ ሸኘው
የምትጠባ ጥጃ አትጩህም
የምትጠባ ጥጃ አትጩህም የማይደርሱበትን አያኩም
የምኞት ፈረስ ልጓም አይገታውም
የምናውቃትን ክምር በድባብ ሸፈኑዋት
የምድሩን በእፍ የሰማዩን በመጣፍ
የምጣዱ ሳለ የእንቅቡ ተንጣጣ
የምጣዱ እያለ የእንቅቡ ተንጣጣ
የምጣዱ እያለ የእንቅቡ ተንጫጫ
የምጥ መድሀኒቱ አንድ እግር ማስቀደም ነው
የሞላለት ድመት በሞዝቮልድ ይተኛል
የሞላለት ድመት ሳንባ ያማርጣል
የሞተ ልጅ አንገቱ ረጅም ነው
የሞተ ቢሞት ያለን እንጫወት
የሞተ አይከሰስ የፈሰሰ አይታፈስ
የሞተው ባልሽ የገደለው ውሽማሽ
የሞተው ባልሽ ገዳዩ ወንድምሽ (ሀዘንሽ ቅጥ አጣ ከቤትሽ አልወጣ )
የሞተ ያልነበረ ይመስላል ያለ የማይሞት ይመስላል
የሞተን አትርሳ የወደቀን አንሳ
የሞተውን እያ ይለዋል
የሞት በደለኛ አያይዞ በዳኛ

የሞኝ ለቅሶ መልሶ መልሶ
የሞኝ ልቅሶ መልሶ መልሶ
የሞኝ ልጅ ባባቱ ምን ይጫወታል አሉ
የሞኝ ሚስት በምልክት
የሞኝ ምስጋና የግንቦት ደመና
የሞኝ ቄስ ጸሎት ዘወትር አቡነ ዘበሰማያት
የሞኝ በትር ሆድ ይቀትር
የሞኝ እጁን ሁለት ጊዜ እባብ ነከሰው አንድ ጊዜ ሳያይ ሁለተኛው ሲያሳይ
የሞኝ ዘመድ ያፍራል
የሞኝ ዘፈን ሁልጊዜ አበባዬ
የሞኝን ጠላ በለው በአንኮላ
የሞኝ ጀርባ ሲመታ ለአዋቂ ይስማማል
የሞኝን ጥርስ ብርድ ፈጀው
የሞኝ ገበሬ እርሻ በሰኔ
የረጋ ወተት  ምርጫ ይደገምለታል
የረጋ ወተት ቅቤ ይወጣዋል
የራሷ ሲያርባት የሰው ታማስላለች
የራስህን አትበላ ገንዘብ የለህ የሰው አትበላ ዐመል የለህ
የራሷ አሮባት የሰው ታማስላለች
የራስዋ እያረረባት የሰው ታማስላለች
የሰማ ያውራ ያየ ይናገር
የሰካራም ግጥም ሁልጊዜ ቅዳ ቅዳ
የሰው አመሉ ዳውላ ሙሉ መቼ ያስታውቃል አብረው ካልዋሉ
የሰው አገሩ ምግባሩ የከብት አገሩ ሳሩ
የሰው አገር ዝናብና የእንጀራ አባት አይምታህ
የሰው እንጂ የቃል ውሸት የለም
የሰው ወርቅ አያደምቅ
የሰው ፈላጊ የራሱን ያጣል
የሴት ምራቋ ወፍራም ነው
የሴትን ብልሀት የጉንዳንን ጉልበት ይስጥህ
የሴት አገር ባልዋ
የሴት አጭር ወይዘሮ የወንድ አጭር አውራ ዶሮ
የሴት ጠጭና የአህያ ፈንጪ አያድርስ ነው
የሴት ልባም ያህያ ቀንዳም
የሴት ልቧ እንጂ ሆዷ አይመርጥም
የሴት መልኳ ምንድር ነው እጅዋን ታጥባ እንኩ ስትል ነው
የሴት መጠጥ ደፋር የወንድ አይን አፋር
የሴት ምክር ማሰሪያው አሽከቴ
የሴት ምክር የሾህ አጥር
የሴት ሞቷ  በማጀቷ
የሴት ረዥም የማቅ ውዥምዥም እንብዛም አያስጎመጅም
የሴት ሰካር ያጭር ሰው ኩራት አይታይም
የሴት ብቻዋን ሂያጅ የቄስ አርፋጅ ሁለቱም ነገር ወዳጅ
የሴት አመዳም የአህያ ሆዳም
የሴት አመዳም የአርጌ ሆዳም
የሴት አገሩዋ ባሏ
የሴት አገሩዋ ባሏ ማደሪያዋ አመሏ
የሴት እንግዳ የመርፌ ጎዳ

የሴት ቀበጥ የበቅሎ መድን ለመሆን ገበያ ትወጣለች
የሴት ትንሽ የለውም
የሴት ጉልበት ምላሱዋ
የሴት ጠጪ የግመል ፈንጪ
የሴት ዘበናይ የፊትዋን እንጂ የኋላዋን አታይ
የሽማግሌ ፍቅር እና የክረምት አበባ አንድ ነው
የሽሮ ድንፋታ እንጀራው እስኪመጣ ነው
የሽሮ ድንፋታ እስኪቀርብ ድረስ
የቀረ ይቀራል እንጂ ቀርቅር ብዬ አልጣራም
የቀበሮ ባህታዊ የለም
የቀበጠች አይጥ በድመት ጭራ ዘፈን ትዘፍናለች
የቀበጠች አይጥ የድመትን አፍንጫ ታሽታለች
የቀበጠ እንትን ቅቤ ቀቡኝ ይላል
የቀበጡ እለት ሞት አይገኝም
የቀን ጠማማን ሚዳቆ አትዘለውም
የቀጣፊ እንባ ባቄላ ያክላል
የቂጥ አጋሚ ፈስ ነው ወሮታው
የቃመ ተጠቀመ ያልቃመ ተለቀመ
የቃርያ እልክ አወፈረኝ
የቄስ ጠበቃ ዳዊት ይጠቅሳል
የቅርብ ጠበል የልጥ መንከሪያ ይሆናል
የቅድሙ በዛ ያሁኑ ተንዛዛ
የቆጡን አወርድ ብላ መሰላል አመጣች
የቆጡን አወርድ ብላ ቤቷን ከርቸሌ አደረገች
የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች
የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷ ጸጉር ታየ
የቆጡን አወርድ ብላ የጣራውን አወረደች
የበላ በለጠኝ የሮጠ አመለጠኝ
የበላ ባይማታም ዱላ ይችላል
የበላችው ያገሳታል በላይ በላዩ ያጎርሳታል
የበላና የተደገፈ ወድቆ አይወድቅም
የበሰበሰ ዝናብ አይፈራም
የቡና ስባቱ መፋጀቱ
የባለጌ ባለሟል ቂጥ ገልቦ ያያል
የባሪያ ደግ የቁልቋል ዘንግ የለውም
የባሰ አለ ሚስትህን አትፍታ
የባሰ አለና አገርህን አትልቀቅ
የቤቱ መቃጠል ለትኋኔ በጀኝ! አለች አሉ!
የባህር ዳር ሲታረስ ጓጉንቸር ሆድ ይብሳታል
የባልቴት ውብራ የክረምት ብራ
የባል ደግነቱ ውሽሜን መርሳቱ
የባል ደግነቱ ውሽምን መርሳቱ
የባሰ አለና አገርህን አትልቀቅ
የባእድ ፍቅር የውሀ ጌጥ አንድ ነው
የቤት ቀጋ የደጅ አልጋ
የተለጎመ በሬ ከቀንበሩ ቢያመልጥ ቢላዋ ይጠብቀዋል
የተመረረ ድሀ ይገባል ከውሀ
የተማረና ታጥቦ የተቀመጠ ብርጭቆ ፈላጊ አያጣም

የተጠማ ከፈሳሽ የተጠቃ ከነጋሽ
የተናቀ ሰፈር በአህያ ይወረራል
የተናቀ ብእር ይገነፍላል
የተናቀ እንትን ያስረግዛል
የተናቀ ያስረግዛል
የተናገሩት ከሚጠፋ የወለዱት ይጥፋ
የተናገሩት ከሚጠፋ ጽፎ ማስቀመጥ
የተናጠ ወተት ቅቤ ይወጣዋል
የተንቀለቀለች አፍሳ ለቀመች
የተንቀዠቀዠች ውሻ ላፏ ሊጥ ለወገቧ ፍልጥ አታጣም
የተከፋ ተደፋ
የተገነዘች ነፍስ የተለጎመች ፈረስ
የትም ፍጪው ዱቄቱን አምጪው
የት ትሂጃለሽ ቢላት በታክሲ አለች
የት ትሂጃለሽ ቢሏት በታክሲ
የት አውቅሽ ብሎ አጥብቆ ሳመኝ
የቸኮለ አፍስሶ ለቀመ
የቸገረው እርጉዝ ያገባል ስትወልድበት ገደል ይገባል የባሰበት እመጫቷን
የቸገረው ዱቄት ከንፋስ ይጠጋል
የነሀሴ ውሀ ጥሩ ነው የሚጠጣው የለም የድሀ ነገር ፍሬ ነው የሚሰማው የለም
የነብርን ጭራ አይዙም ከያዙም አይለቁም
የነቶሎ ቶሎ ቤት ግድግዳው ሰንበሌጥ
የነቶሎ ቶሎ ቤት ግድግዳው ብሎኬት
የነቶሎ ቶሎ ቤት ግድግዳው አስቤስቶስ
የነቶሎ ቶሎ ቤት ግርግዳው ጭራሮ
የነቶሎ ቶሎ ቤት በሊዝ ተሸጠ
የነቶሎ ቶሎ ቤት ዘበኛው ቶሎሳ
የነፋክክር ቤት ሳይዘጋ ያድራል
የእናት እርግማን ወለምታ ነው
የእናት ሞትና የግር እሳት እያደር ያንገበግባል
የእናት ልጅ ቢጣላ እውነት ይመስላል ለሌላ
የእናት ልጅ የሌለው አይበላ ሽሮ የሌለው ምንቸት አይፈላ
የናት ሆድ ዥንጉርጉር
የናት ሆድ ዥንጉርጉር ወላጅ ቀይና ጥቁር
የናት ልጅ የጎን አሳጅ
የናት ሞትና የድንጋይ መቀመጫ እያደር ይቆረቁራል
የናትን ክፋት የደመናን ውሀ ጥማት ባለቤቱ ያውቀዋል
የናት ድሀ የለውም
የንግዳ አይን አፋር ባለቤቱን ይጋብዛል
የአህያ ባል ከጅብ አያስጥልም
የአህያ "እቃው" ሆዱ ውስጥ ነው
የአሳ ግማቱ ከወደ አናቱ
የአሳ ግማቱ ከወደ ጭንቅላቱ
የ10 አለቃዬ ምክትሌ ሆይ አንተም እንደ መቶ ትኮራለህ ወይ
የአባትህ ቤት ሲዘረፍ አብረህ ዝረፍ
የአባይ ልጅ ኩሬ
የአባይን ልጅ ወዳቂ የዞማ ልጅ ሳቂ
የአባይን ልጅ ውሀ ጠማው የላጭን ልጅ ቅማል በላው

የአንዱ ሀገር ዘፈን ለአንዱ ሀገር ለቅሶ ነው
የአንድ ቀን መዘዝ ያለ ዘጠኝ ወር አይመዘዝ
የአይጦች አድማ ምርጫ እስኪደርስ ነው
የአገሬ ሰዎች ተጠንቀቁ የሰረቁት ስጋ ያስይዛል መረቁ
የአፍ ወለምታ በቅቤ አይታሽም
የአፍ ወለምታ በፖሊስ ይታሻል
የእህል ክፉ አጃ የሳር ክፉ ሙጃ የነገር ክፉ እንጃ
የእህል ጣም በጉረሮ የነገር ጣም በዦሮ
የእብድ ገላጋይ ድንጋይ ያቀብላል
የእናት ሞትና የድንጋይ መቀመጫ እያደር ይቆረቁራል
የእንጨት ምንቸት እራሱ አይድን ሌላ አያድን
የክፉ ሰው ተዝካር ውሀ ያስወስዳል በሀዳር
የክረምት ጥማትና የመከር ጊዜ ረሀብ አለባለቤቱ የሚያውቀው የለም
የወረት ውሻ ስሟ ወለተኪሮስ
የወረቀት ላይ ነብር የተግባር ስንኩል (አንሁን)
የወንድ አልጫ የእንዶድ ሙቀጫ
የወንድ አጭር ዝንጀሮ የሴት አጭር ወይዘሮ
የወንድም ልጅ ባይወልዱትም ልጅ
የወንዶች ባል አይተህ ማር
የወንድ ልጅ ሞት ያደረገውን የዘነጋለት
የወንድ አልጫ እንዶድ ሙቀጫ
የወንድምህ ጢም ሲላጭ ጢምህን ውሀ አርስ
የወጣ ቢገባ የገባ ይወጣል
የወደቀ ዛፍ መንገዱን ዘጋ
የወደደና የአበደ አንድ ነው
የወደዱትን ሲያጡ የጠሉትን ይቀላውጡ
የወጋ ቢረሳ የተወጋ አይረሳም
የወጋ ቢረሳ ፖሊስ ያስታውሳል
የወጌሻ ልጅ ዛፍ ላይ ያድራል
የወደቀ ዛፍ ምሳር ይበዛበታል
የዋኘ ይሻገራል የሰራ ይከብራል
የውሀ ሽታ የእባብ ፍለጋ የለውም
የውሀ ውሀ ምን አለኝ ቀሀ
የውሀ ጡር በእድፍ ያስታጥባል
የውድማ ዘንዶ ይቀጠቀጣል እንደበረዶ
የዘመድ ዘመድ ወንዝ ያሻግራል
የዘመድ ጥል የስጋ ትል
የዘሬን ብለቅ ይቀማምጠኝ አለ ቀማጣ
የዘንድሮውስ ብርድ ቀማጥ ያሳቅፋል
የዘገነ አዘነ ያልዘገነ አዘነ
የዝንጀሮ ለቅሶ መልሶ መላልሶ
የዝንጀሮ ስብሰባ በውሻ ጩኸት ይበተናል
የዝንጀሮ ንጉስ እሱ ይከምር እሱ ያፈርስ
የየጁ ቄስ እንደዜ ቅኔው ቢጎልበት ቀረርቶ ሞላበት
የየጁ ደብተራ ቅኔ ቢያልቅበት ቀረርቶ ጨመረበት
የደላው ሙቅ ያኝካል
የደላው ወርቅ ያስራል
የደመና ውሀ ጥምና የእናት በደል አይታወቅም

የደንቆሮ ለቅሶ መልሶ መልሶ
የደንቆሮ ለቅሶ መልሶ መላልሶ
የደንቆሮ ሰርግ በሽብሽባ ያልቃል
የድመት ልጅ መቢጨሯን አትረሳም
የድሮው ኮንጎዬ ካሁኑ ስቶኪንጌ ተሻለኝ
የድፍድፍ ኩራቱ ውሀ እስኪገባበት
የድፍድፍ ኩራቱ ውሀ እስኪገባ ነው
የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል
የጅብ ችኩል ቶሎ ያፏጨል
የገበያ ሽብር ለሌባ ሰርጉ ነው
የገበያ ግርግር ለሌባ ይበጃል
የገንዘብን ነገር ካሰላሰሉት አባ ሀናም ሞቱ እንደጨበጡት
የገጣጣ ሚስት ችግሩን አልቅሶ ካልነገራት አይገባትም
የጉልበት ግማሹ አፍ ነው
የጉድ አገር ገንፎ በጣም ይጣፍጣል
የጉድ አገር ገንፎ እያደር ይፋጃል
የጉሮሮን መታነቅ ያይን መደንቀል ያስጥለዋል
የጎረምሳ መልኩ እንጂ አነጋገሩ አያምርም
የጎጃም አዝመራ ሽንብራ ነው አሉ እኛም እንዳንበላ ተነቀለ አሉ
የጊዜ ግልባጭ እግር ሰውነት ያካል
የግመል ሽንት ይመስል ሁሌ ወደኋላ
የግፍ ግፍ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ
የጥቅምት ቀን እና የቀንጆ ሳቅ አያታልልህ
የጥንት ወዳጅክን በምን ሸኘኸው በሻሽ አዲሱ እንዳይሸሽ
የጨለማ አፍጣጭ የእውር ገልማጭ
የጨለማ አፍጣጭ የእውር ገልማጭ አይረባም
የጨረቃ ሂያጅ የምስክር ፈራጅ
የጨረቃ ሂያጅ የምስክር ፈራጅ
የጨረቃ ንጋትና የእውር ሞት አይታወቅም
የጨርቅ ነጬ የበራ ልጬ
የጨነቀው እርጉዝ ያገባል
የጨነቀው እርጉዝ ያገባል ስትወልድበት ገደል ይገባል
የጨነቀው ይዋጋል ያልደረሰበት ያወጋል
የጨዋ ልጅ ሁሉ አርግዟል ሆዱ
የጨዋ ልጅ ሁሉ አርግዟል በሆዱ
የጨዋ ልጅ ሲያዝን አሳ በወንዝ ይመክን
የጨዋ ልጅ ሲያዝን ውሀ በወንዝ ይመክን
የጨዋ ልጅ ሲፋታ ይጋባ ይመስላል
የጨዋ ልጅ ከከተማ የድሀ ልጅ ከውድማ
የጨዋ ልጅና ቅል ተሰባሪ ነው
የጨው ገደል ሲናድ ሞኝ ይስቃል ብልህ ያለቅሳል
የጨው ገደል ሲናድ ብልህ ያለቅሳል ሞኝ ይልሳል
የጨውን ባለእዳ በጨው ቢያባብሉት ጨዌን ማለቱ አይቀርም
የጨጌ ክብት በየወገኑ ይከተት
የጫማ ጠጠርና የእንጀራ ልጅ እያደር መቆርቆሩ አይቀርም
የጫማ ጠጠርና የእንጀራ እናት እያደር መቆርቆሩ አይቀርም
የፈላ ጠጅ የደረሰ ልጅ
የፈረሰኛ ማቅ ለባሽ የሴት ትምባሆ ቀማሽ

የፈረሰኛ ማቅ ለባሽ የሴት ትምባሆ ጎራሽ
የፈረሰ አልጋ የተሸበረ ዜጋ
የፈረንጅ አሽከር ነጭ ለባሽ ሳህን አመላላሽ
የፈሩት ይደርሳል የጠሉት ይወርሳል
የፈሪ ዱላ ሰላሳ ነው
የፈሪ ዱላ አያዳግምም
የፈሪ በትር አስር
የፈሪ ገዳይነት ለማታ
የፈሰሰ ውሀን ማቆር ይጠቅማል
የፈሰሰ ውሀ አይታፈስ
የፈሰሰ አይታፈስ የሞተ አይመለስ
የፈሲታ ተቆጢታ
የፈሳ የጥጋብም አይደል ሲረሳ
የፈስ ማደናገሪያው ዳባ
የፈስ ማደናገሪያው ዳቦ
የፈቷት ሴት ያጠቡት ወጪት የወጡበት ቤት አንድ ነው
የፈቷት ሴት ያጠቡት ወጪት የወጡበት ቤት አንድ ናቸው
የፉክክር ቤት ሳይዘጋ ያድራል
የፊተኛውን አሳረርሽ ቢሏት የኋለኛውን ጥሬ አወጣች
የፊት መሪ የኋላ ቀሪ
የፊት ምስጋና ለኋላ ሀሜት ያስቸግራል
የፊት እድፍ በመስታወት የሀጢአት እድፍ በካህናት
የፊት ክብት የእጅ ወረት
የፊት ወዳጅህን በምን ቀበርከው በሻሽ የኋለኛው እንዳይሸሽ
የፊት የፊቱን አለ ጓያ ነቃይ
የፋቂ ልጅ ሰነፍ አንዱን ሳይፍቅ አንዱን ይዘፍቅ
የፋቂ ሰነፍ አንዱን ሳይፍቅ አንዱን ይዘፍቅ
የፋቂ ቀንጀ ቡድነቱን አይተውም
የፌጦ መስሎሽ ሰናፍጭ ትቀምሽ
የፌጦ ብቅል የብሳና ጌሾ የተልባ አሻሮ ይህን ጠምቆ ለማ የሰው ነገር ለማይሰማ
የፍቅር ጣእሙ በመሳለሙ
የፍየል ልጇን የሌባ እጇን
የፍየል ጅራት ቂጥ አይከድን ከብርድ አያድን
የፍየል ጅራት ብልት አይከድን ከብርድ አያድን
የፍየል ጅራት ከብርድ አያድን ብልት አይከድን
የፍየል ጅራት ከብርድ አያድን አፍረት አይከድን
የፍየል ጅራት ከብርድ አያድን እፍረት አይከድን
የፍየል ጭራና የሰው ሀሳብ ሁልጊዜ ወደ ላይ ነው
የፍጅት ወራት እሳት በወንፊት
የፖሊስ ዘመድና የቤንዚን አመድ
የፖሊስ ዘመድ የቤንዚን አመድ የለውም
ዪዪዪዪዪ .........አለ !አምቡላንስ (የቁጭት አባባል)
ያህያ ስጋ አልጋ ቢሉት አመድ
ያህያ ባል ቀለበት አያስርም
ያህያ ባል ከጅብ ጉቦ በላ
ያህያ ባል ከዥብ አያስጥል
ያህያ ውሀ ጠጭ ሳይታወቅ መጣጭ
ያህያ ልጅ ጥሎ ይረግጣል የፈረስ ልጅ ጥሎ ይደነግጣል

ያህያ ስጋ ካልጋ ሲሉት ካመድ
ያህያ ካልጋ ሲሉት እምድር
ያህያ ስጋ  ውርደተኛ አልጋ ላይ ቢያኖሩት እመሬት ይተኛ
ያህያ ቀበጥ ከጅብ ጡት ይጣባል
ያህያ ባል ከጅብ አያስጥል
ያህያ እንግዳ የጅብ እራት ነው
ያህያ ደግነት ጭነት ማብዛት
ያህያ ውሀ ጠጭ ሳይታወቅ መጣጭ
ያህያ ጀላፊ መስክ ያጠፋ የሹም ዘፋፊ አገር ያጠፋ
ያህያ ፍለጋና የጥሬ እራት በግዜ ነው
ያህያ ፍሪዳ የእባብ ለማዳ የለውም
ያለባለቤቱ አይነድም እሳቱ
ያለአንድ የላት በዘነዘና ትነቀስ
ያለውን የሰጠ ንፉግ አይባልም
ያለውን የወረወረ ንፉግ አይባልም
ያለአዋቂ ተራች የራሱን አመልካች
ያለ ዝናብ ነጎዳ ያለ ብድር እዳ
ያለ ወጉ አህዮች ተዋጉ
ያለ ባለቤቱ አይነድም እሳቱ
ያለ የሚኖር ይመስላል የሞተ ያልነበረ ይመስላል
ያለ ይበዛል (አለ ወፍጮ)
ያለህ ምዘዝ የሌለህ ፍዘዝ
ያለ መሰረት ቤት ያለ ትምህርት እውቀት የለም
ያለ መከራ አይገኝም እንጀራ
ያለ መከራ ጸጋ ያለ ድካም ዋጋ አይገኝም
ያለ መጥረቢያ እንጨት ሰባሪ የቆማጣ ዘንግ ወርዋሪ
ያለ ምቀኛ አይገኝ ፍቅረኛ
ያለ ሴት ምን ያደርጋል ቤት
ያለ ሴት ቤት ያለበሬ መሬት
ያለ ስራ መብል ያለዳኛ ውል
ያለ ስራ መብል ያለዳኛ ውል አይቻልም
ያለ ስራ አይበላ እንጀራ
ያለ ስራ አይበላ እንጀራ አለባል ቆጥ አይሰራ
ያለስፍራው የተሰበረ ሲጠግኑት አስቸገረ
ያለስፍራው የተሰበረ ሲጠግኑት ያስቸግራል
ያለ በሬ ምን ያደርጋል ገበሬ
ያለበት ይብላላበት
ያለበት ይጉላላበት
ያለ ባለቤቱ አይነድም እሳቱ
ያላባቱ ቢዛቁን አባክኖ ያባክን
ያለአቻ ጋብቻ ቆይ ብቻ ቆይ ብቻ
ያለ እዳው መዝመት ዋ ብሎ መቅረት
ያለ እዳው ዘማች ዋ ብሎ መቅረት
ያለ ክንፍ መብረር ያለ ስራ መክበር
ያለው ሳይዋደድ ለሞተው መናደድ
ያለው ይምዘዝ የሌለው ይፍዘዝ
ያለው ይመዛል የሌለው ይፈዛል
ያለው ይበላል የሌለው ያፈጣል

ያለውን ካልሰቱ በስም አይበሉ
ያለ ዘዴ ጋሻ እንቅብ ነው
ያለ ዘመድ ነግሶ ያለ አቡን ቀስሶ
ያለ ዝናብ ነጎዳ ያለብድር እዳ
ያለ የሚኖር ይመስላል የሞተ ያልነበረ ይመስላል
ያለ ጊዜው የተወለደ ልጅ አባቱን ጥሎ አያቱን ያስረጅ
ያለ ጎረቤት ቡና ያለ ሙያ ዝና
ያለ ጎታ ደረባ ያለልብስ ካባ
ያለ ጎተራ ደረባ ያለልብስ ካባ
ያለ ጎታ ደረባ ምንድን ነው
ያለ ይበዛል አለ ወፍጮ
ያለ ጥርስ ቀሎ ያለ ጓድ አምባጓሮ
ያለ ጨው በርበሬ ያለሞፈር በሬ
ያለ ፊቱ አይቀርስ ያለባለቤቱ አይወርስ
ያለ ፍርድ ማሰር በፈጣሪ ማማረር
ያለ ፍቅር ሰላም ያለ ደመና ዝናብ
ያለ ፍቅር ጸሎት ያለ እንጨት እሳት
ያሉሽን በሰማሽ ኖርዌይ ባልመጣሽ
ያሉሽን በሰማሽ ገበያ ባልወጣሽ
ያላማረ ሰርግ ጉልቻው ይሸረፋል
ያላዋቂ ሳሚ ንፍጥ ይለቀልቃል
ያላዩት አገር አይናፍቅም
ያላረፈች ምላስ ሽማ ትልስ
ያላረፈች እግር ከዘንዶ ጉድጓድ ትገባለች
ያላሰብከውን አግኝ መረገመም ምርቃን አይደል
ያላስደጉት ውሻ ቤት ዘግተው ቢመቱት ዞሮ ይናከሳል
ያላባቱ ቢዛቁን አባክኖ ያባክን
ያላዋቂ ሳሚ ምላስ ይነክሳል
ያላወቁ አለቁ
ያላዞረ ሲዞር አደረ
ያላዋቂ ቀራሽ ማእድ አበላሽ
ያላየ ልጅ ዳቦ ፍሪዳው
ያላዩት አገር አይናፍቅም
ያላዩት ነገር ክፉ አይደለም መልካምም አይደለም
ያልሰማ ጆሮ ከጎረቤት ያጣላል
ያልበላህን አትከክ
ያልበላ ዳኛ አያሟግት ያልጠጣ እንግዳ አይጫወት
ያልተመከ ግልግል ያውቃል
ያልተማረ ዋናተኛ ከዳኛ ፊት እንቢተኛ
ያልተነካ ግልግል ያውቃል
ያልተገላበጠ ያራል
ያልታደለ ቀዳ ሲላፉ ያድራል
ያልታደለ በረዶ ከድንጋይ ላይ ያርፋል
ያልታደለች ከንፈር ሳትሳም ታድራለች
ያልታደለ ከንፈር ሊፕስቲክ ያበዛል
ያልታደለ ከንፈር ሳይሳም ያረጃል
ያልነበረ ያፈርሳል ቀዳዳ ያፈሳል
ያልወለደ አጋድሞ አረደ

ያልወለድኩት ልጅ አባባ ቢለኝ ሆዴን ባርባር አለኝ
ያልወለድኩት ልጅ አባዬ ቢለኝ አፌን ዳባ ዳባ አለኝ
ያልጠረጠረ ተመነጠረ
ያልሚል ይተረጉሚል
ያልሞላ ተርፎ አይፈስም
ያልሞተና ያልተኛ ብዙ ይሰማል
ያልሰማ ጆሮ ከጎረቤት ያጣላል
ያልሰማ ጥኑ ነው ባልሽ ወዳጇ ነው
ያልሰሙት ነገር ክፉም መልካምም አይደለም
ያልሰጡት ተቀባይ ያልጠሩት አቤት ባይ
ያልሳሉት አይላጭ ያላዩት አይቆጭ
ያልቆረጠ እግብ አይደርስም
ያልበሉት እዳ ያልጠሩት እንግዳ
ያልበላ ሬሳ ያልለበሰ እንሰሳ
ያልበላ ዳኛ አያሚግት ያልጠጣ እንግዳ አያጫውት
ያልበላኝን ቢያከኝ አይገባኝ
ያልበጀው እሳት ፈጀው
ያልተማረ አይጸድቅ ያልተወቀረ አያደቅ
ያልተማረ አይምርም ያልተወቀረ አያደቅም
ያልተመታ ልጅ ሲቆጡት ያለቅሳል
ያልተማረ ዋናተኛ ከዳኛ ፊት እንቢተኛ
ያልተረታ አይረታ ያልጠገበ አይማታ
ያልተሾመ አያዝ ያልቀሰሰ አያናዝዝ
ያልተሾመ አያዝ ያልቀሰሰ አይናዝዝ
ያልተቀጣ ልጅ ቢቆጡት ያለቅሳል
ያልተቀጣ ልጅ ያልታጠበ እጅ
ያልተነካ ግልግል ያውቃል
ያልደረሰበት ግልግል ያውቃል
ያልተገላበጠ ያራል
ያልተገላበጠ ያራል ያለ ይበዛል አለ ወፍጮ
ያልተገራ ፈረስ ይጥላል በደንደስ
ያልተጠናከረ ድንገት ተሰበረ
ያልተፈተነ ወዳጅ ያልተተኮሰ ሽክላ
ያልተፈተነ ወዳጅ ያልተተኮሰ ሽክላ ነው
ያልታረመ አፍ ከዋንጫ ይሰፋል
ያልታየ እንጂ ያልተሰማ ያልተደረገ እንጂ ያልተባለ ነገር የለም
ያልታደለ በረዶ ከድንጋይ ላይ ያርፋል
ያልታደለ ከንፈር ሳይሳም ያረጃል
ያልታደች ወፍ አይደ በጥቅምት ይጠፋል
ያልነበረ ያፈርሳል ቀዳዳ ያፈሳል
ያልወለደ አንጀት ጨካኝ ነው
ያልወለደ አይነሳ የሽምብራ ማሳ
ያልወለደ አጋድሞ አረደ
ያልወለዱ ሁሉ ጊደሮች ይባላሉ
ያልወለደኩት ልጅ አባባ ቢለኝ አፌን ዳባ ዳባ አለኝ
ያልወለደኩት ልጅ አባ አባ ቢለኝ አፌን ዳባ ዳባ አለኝ
ያልዘሩት አይበቅልም
ያልዘራሁት በቀለብኝ ዱባ ያልኩት ቅል ሆነብኝ

ያልዘራውን የሚበላ ዝንጀሮ ነው
ያልገደለ በሽታ ምስጋና የለውም
ያልገደለ ዘማች ያልወለደ አማች
ያልጋ ሴሰኛ ሶስት ያስተኛ
ያልጠረጠረ ተመነጠረ
ያልጠሩት መካሪ ያልሾሙት ፈታውራሪ
ያልጠሩት ሰርገኛ በትረኛ
ያልጨ ድንፋታ እንጀራ እስኪቀርብ
ያልጨ ድንፋታ እንጀራ እስኪቀርብ ነው
ያልፋል እስኪያልፍ ያለፋል
ያመል ትንሽ ይጥላል በጭራሽ
ያመሰገኗት ቅል ባፏ ታፈሳለች
ያሞሌ ጥጃ በወንዙዋ ትናፋ
ያመነታ ተመታ
ያመኑት ሲከዳ ይቀላል እዳ
ያመኑት ፈረስ ጣለ በደንደስ
ያመጣሁት ውሻ ነከሰኝ ያነደድኩት እሳት ጠበሰኝ
ያመጣል አንበሴ ይበላል ኮሳሴ
ያማከሩት ዳኛ ያግዛል የመተሩበት እጅ ይወዛል
ያምላክን ነገር ምኑን አውቀሽው ወይ እኔ እበላው አንቺ አርመሽው
ያምላክን ነገር ስንቱን አውቀሽው ወይ እኔ እበላው አንቺ አርመሽው
ያምራል ብለው ለነብር ልጅ አይድሩም
ያምራል ብለው ከተናገሩት ይከፋል ብለው ያስቀሩት
ያምራል ብለው ከመናገር ይከፋል ብሎ መተው
ያምራል ብሎ ይሽልሟል ያውቃል ብሎ ይሾሟል
ያምሩዋል ይታደሏል
ያምና ሞኝ ዘንድሮም ደገመኝ
ያምናውን ዘንድሮ የአዋጁን በጆሮ
ያሞላቀቁት ልጅ አይሆንም ወዳጅ
ያሞሌ ጥጃ በወንዙዋ ትነፋ
ያረረበት ያማስል
ያረሮ ልጅ ጠለፋ
ያረሰ እንደ ልቡ ጎረሰ
ያረገዘች ታስታውቅ ከደረቷ ትታጠቅ
ያረጀን ሹም ገባር ይከሰዋል ያረጀን ጅብ አህያ ይጥለዋል
ያራስ ክፋ መበለት ያደጋ ክፋ እሳት
ያራሷን በርጉዙዋ
ያራሷን ገንፎ እርጉዙዋ ውጣ ሞተች
ያርጋጅ አናጋጅ
ያርጋጅ አንጓጅ
ያሳደግሁት ውሻ ነከሰኝ ያነደድሁት እሳት ጠበሰኝ
ያስረ ይፈታል የሰጠ ይረታል
ያስለመዱት ሰው ሁልጊዜ እጅ ያያል
ያሰቡት አይገድም ጎኔን ላርገው ጋደም
ያሳደግኋት ጥጃ አለችኝ በርግጫ
ያሳደኩት ውሻ ነከሰኝ ያነደድኩት እሳት ጠበሰኝ
ያስታርቀኛል ሙተራ እያንዳንዱ እየኮራ
ያሽላል ያሉት ኩል አይን ያጠፋል

ያቀረቡልህን ጉረስ የተረፈህን መልስ
ያበረ ወገኑን አስከበረ
ያበራሽን ጠባሳ ያየ በእሳት አይጫወትም
ያ በሬ ባላገደደ ያ በሬ ገደል ባልገባ
ያ በሬ ባገደደ ያ በሬ ገደል ገባ
ያ በሬ ባገደደ ያ በሬ ገደል ገባ ያበጠው ይፈንዳ
ያበደ ለኑሮው የፈረደ ለጉሮሮው
ያበደች ጋለሞታ እናቷን ትመታ
ያበደና የወደደ አንድ ነው
ያበጠው ይፈንዳ
ያባ ሆይ መቋሚያ ላዩ ባላ ታቹ ዱላ
ያባ ጎፍናኔ ቤቱ በረድ
ያባትህ ቤት ሲዘረፍ አብረህ ዝረፍ
ያባት ወዳጅ  የድንጊያ ገድጋጅ
ያባቱን ቢሰጡት ህይወቱ ያባቱን ቢነሱት ሞቱ
ያባቱን ያገኝ ህይወቱ ያባቱን ያጣ ሞቱ
ያባት ልጅ የደንደስ ስጋ
ያባት ልጅና ጀሮ አንድ ነው
ያባት ምርቃት አያስገባም ጥቃት
ያባት ልጅ የማድጋ ዶሮ ነው
ያባት ልጅ የማድጋ ዶሮ አንድ ነው
ያባት ሞቱን አይወዱ ረጃቱን አይሰዱ
ያባት ሞቱን አይወዱ ረድኤቱን አይሰዱ
ያባት ሲቀር ምስህ ቅበር
ያባት አገር ከሞት አያስጥልም
ያባት እርግማን ሲዳሩ ማልቀስ
ያባት እዳ ለልጅ ያፍንጫ እድፍ ለእጅ የወፍጮ እዳ ለመጅ
ያባት ወርቅ ባለዝና እህል ለቀጠና
ያባት ያምራል የባእድ ያናግራል
ያባት ያምራል የባእድ ያኖራል
ያባት ደግ ይደልላል ያባት ክፉ ለእንጀራ ልጅ ያደላል
ያባትህ ቤት ሲበዘበዝ አብረህ ዝረፍ
ያባትህና የናትህ ወገኖች ሲጣሉ ጥግህን ያዝ
ያባያ ልጅ ወዳቂ ያራኝ ልጅ አጥባቂ
ያባያ እናት አትታረድም
ያባያ ወንድሙ አይታረድም
ያባይ ምልክቱ አንደበቱ የገዳይ ምልክቱ ሽልማቱ
ያባይ እንባ አይታገድም
ያባይን እናት ውሀ ጠማት
ያባይ ውሀ ተለያየ ሲሉ ተገናኘ
ያባይን ልጅ ውሀ ጠማው የላጭን ልጅ ቅማል በላው
የአብሮ አደግ ልብ በቁና ይሰፈራል
ያብዬን እከክ ወደ እምዬ ላከክ
ያብዬን እከክ ወደ እምዬ ልክክ
ያተር ክምር የጭሰኛ ክብር
ያናጢን ልጅ ጅብ በላው የላጭን ልጅ ቅማል ፈጀው
ያንበሳ ልመና ጋማ ይዞ ነው
ያንበሳ ልመና ጋማ ይዞ የቂስ ልመና አናዞ

ያንበሳ ማላጅ ጋማ ይዞ ጅብን መውጋት አህያን ተጎዝጉዞ
ያንበሳ ማላጅ ጋማ ይዞ ጅብን መውጋት አህያን ተገን ይዞ
ያንበሳ አማላጅ ጋም ይዞ ጅብን መውጋት አህያን ተገን ይዞ
ያንበሳ ኮርዲዳና የጨዋ ልጅ ሞግዚት ከመሆን ይሰውርህ
ያንበሳ ገራም ይውላል ከላም
ያንተን የሚመስል የኔም አለኝ ቁስል
ያንቺን አትበይ ገንዘብ የለሽ የሰው አትበይ ምግባር የለሽ
ያንካሳ ልቡ ኢየሩሳሌም
ያንዱ በሬ ሲሞት ላንዱ አጋዘኑ ፍስሀው ላንዱ ሀዘኑ
ያንዱ ቤት ሲቃጠል ላንዱ ቋያው ነው
ያንዱ ቤት ሳይጠፋ ያንዱ ቤት አይለማ
ያንዱ ቤት ካልጠፋ ያንዱ ቤት አይለማም
ያንዱ ነገር ላንዱ የእንጀራ ልጁ ነው
ያንዱ አገር መልከኛ ላንዱ አገር ገባር ነው
ያንዱ ላም ወተት ያንድ እርሻ እሸት
ያንድ ሚስቱን የሺ ከብቱን
ያንድ ሰው ፍቅር ባንድ እጅ እንደማጨብጨብ ያለ ነው
ያንድ ሰው ነገር ሰምተህ አትፍረድ
ያንድ በሬ እሸት ያንድ ላም ወተት
ያንድ እርሻ እሸት ያንድ ላም ወተት
ያንድ ቀን ስህተት ለዘላለም እውቀት ነው
ያንድ ቀን ስህተት የዘላለም ጸጸት ነው
ያንድዋ እለት አንድዋ ባልቴት
ያንጎርጓሪ ጉልበት የተራጋጭ ወተት
ያኖሩት እንቅርት መለያ ይሆናል
ያኖሩት እንቅርት ያገለግላል
ያኩራፊ ምሳ እራት ይሆነዋል
ያኩራፊ ምሳው የነበረ እራት ይሆነዋል
ያኮረፈ ልብሱን አራገፈ
ያኮረፈ ምሳው እራቱ ነው
ያወረደ መአቱን ያመጣ ምህረቱን
ያወቀ ተጠነቀቀ የዘነጋ ተነጠቀ
ያወቀ ተጠነቀቀ የዘነጋ ተወጋ
ያወቀ ተጠነቀቀ ያላወቀ ተነጠቀ
ያወቀ ናቀ
ያወቀ ዘለቀ ያላወቀ አለቀ
ያወቁ ሲታጠቁ ያላወቁ ተሳቀቁ
ያዋቂ ሴት ቤት አለው ውበት
ያዋቂ አጥፊ የእስራኤል ጣፊ
ያዋቂ አጥፊ የጸመኛ ገዳፊ
ያዋጁን በጆሮ የእለቱን በቀጠሮ
ያውሬ ስጋ ለወሬ
ያውቃል ብሎ ያሚል ያምራል ብሎ ይሸልሚል
ያውቃል ብሎ ይሾሚል ያምራል ብሎ ይሸልሚል
ያው እንዳያችሁኝ ቅዳሜ የወጣሁ ይቆጡኛል ብዬ እርብ ማታ መጣሁ
ያዙኝ ልቀቁኝ
ያዛቸ ቤተ ክርስቲያን ሳሚ ያጋፋሪ ራስጌ ቋሚ
ያየ ላውራ ቢል ያልሰማ አወራ

ያየ ላውራ ቢል የሰማ አወራ
ያየ ልናገር ቢል የሰማ ላውራ አለ
ያየ ቢሄድ የሰማ ይመጣል
ያየ ቢሄድ ያልሰማ ይመጣል
ያየ ይናገራል የተወለደ ይወርሳል
ያዩትን ሊሰሩ አይናቸውን ታወሩ
ያዩትን ቢያጡ ያላዩትን ይቀላውጡ
ያያን ጨንቋራ ሁሉ ያየዋል
ያይጥ ምስክሯ ድንቢጥ
ያይጥ ሞት የድመት ሰርግ
ያይጥ እርዳታ በጭራንፎ ያልቃል
ያይጥ ፋከራ ለመከራ ድመት ምን ሊበላ
ያይጠች ዝላይ ለነአቶ ውሮ ሲሳይ
ያደረገችውን ታስታውቅ ከደረቷ ትታጠቅ
ያደፈ በእንዶድ የጎለደፈ በሞረድ
ያደፈውን በእንዶድ የጎለደፈውን በሞረድ
ያዳቀነ ሰይጣን ሳያቀስ አይለቅም
ያዳቀነ ሰይጣን ሳያቀስ አይቀርም
ያዳቀነ ሰይጣን የግል ኮሌጅ ከፈተ
ያዛቀነ ሰይጣን ሳያቀስ አይቀርም
ያዳኝ ውሻ ጠጉር ባፋ ብትር ትርፋ
ያገሩን ሰርዶ ባገሩ በሬ
ያገሩን ሰርዶ ያገሩ በሬ ይወጣዋል
ያገር ልማት የገበሬ ሀብት
ያገር ልጅ በምን ይመታል በኩበት ያም እንዳይሄድ ያም እንዳይሞት
ያገር ልጅ በምን ይማታል በኩበት ያ እንዳይሄድ ያ እንዳይሞት
ያገር ልጅ የማር እጅ
ያገር ልጅ የማር ጠጅ
ያገር እድር ለንጉስ ያስቸግር
ያገር እድር ጦም ያሳድር
ያገርህ ልጅ ብታገባት ሚስትህ ብትፈታት እህትህ
ያገርህ ልጅ ብታገባት ሚስትህ ብትፈታት እትህ
ያገርህ ዱር ፍራትን ያስወግዳል እንጂ ከሞት አያድንም
ያገርን ሰርዶ ያገር በሬ ያወጣዋል
ያገባሽስ ይፈታሻል ይብላኝ ለወለደሽ
ያገባሽ ይፈታሻል ይብላኝ ለወለደሽ
ያገባሽ ይፈታሻል ወዮለት ለወለደሽ
ያገኘ ከራሱ ያጣ ከዋሱ
ያጓኑት ድንጋይ ተመልሶ ራስን
ያጓኑት ድንጋይ ተመልሶ ራስን ይመታል
ያጣ ለማኝ ተሳድቦ ይሄዳል
ያጣጣመ የቀረጠመ
ያጣ ሰው ያገኘ አይመስለውም
ያጥንት ፍላጭ የስጋ ቁራጭ
ያፍ እማኝ አደረገኝ ለማኝ
ያፌን እስክውጥ እድሜ ይስጠኝ ይላል እርኩም
ያፍ ወለምታ በቅቤ አይታሽም
ያፍ ዘመድ በመንገድ አይገድ

ያፍላ ለማኝ አደረገኝ ለማኝ
ያፍላ የለው ቀርፋፋ
ያፍላ የለው ቀፋፋ
ይሄ እንግዳ ቸኮለ ሊያድር ነው መሰለኝ
ይህ ሁሉ ከርከሬሻ ባንቺ የተነሳ
ይህ ሁሉ ጠባሳ ባንቺ የተነሳ
ይህ አንበሳ ደም ደም አገሳ
ይህ እንግዳ ቸኮለ ሊያድር ነው መሰለኝ
ይህ ከርከሬሻ ዳቦዬን ለማንሻ
ይህን ብሰጥ ምን እውጥ
ይህን ብትሰጥ ምን ትውጥ
ይህንን ፈርቼ ደጄን በቀን ዘግቼ
ይህን ፈርቼ ደጄን በቀን ዘግቼ
ይህች ባቄላ ካደረች አትቀረጠምም
ይህች ተፍተፍ እኔን ለመመንተፍ
ይሆናል ብዬ ጎሽ ጠመድኩ የማይሆን ቢሆን ፊትቼ ሰደድኩ
ይሆን ቢሆን ዝሆን ይበላ ቢሆን
ይሉሽን በሰማሽ ገበያም ባልወጣሽ
ይሉሽን ባልሰማሽ ገበያም ባልወጣሽ
ይሉሽን ባወቅሽ ገበያም ባልወጣሽ
ይሉ አይሉ የት አለ ቅሉ
ይሉሽን ብትሰሚ ጎንደር ላይ ክረሚ
ይሉኝ አይል ውሽማ ዶሮ ሲጮህ ይማለላል
ይሉኝ አይል የኋላውን አያይ
ይሉኝ አይል ጸሀፊ ከሙሴ ይገድፋል
ይሉኝታ ተፈርቶ እስከመቼ ተቀራምቶ
ይሉኝታና መጠቀም ባንድነት አይገኙም
ይሉኝታ የራስ አሊን ቤት ፈታ
ይመሰክረዋል ለነፍሱ ይፈተፍተዋል ለከርሱ
ይመስል አይመስል የጠይብ እጅ ተከሰል
ይመታሉ የሚጠሉ ይመስል ይስማሉ የሚወዱ ይመስል
ይሙት የገደለ ይካስ የበደለ
ይማሩኝ እያልክ ከምትታማበት አትገኝ
ይማሰላል ካሉ ይዛመዳል አይገድም
ይሰጠኝ መስሎ ሊሸጠኝ
ይሰጡኛል ብሎ ከሰጠ ቀጥቦ የበላ በለጠ
ይሰጡ ብሎ ከሰጠ ቀጥቦ የበላ በለጠ
ይሰጣል መስሎ ይሸጣል
ይሰብረኝ ይሰንጥረኝ የሚሉ የሰውን ልብ ሊሰብሩ
ይቅር ለእግዜር ወድቆ እማይሰበር
ይቅር ለእግዜር ወድቆ አይሰበር ሞቶ አይቀበር
ይቅደም ደግነት ይከተል ቸርነት
ይበላ እንደ ቤቱ ይሰራ እንደ ጉልበቱ
ይበላ እንደ ቤቱ ይሰራ እንደ ጎረቤቱ
ይበላው ካጣ ይበላበት ያጣ
ይበጃል ያሉት መድሀኒት አይን አጠፋ
ይበጃል ያሉት ኩል አይን አጠፋ
ይብላ እንደ ቤቱ ይስራ እንደ ጎረቤቱ

ይብላኝ ለወለደሽ ያገባሽስ ይፈታሻል
ይብራና ይብራ ተጣሉ በሰው ሸንብራ
ይታደሏል እንጂ ይታገሏል
ይታደሉታል እንጂ አይታገሉትም
ይቺ ባቄላ ያደረች እንደሆን አትቆረጠምም
ይቺን ለኛ ጥሬን ለጌኛ
ይቺም ቂንጥር ሆና ቡታንታ አማራት
ይቺን በላህ ብለህ ጦሜን አታሳድረኝ አለ አሉ
ይውደደኝ የጀርባዬ ቅማል አለች አንዷ
ይገርማል አህያ ከዥብ ይከርማል
ይደንቃል ይገርማል አህያ ከዥብ ይከርማል
ይኖሩዋል በደጋ ይተኙዋል በአልጋ
ይወልደዋል ካሉ ይመስለዋል አይገድም
ይውጋሽ ብሎ ይማርሽ
ይጥሉህ አትጥላቸው ይበድሉህ አትበድላቸው
ይጠላኝ ይመስል ይመታኛል ይወደኝ ይመስል ይሰመኛል
ይወደዋል ካሉ ይመክሩዋል ይወልደዋል ካሉ ይመስሏል
ይውጋህ ብሎ ይማርህ
ይውጋህ ብሎ ይማርክህ
ይገርመኛል ገንፎ ከራቴ ተርፎ

ደ
ደሀ ሰው ዶሮ ካረደ ከሁለት አንዳቸው ቢታመሙ ነው
ደሀና ሲታጣ ይመለመላል ጎባጣ
ደሀና ወገን ያጣ ወየው ያለበት ጣጣ
ደሀና ጦር ያለው ለግምብ ይሞክረው
ደመና ለዝናብ ድግስ ለሆዳም
ደመና በሰማይ የጨዋ ልጅ በአደባባይ
ደመናን የጨበጠ ሰማይን የቧጠጠ የለም
ደመወዙ ስንዴ ስራው ምን ግዴ
ደመወዝ ያጣ ሎሌ ይኮበልላል በሀምሌ
ደም ቢያለቅሱ ድንጋይ ቢነክሱ
ደም ተቀብቶ ዝንብ አይፈሩም
ደም ተቃብቶ ዝንብ አይፈሩም
ደም ተበክለህ ዝንብን አትጥላ
ደም ከውሀ ይቀጥናል
ደም ካልፈሰሰ ስርየት የለም
ደሞዝተኛ አርፈህ ተኛ
ደረስሁ ልጅ ፈላሁ ጠጅ
ደረቅ ይቀመጠላል እርጥብ ይጎብጣል
ደረቴን ቢያመኝ እግሬን አገመኝ
ደረቴን ሲያመኝ እግሬን አገመኝ
ደረጃ ለፍቶ መሄጃ
ደስታና መከራ ቀኝና ግራ
ደስታና መከራ ቀኝና ግራ ናቸው
ደባ ራሱን ስለት ድጉሱን
ደባ ራሱን ስለት ድጉሱን አያጣውም

ደባል ሲሰነብት ይሆናል ባለቤት
ደባልና ሹመት ያለሰበብ አይሄድ
ደብር ለላሰታ ድግድግታ ለጌታ
ደብተራ ሲኮራ እቤት ክርስቶያን ገብቶ ጭራ ይይዛል
ደብተራ የዘኬ ጎተራ
ደብተራ የዘኬ ጎተራ ዘኬውን ሲቋ ጥር አነቀው ነብር
ደብተራና ተማሪ ሰናፊልና ሱሪ
ደንቆሮ ከሚያጫውተኝ የሚሰማ ያውጋኝ
ደንቆሮ የሰማ ለት ያብዳል
ደወል ላንበሳ ባማረለት ታዲያ ማን ይሰርለት
ደወል እንደ ጠዋቱ ትጬሀ ለች
ደጃቸውን አይዘጉ ሰውን ሌባ ይላሉ
ደጃቸውን ከፍተው ሰውን ሌባ ይላሉ
ደጃፉን ጥሎ በጓሮ ይመጣል
ደገኛ ሲያርስ ቀለኛ ያነፍስ
ደጉ ነገር ሳያልቅ ክፉ መናገር
ደግ ሰው ከንጀራው ቀርሶ ከወጡ አጥቅሶ
ደግ ሳይበላ ክፉ ይመራ
ደግ ጌታ ሲለግስ እንደ ፏፏቴ ያርስ
ደግ ጎረቤት ውሻና ድመት ያሳድጋል
ደግና ማለፊያ ትግልና ልፊያ
ደግ አማችን መጠር ክፉ አማችን በጠር
ደግ አባት እርስት ያቆማል ክፉ አባት እዳ ያቆያል
ደግነት አይታረስ ልጅነት አይመለስ
ደግ ጎረቤት እቃ አያስገዛም
ደግ ጎረቤት ያወጣል ከመአት
ደካማ ቀበሌ በአህያ ይወረራል
ደፋር ሴት ጉልቻ ረግጣ ትወጣለች
ደፋር ወጥ ያውቃል
ደፋርና ጭስ መውጫ ቀዳዳ አያጣም
ደፋርና ጭስ መውጫ አያጣም
ደፋርና ጭስ ምን ያመጣሉ
ደፋርና ጭስ ዝዋይ ገቡ
ዱርዬ ያገባ በሬው በሰኔ ገደል የገባ
ዱላ ለባለጌ ምርኩዝ ለአሮጌ
ዱላ የሚጠላው ሽክላ ብቻ ነው
ዱላን ይዞ ሌባን መጠየቅ
ዱላ ይዞ ሌባን መጠየቅ
ዱባ ባገሩ ጋን ያህላል አሉ
ዱባና ቅል አበቃቀሉ ለየቅል
ዱባና ቅል አበቃቀሉ አንድ ይመስላል አበላሉ ለየቅሉ
ዱባና ቅል አብሮ ይበቅል አበላሉ ለየቅል
ዱቄት ባመድ ይስቃል
ዱጨት ባመድ ይስቃል
ዲያቆን ሲጠግብ በጧፍ ይማታል ወይፈን ሲቦርቅ ድንበር ያፈርሳል
ዲያቆን ከዘፈነ ፍየል ከቀዘነ
ዲያቆን ከዘፈነ ፍየል ከቀዘነ መዳኛም የለው
ዲያቢሎስ በክፋቱ ተወጋ ዳቢቱ

ዳሩ ምን ይሆናል ሆነና ሆነና
ዳር ሲፈታ መሀል ዳር ይሆናል
ዳር ዳር ያለ በመሀል የከበረ
ዳቦ ሲበሉ ልብ ልቡን ዳገት ሲወጡ ጥግ ጥጉን
ዳቦ በገና ቡና በጀበና
ዳቦ በወጥ በግዜር ማምለጥ
ዳቦ ካልበሉት ድንጋይ ሎሚ ካልመጠጡት እንቧይ
ዳቦ ያለ ቅርፊት ጠላ ያለ ምርጊት
ዳቦውን ጎርሶ ደሙን አብሶ
ዳተኛ በሬ ሀብታም ነው
ዳኛ ለዳኛ ያወርሳል ጉም ተራራ ያለብሳል
ዳኛ ምን ያደላ ከተረታ ሊበላ
ዳኛ ምን ያደላ ከተረታው ሊበላ
ዳኛ ሲመረምር ከራስ ይዞ እስከ እግር
ዳኛ ሲቆጣ ማር ይዞ ከደጁ
ዳኛ ሲያዳላ በዳኛ አሀያ ሲያጋድል በመጫኛ
ዳኛ ሳለ ተናገር ውሀ ሲጠራ ተሻገር
ዳኛ ሲገኝ ተናገር ውሀ ሲጠራ ተሻገር
ዳኛ ሰበር በእጅ ክበር
ዳኛ ቢንቁ የተያዘ እሀልን ይወቁ
ዳኛ ቢንቁ የተያዘ እሀል ይወቁ
ዳኛ ቢያዳላ በዳኛ አሀያ ቢያጋድል በመጫኛ
ዳኛ ቢያጋድል በዳኛ አሀያ ቢያጋድል በመጫኛ
ዳኛ አውጥቼ ዘንግ አቅንቼ
ዳኛ አይነቀፍ እሳት አይታቀፍ
ዳኛ ካዳላ ጭነት ቀላል
ዳኛ የወል ምሰሶ የመካከል
ዳኛ የወል ምሰሶ የማሃል
ዳኛ የፈረደበት መርከብ የተሰበረበት
ዳኛ የፈረደው ስለት የቀደደው
ዳኛ ያደላበት እሳት የበላበት
ዳኛ ያፈሰሱለት ፈረስ የከሰከሱለት
ዳኛ ይመረምራል ጣዝማ ይሰረስራል
ዳኛና በሬ ሀብታም ነው
ዳኛ ፍርድ አይከላ እሀል ጎታ ይሞላ
ዳኛን ቢንቁ የተያዘ እሀልን ይወቁ
ዳኞች ከመረመሩ ይናገራል ምድሩ
ዳኞች ከመረመሩ ይናገራል ምድሩ ይገናል ነገሩ
ዳኞች ከመረመሩ ይገኛል ነገሩ
ዳዊትን ያሀል መዝሙር ጨለማን ያሀል ጥቁር (የለም)
ዳክዬን ከውሀው ፈረስን ከገለባው
ዳኛ ሲገኝ ተናገር ውሀ ሲጠራ ተሻገር
ዳገት ሲወጡ ጥግ ጥጉን ዳቦ ሲበሉ ልብ ልቡን
ዳገት እርሙ ሜዳ ወንድሙ
ድሀ ለወዳጁ አይሰንፍ ሀብታም ካለወዳጁ አይተርፍ
ድሀ ሲቀልጥ አመድ አመድ ይሸታል
ድሀ ሲቀመጥ እጁን ይዘሀ አወዛውዘው
ድሀ ሲቀማጠል ከወገቡ ቀምጠል

ድህ ሲቀማጠል ከወገቡ ቅምጥል
ድህ ሲቆጣ እግሩ ይፈናጠራል
ድህ ሲቆጣ እግሩ መንገድ ያሰልጣል
ድህ ሲቆጣ ከንፈሩ ያብጣል መንገዱን ያሰልጣል
ድህ ሲቆጣ መንገድ ያፈጥነዋል
ድህ ሲናገር ሬት ኮሶ ሀብታም ሲናገር የማር በሶ
ድህ ሲንቀባረር ያለቀሰ ይመስላል
ድህ ሲያገኝ ያጣ አይመስለውም
ድህ ቅቤ ወደ ማን ሊሸከም ነዶ
ድህ በህልሙ ቅቤ ባይጠጣ ኑሮ እከክ ይወረው ነበር
ድህ በህልሙ ቅቤ ባይጠጣ ኖሮ እከክ ይጨርሰው ነበር
ድህ በህልሙ ቅቤ ባይጠጣ ኖሮ እከክ በወረሰው
ድህ በህልሙ ቅቤ ባይጠጣ እከክ ይጨርሰው ነበር
ድህ በህልሙ ቅቤ ባይጠጣ እከክ በፈጀው
ድህ በሽታ አያውቅም ሀብታም ጤና የለውም
ድህ ተበድሎ ማሩኝ ይላል ቶሎ
ድህ ውሃውን ጠጥቶ እሳቱን ይሞቃል ሀብታም ስለገንዘቡ ይጨነቃል
ድህና ድመት ሊሞት ሲል ያምርበታል
ድህና ገበያ ሳይገናኙ ይሞታል
ድህ በአመዱ ንጉስ በዘውዱ
ድህ በጉልበቱ ባለጸጋ በሀብቱ
ድህ ቢናገር አያደምቅ ቢጨብጥ አያጠብቅ
ድህ ባይ አይኔን አመመኝ
ድህ ተበድሎ ማሩኝ ይላል ቶሎ
ድህ ተበድሎ ራሱ ይታረቃል ሀብታም በድሎ ተመልሶ ይስቃል
ድህ ከንቡ ይዳላ
ድህ ከንቡ ይዳራ
ድህ ካለቀሰ ቀኑ መች አነሰ
ድህ ካልሰራ ዶሮ ካልጫረ
ድህ ካልጋረ ዶሮ ካልጫረ
ድህ ካልዘራ ዶሮ ካልጫረ
ድህ ካልዘራ ዶሮ ካልጫረ (ማን ያበላው ነበረ)
ድህ ከርሻ ዳቦዬን ለማንሻ
ድህ የሚበላው እንጂ የሚከፍለው አያጣም
ድህ በጉልበቱ ባለጸጋ በሀ ብቱ
ድህ በጉልበቱ ባለጸጋ በከብቱ
ድህ ያልፍልኛል ይላል ጌታ ቀኑን ይቆጥራል
ድህ ያመልክት ዳኛ ያሟግት
ድህና ሹም ተሟግቶ ድንጋይና ቅል ተማትቶ የማይሆን ነው ከቶ
ድህና ጌታ ተሟግቶ ድንጋይና ቅል ተማትቶ የማይሆን ነው ከቶ
ድህ ምን ትሰራለህ እንጂ ምን ትበላለህ የሚለው የለም
ድህ ሲያስለቅሱ ከስላሴ ይወቀሱ መንግስተ ሰማያትን አይወርሱ
ድህ ቢያስለቅሱ ከስላሴ ይወቀሱ መንግስተ ሰማያትን አይወርሱ
ድሀን ካስለቀሱ በስላሴ ዘንድ ይወቀሱ
ድሀን ፈርቼ ደጄን በቀን ዘግቼ
ድህነት ከአምላክ መስማማት
ድህነት ከአምላክ መስተካከል
ድል በመታደል ሙያ በመጋደል

ድል የባለ እድል
ድል እድል በአንድ ድልድል
ድል ድል እድልህ እንዳይጎድል
ድመት ላመሏ ዛፍ ላይ ትወጣለች
ድመት መንኩሳ መናከሷን አትረሳ
ድመት መንኩሳ አመሏን አትረሳ
ድመት በታች ከሆነች ውሻ ታሸንፋለች
ድመትና ቁንጫ ባዶ ቤት ይወዳል
ድመትና አይጥ እሳትና ጭድ
ድመትን በቆሎ መጠርጠር
ድመትን አይጥ ገደለቻት ወይ ጥቃት ወይ ጥቃት
ድመት ውስጥ ውስጡን አውሬ ናት
ድምቢጥ እንደ አቅሟ በብር ትታገማለች
ድምቢጥ እንደ አቅሟ በብእር ትታገማለች
ድምጽና ቁንጫ ባዶ ቤት ይወዳል
ድሪቶ ከነቅማሉ መጥፎ ሰው ከነአመሉ ወዲያ በሉ
ድሪያ የዝሙት ዋዜማ
ድር ቢያብር አንበሳ ያስር
ድርብርብ እንደ ደጋ ንብ
ድርና ማግ ለሀጭና ልጋግ
ድር ቢያብር ጋቢ ይሰራል
ድር ቢያብር አንበሳ ያስር
ድርጎ ራቱ ድርጎ ቢቀር ሞቱ
ድርጎ የለመደች መበለት ወተት ያየች ድመት
ድርጭት ፈንጠር ምዝግዝግ ጎንደር
ድሮም እንዳይሆን ነው የቄስ ልጅ መኮነን (አለ)
ድሮም እንዳይሆን ነው የቄስ ልጅ መኮንን (አለ)
ድሮ ካያታችን ካጤ ነው ትውልዳችን
ድሮም ሌባ ሲሰርቅ እንጂ ሲካፈል አይስማማም
ድስት ግጣሙን አያጣም
ድበላ አንዳንድ ጊዜ ይበላ
ድንቢጥ እንደ አቅሟ በብእ ር ትታገም
ድንቀኛ ተኳሽ ድር ይበጥሳል
ድንቁርና ከልብህ መካከል ተራራ ያህል
ድንኳን ያየ ባለጌ
ድንኳን ገልጦ ዙፋንን ረግጦ
ድንኳን ገልጦ ዙፋን ረግጦ
ድንኳን ገልጦ ዙፋን አጊጦ
ድንገተኛ ስህተት የቁልቁለት ውድቀት
ድንጋይ ለረገጠ ፍለጋ የለውም ውሀ ለጠጣ ሽታ የለውም
ድንጋይ ላይ ተቀማጭ የባለጌ ተለጣጭ
ድንጋይ በድንጋይ ላይ ትልቅ ቤት ይሆናል
ድንጋይ ቢያጎኗት ተመልሳ ካናት
ድንጋይ ወርዶ እዘብጥ ያርፋል ያገኘው ይተርፋል
ድንጋይ ሲያረጅ መጭ ያበቅላል
ድንጋይ ወደ ሰማይ ቢወርወር ተመልሶ ምድር
ድንጋይ ወደ ሰማይ ቢወርወር ተመልሶ ወደ ምድር
ድግርና ገባር ሲተካከል ያምር

ድግስ የሌለው ዋዜማ ምልክት የሌለው ዜማ
ድጥ ማንሸራተቱን ባለጌ ማሽሟጠጡን አይተውም
ዶማ ለመማሻ ማረሻ ለመፈለሻ
ዶሮ ላትበላው ታፈስ
ዶሮ ልጆቹዋን ይዛ ጓሮ ለጓሮ
ዶሮ ባሏ ሲሞት ሞተች እጢስ ገብታ
ዶሮ ሲሉ ሰምታ ሞተች እጢስ ገብታ
ዶሮ ሲቀጣጥቧት በመጨኛ ጣሏት
ዶሮ ሲደልሏት በመጨኛ ጣሏት
ዶሮ በልቶ ብስና ጎመን በልቶ ጤና
ዶሮ በልቶ ከብስና ጎመን በልቶ በጤና
ዶሮ በልጅዋ አንጀት ትጫወታለች
ዶሮ በማሰሮ ገደል ለዝንጀሮ
ዶሮ በጋን
ዶሮ ቢጠፋ ከቤቱ መነኮሰች እናቱ
ዶሮ ቢጠፋ ካባቱ መነኮሰች እናቱ
ዶሮ ቢያማት በሬ ተሳሉላት
ዶሮ ብታልም ጥሬዋን
ዶሮ ብትታመም በግ አረዱላት
ዶሮና ቀበሮ ተገናኝተው ጓሮ
ዶሮና ቀበሮ ተገናኝቶ ጓሮ
ዶሮን ሲያታልሏት በመጫኛ ጠልፈው ጣሏት
ዶሮን ሲያታልሏት በመጫኛ ጣሏት
ዶሮን ሲያታልሏት አንቺ እሩጭ እኛ እንከተልሽ አሏት
ዶሮን ሲያታልሏት ጥምር መንግስት አሏት
ዶሮን ሲያታልሏት ፎቶ አነሷት
ዶሮ አንዱን እንቁላል በወለደችበት ወታቦ ትሞላለች
ዶሮ እቤት ውላ ዝናብ ትመታለች
ዶሮ እኔ ባልበላው ጭሬ አላፈሰውም ወይ አለች
ዶሮ እኔ ባልበላ ጭሬ አላፈስም ወይ አለች
ዶሮ ከቆጥ በሬ ከጋጥ
ዶሮ ከቤት ሆና ዝናም ይመታታል
ዶሮ ከቤት ውላ ዝናብ ይመታታል
ዶሮ ከጋጥ አህያ ከቆጥ
ዶሮ ከጋጥ በሬ ከቆጥ
ዶሮ ከጨኸ ሌሊት የለም ከደብረ ታቦር ወዲያ ክረምት የለም
ዶሮ ከጨኸ ሌሊት ከደብረ ታቦር ወዲያ ክረምት የለም
ዶሮ ከጨኸ የለም ሌሊት ከቡሄ ወዲያ የለም ክረምት
ዶሮ ካልበሏት አሞራ ናት
ዶሮ ጭራ ማረጃዋን አወጣች
ዶሮ ጭራ መታረጃዋን አወጣች
ዶሮ ጭራ የምታወጣው ምስጢር
ዶሮ ጭራ ጭራ አወጣች ማረጃዋን ካራ
ዶክተር ሲበዛ በሽተኛ ይሞታል

ጀ

ጀማሪ ይፐፋ ሰካራም ይትፋ

ጀምሮ የማይፈጽም ፈጭቶ የማያልም

ጀምሮ ይጨርሳል ለጉሞ ይተኩሳል

ጀምሮ ይጨርሳል አልሞ ይተኩሳል

ጀምበር ሳለ እሩጥ አባት ሳለ አጊጥ

ጀርባ ለባለቤቱ ባእድ ነው

ጀርባዬን አሳከከኝ ተንጠራርቼ ማከክ ተሳነኝ

ጀርባዬን እከከኝ ለኔ ራቀኝ

ጀርባዬን እከክልኝ ለኔ ራቀኝ

ጀግና የሚታወሰው ወይም ከሞተ ወይም ከተለየ በኋላ ነው

ጀግናን ከደረቱ አበባን ከአናቱ

ጃርት ያስደነገጠው ዱባ ይመስላል

ጅል ስለላ ላይ ሄዶ ምግብ ቢቀርብለት ስለላ ላይ ነኝ ብሎ .እርፍ

ጅምርን ለነገ አያሳዩም

ጅምር ይጨረሳል ልጉም ይተኩሳል

ጅራትና ሀሜት በሰተኋላ ነው

ጅራትና ጉድ በስተኋላ ነው

ጅራትና ጉድ ከወደኋላ ብቅ ይላል

ጅራቷ ታደርሰኝ ካናቷ

ጅራቷ ታደርሳለች ከናቷ

ጅራፍ መትቶ ያለቅሳል ባለጸጋ በድሎ ተመልሶ ይወቅሳል

ጅራፍ እራሱ ገርፎ እራሱ ይጮሃል

ጅራፍ እሱው ይገርፍ እሱው ይለፍ

ጅራፍ እሱው ይገርፍ እርሱው ይለፊልፍ

ጅብ ምን ይመስላል እግሩ ያነክሳል አፉ ይነክሳል

ጅብ ሲበላህ በልተሀው ተቀደስ

ጅብ ባጥንት የተገደገደ በጅማት የተማገረ ቤት አለ ቢሉት ወዴት ነው ሳይል ገደል ገብቶ ሞተ

ጅብን ለመግደል ከአህያ ተጠለል

ጅብን ሲወጉ በአህያ ይጠጉ

ጅብ ከላይ ውሀ ሲጠጣ ከታች ያለችውን አህያ አታደፍርሽብኝ አለ

ጅብ ከማያውቁት አገር ሄዶ ቁርበት አንጥፉልኝ ይላል

ጅብ ኪበላህ ጅብ በልተህ ተቀደስ

ጅብ አጥንት ባየበት ይመላለሳል

ጅብ አያውቁት አገር ሄዶ ቁርበት አንጥፉልኝ አለ

ጅብ እማያቁት አገር ሄዶ ሩም ሰርቪስ ያዛል

ጅብ እማያቁት አገር ሄዶ ቴሌ ሴንተር ከፈተ

ጅብ እሰር ብሎ ተሰሮ ገባ

ጅብ እስኪነክስ ያነክስ

ጅብ እንኳን ጓደኛውን ይጣራል

ጅብ እንኳን ጓደኛውን ይጠራል

ጅብ እንደቁመቱ ልብ የለውም

ጅብ እንዳባቱ ይዘርጥጥ

ጅብ እንዳባቱ ይዘርጥጥ አህያ እንደአባቱ ይፈርጥጥ

ጅብ እንዳገሩ ይጮሀል

ጅብ እንዳገሩ ይጮሀል የደላው ሙቅ ያኝካል

ጅብ እንደጉልበቱ ልብ የለውም

ጅብ ታኮተኮተ ሰው ከተከተተ
ጅብ ከሚበላህ በልተህ ተቀደስ
ጅብ ካኮተኮተ ሰው ከተከተተ
ጅብ ውሀ ሲጠጣ ታች ያለችውን አህያ አታደፍርሽብኝ አለ
ጅብ የማያውቁት አገር ሄዶ ቁርበት አንጥፉልኝ አለ
ጅብ የኔ ነው ስለው ወናፎን ቀማኝ
ጅብ ጥጃቹን ጠብቅ ሲባል ይጠፉብኛል አለ
ጅብና ሽማኔ ከጉድጓድ አይወጡም
ጅብና እህል ሳይተዋወቁ ይኖራሉ
ጅብን ሊወጉ ካህያ ይጠጉ
ጅብን ሲወጉ ባህያ ይጠጉ
ጅብን ከምን መታኸው ከአፉ አሰፋሁለት
ጅብን ፈርቼ ከዛፍ ብወጣ ነብር ቆየኝ
ጆሮህ የት ነው ቢሉት እዚህ አለ አሉ
ጆሮ ለባለቤቱ ተቃዋሚ ሆነ
ጆሮ ምነው አታድግ ቢሉት ጉድ እየሰማሁ በየት ልደግ አለ
ጆሮ ለባለቤቱ ባዳ ነው
ጆሮ በላ ሆድ ጠሙን አደረ
ጆሮ ባይጠም ይመስላል ሆዳም
ጆር አይጠምም አይን አይጠግብም
ጆሮ እዳውን አይሰማም
ጆሮ ካያት ያረጃል
ጆሮ ካያቱ ያረጃል
ጆሮ የሰማውን ለማየት ይሄዳል አይን
ጆሮ የሰማውን ለማየት አይን ይንከራተት
ጆሮ የሰማውን ልብ ያውቀዋል
ጆሮ የሰማውን ልብ ያውቃል
ጆሮ የቀድሞዎቹ እኩያ ነው
ጆሮውን ቢቀርጡት መስሚያው ይቀራል
ጆሮ ያለው ይስማ የሰማ ያሰማ
ጆንያን ያቆመው እህል ነው

ገ
ገላጋይ አጥቼ ግልገሌን በላኋት
ገለፈንት የሴት ጋለሞታ
ጉድ ነሽ ያንኮበር ቅጠል በየሄድሽበት ነገር ማንጠልጠል
ጋን በጠጠር ይደገፋል
ግም ለግም አብረህ አዝግም

ጠ
ጠላትህን ውሀ ሲወስደው እንትፍ ብለህ ጨምርበት
ጠርጥር በገንፎ ውስጥ እንዳለ ስንጥር
ጠበንጃ ራሱ መቶ ራሱ ይጮሀል
ጠንቋይ ለራሱ አያቅም
ጡጥም ከፈስ ተቆጠረች
ጤፍ ከአቅሙ እንክርዳድ ከፈለ
ጤፍ ከዘመዷ ጎታ ትሞላ
ጥልቅ ብዬን ውሀ ወሰዳት

ጥርሴስ ልማዱ ነው አይኔን አታስቀው
ጥርሴስ ልማዱ ነው አይኔን አታስቂው
ጥርስና ከንፈር ሲደጋገፍ ያምር
ጥርስ የሌላት ጥርስ ያላትን ነክሳ አነካክሰ ታስተምራለች
ጥቂት ያለው ሁሉ ብርቁ ነው
ጥንቸልም ለሆዷ ዝሆንም ለሆዱ አብረው ውሀ ወረዱ
ጥይትና ማጣትን ተኝቶ ማሳለፍ ነው
ጥጃ ቢፈነጭ በሜዳ ውሀ ቢሄድ በጎድጓዳ
ጥጃ ቢፈነጭ በሜዳ ውሀ ቢሮጥ በጎድጓዳ
ጥጋበኛ ከርከሮ የነፍጠኛ ጎጆ ይታከካል
ጥጋበኛንና ውሀ ሙላትን ቁመህ አሳልፈው
ጦር ሲመጣ ዛቢያ ቀረጣ
ጦጣ መጀመሪያ የመቀመጫዬን አለች አሉ
ጦጣ ባለቤቱን ታስወጣ

## ጨ

ጨረቃ ሲጠፋ ኮከብ አባወራ ይሆናል
ጨዋነሽ ቢሏት ሳቁ ገደላት
ጨው ለራስህ ብለህ ጣፍጥ አለበለዚያ ድንጋይ ነው ብለው ይወረውሩሀል
ጨንገራ ለመፍጨት አንጀት ለመጎተት በለው ዋተት ዋተት
ጨማ የለኝም ብለህ አትዘን ካልሲ የሌለው አለና
ጨማ የለኝም ብለህ አትዘን እግር የሌለው አለና
ጭድ ይዞ እሳት ሳል ይዞ ስርቆት
ጭድ ይዞ ወዘት ሳል ይዞ ስርቆት

## ጰ

ጳጉሜ ሲወልስ ጎተራህን አብስ
ጳጉሜ ሲወልስ ገበሬ ጎተራህን አብስ
ጳጉሜ ቢለግስ ጎታህን አብስ

## ጸ

ጸሀይ ሳለ ሩጥ አባት ሳለ አጊጥ
ጸሀይ ብልጭ ወፍ ጭጭ ሲል
ጸሀይ ካልወጣ ከሰፈረበት አይነሳ አንበጣ ሴት ምክንያት አታጣ
ጸሀይ የጠዋት አዱኛ የሽበት
ጸሀይ ያየውን ሰው ሳያየው አይቀርም
ጸሀይና ንጉስ ሳለ ሁሉም አለ
ጸሎት በጽሞና ነገር በደመና
ጸሎት በፍቅር ሀይማኖት በምግባር
ጸሎት ከፍቅር ሀይማኖት ከምግባር ይበጃል
ጸሎት ከፍቅር ሀይማኖት ከግብር
ጸሎት ያለፍቅር ሀይማኖት ያለግብር አይረባም
ጸጸት እያደር ይመሰረት
ጻድቃን ሳይቀጣጠሩ ይገናኛሉ
ጻድቃን ሳይቀጣጠሩ ይገናኛሉ ሀጥአን ግን በተቃጠሩበት ይተጣጣሉ
ጸዋ በተርታ ስጋ በገበታ

ጽድቁ ቀርቶብኝ በቅጡ በኮነነኝ
ጽድቁ ቀርቶብኝ በውሉ በኮነነኝ
ጽድቅ ለመንኳሽ ቀኝ ለከሳሽ
ጽድቅ እንደ ላሊበላ እድሜ እንደ ማቱሳላ ይስጥህ
ጽህፈት በብራና ዘፈን በበገና
ጾማ ጾማ ለጸሎተ ሀሙስ እርጎ ትልስ
ጾም ገዳፊና ሰው ጠባቂ ለጥቂት ይሳሳታል

ፈ

ፈላ ገነፈለ ተሞላ ጎደለ
ፈረሰኛ ሲሮጥ እግረኛን ምን አቀመው
ፈረሰኛ ሲሸሽ እግረኛን ምን አመጣው
ፈረሰኛ የወሰደውን እግረኛ አይመልሰውም
ፈረሱም ይኸው ሜዳውም ይኸው
ፈረስ ሲያጠብቅ ልጓም አይለቀቅ
ፈረስ በራሪ በቅሎ ሰጋሪ
ፈረስ ቢያነክስ አህያ ታጉዝ
ፈረስ ቢጠፋው ኮርቻውን ገልቦ አየ
ፈረስ አውቃለሁ ስገታ እወድቃለሁ
ፈረስና ገብስ ያጣላል
ፈረስ ያደርሳል እንጂ አይዋጋም
ፈረስ ጥሎ ይደነግጣል በቅሎ ጥሎ ይረግጣል
ፈረስ ጥሎ ይደነግጣል አህያ ጥሎ ይረግጣል
ፈረንጆች እንደመርፌ ይገቡ እንደዋርካ ይሰፉ
ፈሩ ፈሩ ማጀት አሩ
ፈሩ ፈሩ ማጀት አደሩ
ፈሪ ለናቱ
ፈሪ ለናቱ ይገባል
ፈሪ ለናቱ ጀግና ለጀግንነቱ
ፈሪ በገዛ ጠቡ ገላጋይ ይሆናል
ፈሪ ቢሸፍት እስከ ጓሮ
ፈሪ እንዳይሉኝ አንድ ገደልሁ ጀግናም እንዳይሉኝ አልደገምሁ
ፈሪ ከውሀ ውስጥ ያልበዋል
ፈሪ ካልጋ ላይ ይወድቃል
ፈሪ ካልጋ ላይ ወድቆ ይሞታል
ፈሪን ውሀ ውስጥ ያልበዋል
ፈሪ ውሀ ውስጥ ሆኖ ያልበዋል
ፈሪ ውሀ ውስጥ ያልበዋል
ፈሪ የሚያባርረው ሳይኖር ይሸሻል
ፈሪ የናቱ ልጅ ነው
ፈሪ ፈራና እጉድባ ቢኛ ጆሮውን በላው ያይጥ ቀበኛ
ፈሪ ፈራና እጉድባ ቢተኛ ጆሮውን በላው ያይጥ ቀበኛ
ፈርተው ድንጋይ ሲጥሉ ጅብ ወጣ ከዱሩ
ፈርተው ድንጋይ ቢጥሉ ጅብ ወጣ ከዱሩ
ፈርተው ድንጋይ ቢወረውሩ ጅብ ወጣ ከዱሩ
ፈሷን ፈስታ ቂጧን ጨበጠች
ፈስ በወረንጦ እየተለቀመ ነው
ፈስቶ ቂጥን መያዝ

ፊስ ያለበት ቂጥ ዝላይ አይችልም
ፊስ ያለበት ዝላይ አይችልም
ፊትል ሲረዳዳ አንበሳ ያስራል
ፊትል ሲረዳዳ አንበሳ ያስቀራል
ፊክሮ መሸሽ ታሪክ ያበላሻል
ፊዛዛ እያንቀላፋ ይገባል ፊፋ
ፊጅቶ ከሚያጠግበኝ እስቲበርድ ይራበኝ
ፊጅቶ ከሚያጠግበኝ እስኪበርድ ይራበኝ
ፊገግታ የልብ አለኝታ
ፊጣሪን የሚያህል ጌታ ርስትን ያህል ቦታ
ፊጣሪን የሚያህል ጌታ ገነትን ያህል ቦታ
ፊጥነው የገመዱት ፊጥኖ ይበጠሳል
ፊጥኖ መስጠት ኋላ ለመጸጸት
ፊጥኖ መስጠት ቶሎ ለመጸጸት
ፊጥኖ መስጠት በኋላ መጸጸት
ፊጭታ የነበረች ላመልማሎ ኮራች
ፊት ያሞጠሙጧል ኋላ ያፏጨዋል
ፍሪክና ጻድቅ አይቀጣጠርም
ፍሬ በመስጠቱ ባልታወቀ ሾላ የወፎች ዝማሬ ቀደመ አሉ
ፍቅር ሲጠና ቀሎ ያጓርሳል
ፍቅርና ጉርሻ ካላስጨነቀ አያምርም
ፍቅር ካለ ዘጠኝ ቂጣ ለባልና ሚስት ይበቃል
ፍቅር ፍቅር ሲሉ ደሀ ሆነው ቀሩ
ፍየል ሁለት ወልዳ አንዱ ለመጽሀፍ አንዱ ለወናፍ
ፍየል ላምስት ዶሮ ለባልና ለሚስት
ፍየል መንታ ወልዳ አንዱ ለመጽሀፍ አንዱ ለወናፍ
ፍየል መንታ ትወልድና አንዱ ለወናፍ አንዱ ለመጽሀፍ
ፍየል ሲሰባ ሾተል ይልሳል
ፍየል በልታ በበግ አበሰች
ፍየል በልታ በበግ አሳበበች
ፍየል ሲቀናጣ እናቱን ይሰራል
ፍዬል በግርግር እናቱን ይሰራል
ፍዬል በግርግር እናቱን ይሰር
ፍየል ከመድረሷ ቅጠል መበጠሷ
ፍየል ከቀዘነ ዲያቆን ከዘፈነ
ፍየል የለኝ ከነብር ምን አጣላኝ
ፍየልና ቀበሮ ምጥማጥና ዶሮ
ፍየሏን እንደበግ
ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ
ፍዳ ለሀጥአን እሴት ለጻድቃን
ፍጥም አያናግር የጎርፍ ሙላት አያሻግር
ፍጥም አፍራሽ ቤተክርስቲያን ተኳሽ
ፍጥም ያቀማል እርቅ ይጠቀልላል
ፍጥም ያዋውላል አቧራ ያስላል
ፎክሮ መሸሽ ታሪክ ያበላሽ

~ ተቋጨ ~